# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር 8ኛ ዓመት ቁጥር 1 መጋቢት/ሚያዝያ 1992ዓ.ም



## ደብረ ብርሃን ሥላሴ /ጎንደር/

/ታሪኩን ወደፊት እናወጣዋለን/

- ኢትዮጵያውያን ሃይማኖታቸውን፣ ባህላቸውንና ትውፊታቸውን የማወቅ ጥማትና ጉጉት አለባቸው።
  /የማኅበሩ መልእክት/
- ችግረኛው ጮኸ እና እግዚአብሔርም ሰማው
  /በረከተ ወንጌል/
- በጎቼን ጠብቅ
  /ትምህርት ሃይማኖት/
- የቤተክርስቲያን ትምህርት በዚህ መልኩም ቢቀርብ
  /ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ//

www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ስብከታችን ወቃሽ ባይሆን

ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ከወላጆቻቸው የሚይዛቸው ሕፃናት፣ ንጽሕናውን ካልጠበቀ የሕክምና አፈጻጸም የሚይዛቸው ሕሙማን፣ ካልታመነ የትዳር ጓደኛ የሚተላለፍባቸው ታማኝ ባለትዳሮች እና ተገደው በመደፈር የቫይረሱ ተሸካሚ የሚሆኑ መኖራቸውን መዘንጋት የለብንም:: ጉዳዩን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አንዳንድ ሰባክያነ ወንጌል ስለበሽታው ሲያነሱ የዝሙት ሰሰኞች ችግር ወይም መቅሰፍት እንደሆነ ይናገራሉ:: ይህ ደግሞ የሕሙማኑን ቅስም በመስበር ለበቀል የሚያነሳሳና ለበሽታው ሥርጭት መገታት የሚደረገውን ጥረት የሚያሰናክል መሆኑን ልብ ልንለው ይገባናል:: ስብከታችን ሕሙማን ወገኖቻችንን ሊያጽናና ወደ ቤተክርስቲያን ሊያቀርብ የሚችል ቢሆን መልካም ነው:: እግዚአብሔር አስተዋይ ልቡናን ይስጠን::

*ተናኜ ዓለሙ*
*አዲስ አበባ*

## ስእነማን እንደሚገባ

ባለሁበት በድሬዳዋ ከተማ ለብዙ ዓመታት «ባልና ሚስት» ሆነው በአንድ ላይ ሲኖሩ የቆዩ ወንዶችና ሴቶች ድንግልናቸውን ጠብቀው እንደቆዩ በመምሰል በተክሊል ሥርዓት ሲጋቡ በተደጋጋሚ እመለከታለሁ:: ሥርዓተ ተክሊል ለደናግል ብቻ የሚፈጸም ምስጢር ሆኖ ሳለ ለቪዲዮ ካሜራ ሲባል ሥርዓተ ቤተክርስቲያን መጣሱ አግባብ አይደለምና ተክሊል ለእነማን እንደሚገባ ያለመታከት ብናስተምር መልካም ነው:: በተክሊል ካላገባችሁ ወደእኔ አትመጡም አላለንም:: የንስሐ አባቶችም ልጆቻቸውን በመከታተል ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን መጠበቅ የበለጠ ቢጥሩ ጥሩ ነው::

*ኃይለማርያም ታደሰ*
*ድሬዳዋ*

## ስውሾች አትስጡ

መንፈሳዊ መጻሕፍትን እና ሥዕላትን ክብራቸውን በማይጠብቁ ቦታዎች /ለምሳሌ መጠጥ ቤት፣ ቪድዮ ቤት...ወዘተ. / መቀመጣቸው እንዳለ ሆኖ አሁን ደግሞ መዝሙር እየሰሙ ጫት መቃም እና ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ምግባራትን መፈጸም እየተለመደ መጥቷል:: በርግጥ ካለማወቅም ሊሆን ይችላል:: በልዩ ልዩ ሱሶች የተያዙ ሰዎች ወደ መንፈሳዊነት መመለሳቸው የሚፈለግ ቢሆንም እነርሱ ወደ ቅዱስ ቦታ ቢመጡ እንጂ ቅዱሳት ንዋያትን እና መዝሙራትን አጉል ቦታ እየወሰዱ ክብራቸውን ማሳነስ የለባቸውም:: ስለዚህ ይህ ተግባር ከቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚቃረን ነውና ቢታረም::

*በላቸው አከሉ*
*ከጂማ*

## በዚህም መጥተዋል

በታኅሣሥ 1992 ዓ.ም. እዚህ አዲስ አበባ አሥመራ መንገድ አካባቢ በሚገኘው ቀደም ሲል «ዘርፈሺዋል» እየተባለ በሚጠራው ትምህርት ቤት ላሉ መምህራን መናፍቃን የእነርሱን የ«መዝሙር» ክር እና በራሪ ጽሑፎች «የገና ሥጦታ» በሚል አድለዋል:: መምህራኑ እምነታቸውን ለወጡ ማለት በሥራቸው የሚያልፉ ተማሪዎች ለምን እየተጋለጡ እንደሚያልፉ ግልጽ ስለሆነ የመናፍቃኑ ይህ «ስጦታ» በዓላማና በጥናት የተደረገ ነው:: እንደውም በአንዳንዶች መምህራንም ቤተሰብ «መዝሙር» ተብሎ የተሰጣቸውን «እንሰማለን» «አትሰሙም» በሚል መከፋፈል እንደተፈጠረ አውቃለሁ :: ስለዚህ አሁን ደግሞ ዲያብሎስ በዚህ መጥቷልና እንጠበቅ:: የትምህርት ቤቶች አስተዳደሮችም ጉዳዩን ሊከታተሉት ይገባል::

*ኤፍሬታ*
*ከአዲስ አበባ*

## ሳይቃጠል በቅጠል

ወደ ድሬዳዋ ለሥራ ሄጀ በነበረበት ወቅት የድሬዳዋ ቅድስት ማርያም ሰንበት ት/ቤት ባሳየው አንድ መንፈሳዊ ቴአትር ላይ ተገኝቼ ነበር:: በእውነቱ መልእክቱ ጥሩ ሆኖ ሳለ የዓለማውያንን ሕይወት ለማንጸባረቅ ሲባል የተደረጉት አንዳንድ የመምሰል ድርጊቶች /ለምሳሌ አለባበስ ፣ ሰርግ / ግን አስፈላጊ አልነበሩም:: እንደእኔ እንደ እኔ ለውጭው ዓለም የአለባበስ ባህል የተገዙ ዓለማውያንን የአለባበስ ሁኔታ ለመግለጽ ያን ያህል አካላትን ማጋለጡ አስፈላጊ አይደለም:: የቴአትሩ ክፍል የሆነውን ሰርግ ለመሥራትም የሰርጉን ዘፈን ጆሮ እስኪነቅል ድረስ ከፍቶ የስብሐቱን ቦታ የጭፈራ ቤት ማስመሰሉም አግባብ አይደለም :: በተጨማሪ ቴአትሩ ሲያበቃ እንደ ሙዚቃ ተመልካቹ ምእመን ወደ መድረኩ እየ ተመመ በተዋንያኑ ግንባር ላይ ብር ሲለጥፍ ይታይ ነበር:: ሰንበት ትምህርት ቤቶች የየአባላታቸውን ተሰጥኦ እየተጠቀሙ በልዩ ልዩ መንገድ ወንጌልን መስበኩ የተገባ ቢሆንምና ይህ ጥሩ ተግባራቸው በምእመናን መደገፉ ጥሩ ቢሆንም እንደ ዚያ ዓይነቱ ግርግር ፈጠራ መኖር ያለበት አይመስለኝም:: ተዋንያኑም እንደዛ የለፋበትን ሥራ ውዳሴ ከንቱ በልቶት እንዳይቀር ይሄ ሁሉ ግርግር ቢቀነስ...ሳይቃጠል በቅጠል ብዬ ነው::

*ተስፋ ዘድንግል ዘበአማን*
*ሰሜን ወሎ*

## በመስከረም ልታብድ የፈለገች

ጊዜው እየተቀያየረ በመጣ ቁጥር የዓለም ባሕርይም እየበዛ ነው:: ታዲያ ዛሬ እንደ ዓለማውያን ከራስ ስሜት ጋር በማገናኘት የኮሌክሽን ሙዚቃ እንደሚባለው ሁሉ መዝሙሮችም እየተበላለጡ በኮሌክሽን መዘጋጀት ጀምጠረዋል:: መዝሙር ከመዝሙር፣ ቅዳሴ ከቅዳሴ አይበላለጥም:: ነገር ግን «በመስከረም ልታብድ የፈለገች ሴት በነሐሴ ቀሚሷን ከፍ ከፍ ታደርጋለች» እንደሚባለው ሁሉ መንፈሳዊ ይዘቱን ለቅቆ ችግር ከመምጣቱ በፊት ሁሉንም በእኩል ብናያቸውና በነገሩ ሁላችንም ከወዲሁ ብናስብበት መልካም ነው እላለሁ::

*ዲ/ን ሙሉጌታ መኮንን*
*ከኤፌሶን*

ቤተክርስቲያን ዶግማዋን፣ ቀኖናዋንና ሥርዓቷን ከዓለም ልዩ በሚያደርጋትና የእሷ ብቻ በሆነው ፊደሏ በመጻፍ፣ በአንደበቷ በመሰበክ ሰዎች ሁሉ የድኅነት ትምህርቷን እየሰሙ ወደእቅፏ እንዲገቡ ስታስተምር ቆይታለች። ወደፊትም ታስተምራለች። ታዲያ ቤተክርስቲያናችን የቀየ የማስተማሪያ ይትበሀል እያለች ኤግዚቢሽን ማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

/የማኅበሩ መልእክት/

መስቀል ተሳልሞ ይፍቱኝ የሚል ሞልቷል። ነገር ግን ምእመኑ ከኃጢአት ማሰሪያ ኃጢአቱን ተናዞ ቄሱ በቤተክርስቲያን ስም የሚሰጠውን ቀኖና ሲፈጽም እንጂ መስቀል ተሳልሞ ይፍቱኝ በማለት ብቻ ኃጢአቱ አይወርድም። በእርግጥ የሀልዮን ኃጢአት ሊያስተሰርይ ይችላል። ለነቢቡና ለገቢሩ ኃጢአት ግን ቀኖና ያስጠ ፈልገዋል።

/ትምህርተ ሃይማኖት/

ማኅበሩ በአንድ ርዕሰ መንበር የሚተዳደር በዘጠኝ የተከፈለ ነበ ር ። ዘጠኝ ደወልም ነበረው። የተለያዩ የቤት እንስሳት ሲኖሩት መልካቸውም በሙሉ ነጭ ነበር። ደብረ በልበሊት የተባለበት ምክንያት ደግሞ ፊቅጦር የተባለ ሰው... .

/እናስተዋውቃችሁ/

ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት የምደፍረው በእምነት ስለምጸ ምረው ነው ብዬ አምናለሁ። ሴት ልትሠራው አይገባም የሚባለውን ሥራ ሁሉ ለመሥራት፣ በራሴ ለመተማመን ችያለሁ። ለዚህ ሁሉ ደግሞ ክርስትና መሪዬ ነው።

/ዓምደ ወራዙት/

ቤተክርስቲያናችንን የዕውቀት ምንጭ የሚያስብሏት የሥነ ዜማ ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የሥነ ሕንፃ ወዘተ... ዕውቀቶቿ እንደ ዕንቁ የዕውቀት ሀብትነታቸው ከአብራኳ በተከፈሉ ልጆቿ አንድ በአንድ እየተመዘዙ ተጠንተው ለትውልዱ በሚገባ መልኩ አልቀረቡም።

/ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ/

«አቤቱ ወደእረፍትህ ተነሥ » /መዝ 131፡8/

**እንኳን ለብርሀነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!**

ዋና አዘጋጅ - ግርማ ወ/ሩፋኤል
ም/ዋና አዘጋጅ- መርሻ አለኸኝ

ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

E -mail-EOC-M-KIDUSAN @ telecom.net.et.

ሐመር
8ኛ ዓመት ቍጥር 1
መጋቢት/ ሚያዝያ 1992 ዓ. ም

## ይዘት

የማኅበሩ መልእክት
- ኢትዮጵያውያን ሃይማኖታቸው፣ባሕላቸውንና ትውፊታቸ ውን የማጠቀ ጥማትና ጉጉት አለባቸው ........ 2

ድብዳቤዎች ........ 4

በረከተ ወንጌል
- ችግረኛው ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው ........ 6

ትምህርተ ወንጌል
- ቃል ........ 8
- በጎቹን ጠብቅ ........ 11

ምዕራፍ ........ 13

እናስተዋውቃችሁ
- ደብረ በልበሊት ኢየሱስ ገዳም ........ 14
- የሐንስ ኅፃር ........ 16

የዓምደ ወራዙት
- ዓላማ ያለው የወጣትነት ሕይወት ........ 20

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- የሥነ ልቡናና የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ በሌች. አይ. ቪ. ኤድስ ዙሪያ.. ........ 24
- ምንተንግበር ........ 27

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
- የቤተክርስቲያን ትምህርት በዚህ መልኩም ቢቀርብ ........ 29

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐድ አምላክ አሜን

## ኢትዮጵያውያን ሃይማኖታቸውን፣ባሕላቸውንና ትውፊታቸውን የማወቅ ጥማትና ጉጉት አለባቸው

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ባሳለፈቻቸው ረዥም ዘመናት በየጊዜው ያጋጠሟትን የተለያዩ ፈተናዎች በማለፍ ለኢትዮጵያ መታወቅንና በረከትን ያስገኙና የሚያስገኙ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳትና ቅርሶች ባለቤት ለመሆን በቅታለች፡፡ ሀገራችን በጦርነትና በረሃብ በዓለም ሕዝብ ዘንድ ስትታወቅና እኛም በእነዚህ ወቅታዊ ሁኔታዎች አንገታችንን እንድንደፋ የ ተገደድንበት ወቅት ሁሉ በየትኛውም ቦታ በሐፍረት ደፍተነው የነበረውን አንገታችንን ቀና እንድናደርግና በኩራት ስለአገራችንና ስለሃይማኖታችን መናገር እንድንችል ያስቻሉንንና የእኛነታችን መለያ የሆኑ ቅርሶቻችንን ልዩ ልዩ መከራዎችን ሁሉ በጽናት ተቋቁመው ለእኛ ያቆዩልንን አባቶቻችንን ከልብ ልናመሰግናቸው ይገባል፡፡ ቁጥራቸው የበዛ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በስፋት በሚወራብንን የጦርነትና የረሃብ ዜና ሳይሸሹ ወደአገር ቤት እንዲጎርፉ የሚያደርጋቸው አገሪቱ ካላት የተፈጥሮ ውበት በተጨማሪ በዋነኛነት የቤተክርስቲያን ሀብታት የሆኑ ንዋያተ ቅድሳትና ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት መሆናቸው የማይታበል ሃቅ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ከላይ የተገለጸው የአባቶቻችን ተጋድሎና ጥንቃቄ እንዳለ ሆኖ፤ በጦርነት፣በዘረፋና በአያያዝ ጉድለት ቁጥራቸው ቀላል የማይባልና በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ ንዋያተ ቅድሳትና ቅርሶችን ማጣታችን የሚታወቅ ነው፡፡ ለዚህም በዮዲትና በግራኝ መሐመድ ወረራ የተቃጠሉትንና በመቅደላ ጦርነት ወቅት ብቻ ተዘርፈው ወደ እንግሊዝ የተወሰዱትን በሺህ የሚቆጠሩ ንዋያተ ቅድሳትንና ቅርሶችን ማስታወስ ይበቃል፡፡

በሌላ በኩል ግን በእግዚአብሔር ቸርነትና በአባቶቻችን ትጋት በአገር ውስጥ ቁጥራቸው እጅግ የላቀ ንዋያተ ቅድሳትና ቅርሶች በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በሚገኙ አድባራት፣ገዳማት፣ሙዝየሞችና ታሪካዊ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህን ሀብቶቻችንን በተገቢው መንገድ መዝግቦና በጥንቃቄ ጠብቆ ማቆየት የምንችልበትን መንገድ መፈለግና በተግባር ላይ ማዋል ለነገ የማይባል የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ሊሠሩ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ ትውልዱ ሀብቱን ዐውቆ ለሕልውናቸው /ለደኅንነታቸው/ ዘብ እንዲቆም ማድረግ ነው፡፡ ትውልዱ የቀድሞ አባቶቹ በታላቅ ተጋድሎ ያቆዩለትን ንዋያተ ቅድሳቱንና ቅርሶቹን መጠበቅና መንከባከብ የሚገባቸውንም ክብር መስጠት የሚችለው ስለምንነታቸውና ስለማንነታቸው የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረው ሲደረግና የባለቤትነት ስሜት በውስጡ ሲያድር ብቻ ነው፡፡

ይህን ነጥብ በዋና ዓላማነት በመያዝም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር መንፈሳዊ አገልግሎቱን በመስጠት ላይ የሚገኘው ማኅበራችን «የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንት፣ዛሬና ነገ» በሚል ዐቢይ ርዕስ ከመጋቢት 17–24 ቀን 1992 ዓ.ም ታላቅ ኤግዚቢሽን በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል አዘጋጅቶ ለሕዝብ ሊያቀርብ ችሏል፡፡

ቤተክርስቲያን ዶግማዋን፣ቀኖናዋንና ሥርዓቷን ከዓለም ልዩ በሚያደርጋትና የእሷ ብቻ በሆነው ፊደሏ በመጻፍ፣በአንደበቷም በመስበክ፤ ሰዎች ሁሉ የድኅነት ትምህርቷን እየሰሙ ወደእቅፏ እንዲገቡ ስታስተምር ቆይታለች፡፡ ወደፊትም ታስተምራለች፡፡ ታዲያ ቤተክርስቲያናችን የቆየ የማስተማሪያ ይትበህል እያላት ለምን ኤግዚቢሽን ማዘጋጀት አስፈለገ?

ኤግዚቢሽን ስፊ የዕውቀት ዘርፎች በአንድ ቦታ ጠቅለል ብለው ለዕይታ የሚቀርቡበት መድረክ ነው፡፡ በመሆኑም የቤተክርስቲያናችንን የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክና በዚህም ዘመን ያካበተቻቸውን ሀብታት /ቅዱሳት መካናት፣ንዋያተ ቅድሳት፣መጻሕፍት፣ቅዱሳት ሥዕላት ወዘተ/ በአንድ ቦታ አቅርቦ የቤተክርስቲያን ልጆች የበለጠ እንዲያውቁ፣በተለያዩ ምክንያቶች ከቤተክርስቲያን ጉያ የወጡና ከቶውኑም ያልገቡ ሰዎች የቤተክርስ ቲያንን ማንነት እንዲረዱ ለማድረግ ኤግዚቢሽኑ ተዘጋጅቶ ነበር ከዚህ በተጨማሪም ከመስማት የበለጠ ማየት ዕውቀትን ያቀርባልና ትውልዱ በጆሮው የሚሰማውን በዓይኑ እንዲያይና ኃላፊነቱን እንዲወጣ ለማድረግ ኤግ ዚቢሽኑ አስፈልጓል፡፡ ስለ ቤተክርስቲያናችን ለማስተማር መፈለጋችን በዚህ መልክም ማቅረባችን ከላይ ከተ ጠቀሱት ምክንያቶች በመነሣት ነው፡፡ ያሰብነው ለመሳካቱ ደግሞ ምስክሮቻችን የኤግዚቢሽኑ ተመልካቾች ናቸው፡፡



www.eotcmk.org

በቤተክርስቲያናችን ታሪክ አንድ ኤግዚቢሽን በዚህ መልኩ በስፋት ሲዘጋጅ የመጀመሪያው እንደመሆኑ ከአዘጋጆቹ የልምድ ማነስ በተጨማሪ ከኤግዚቢሽን ዝግጅት የሥራ ባሕርይ አስቸጋሪነት የተነሣ የዝግጅቱ መንገድ አልጋ በአልጋ አልነበረም። ለዝግጅቱ ከሚያስፈልገው የገንዘብ እጥረት ጀምሮ የአንዳንድ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለዕይታ የሚቀርቡ ንዋያተ ቅድሳትን አንሰጥም እስከማለት ድረስ በርካታ ችግሮች አጋጥመውን ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ በጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤትና ከሥሩም ልዩ ልዩ መምሪያዎች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣ሰንበት ት/ቤቶች፣ምእመናን እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ርብርቦሽ ኤግዚቢሽኑ ዕውን ሆኗል። በእውነቱ ማኅበሩ ከተቀጠሱት ክፍሎች ያገኘው ድጋፍና ትብብር ይህን ዓይነቱን ዝግጅት ወደፊትም በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀጥልበት የሚያደርግ መሆኑን ያምናል።

ማኅበራችን ኤግዚቢሽኑ በቀረበበት ሳምንትም ሆነ ከዚያ ወዲህ ተመልካቾች በጽሑፍና በቃል የሰጡትንና እየሰጡት ያለውን አስተያየት ሲያይ በርካታ ነገሮችን ተረድቷል። ከተረዳቸው ነገሮችም አንዱ ኢትዮጵያውያን በተለይም የቅድስት ቤተክርስቲያናችን ልጆች ታሪካቸውን፣ባሕላቸውንና ትውፊታቸውን የማወቅ ጥልቅ ጥማትና ጉጉት እንዳላቸው ነው። ሌላ አብነት ሳያስፈልግ በኤግዚቢሽኑ ሳምንት በማዕከሉ የነበረው ሰልፍና ሽሚያ ለዚህ ዐብይ ማስረጃ ነው። አባ ወራዎች ቤተሰባቸውን ያዘው፣ጨቅላ ሕፃናት ያዘሉ እናቶች በጠራራ ፀሐይ እየተቆሉ ለሦስት አራት ሰዓታት በትዕግሥት ሰልፍ ይዘው ቆመው ሲደርሳቸውም ረጅም ሰዓት የሚወስደውን ጉብኝትና ገለጻ በንቃት ተከታትለው ሲሄዱ ያም ሆኖ በጊዜው መገታት የተነሣ ከክፍለ ሃገር የመጡም በርካታ ምእመናን የማየት ዕድል ሳያገኙ ሲመለሱ ያየ የሚረዳው ይህንኑ ከላይ ያልነውን ቤተክርስቲያኑን የማወቅ ጉጉት ነው።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ጥማቱን የሚያረካለት ይፈልጋል። ዛሬ አንዳንድ የቤተክርስቲያን ልጆች ለመጤ የእምነት ድርጅቶች በቀላሉ እጃቸውን የሚሰጡትም ከዚህ የተነሣ ነው። ምናልባት ቅልውጥና ባሕርይው የሆነ ካልሆነ በስተቀር በቤቱ ጠግቦ እንደሚያድር የተረዳ፣በቤቱ ያለው ለእሱ ብቻ አይደለም። ለሌሎችም እንደሚተርፍ ያወቀ ሰው የሞቀና የሞላ ቤቱን ትቶ ቅልውጥና ወደሌሎች ቤት አይሄድም። ስለዚህ ምእመናን በደስታና በመፈቃቀር ምድራዊውንና ሰማያዊዉን መንገዳቸውን እያስተካከሉ እንዲቀመጡ እናት ቤተክርስቲያናቸውን እንዲያውቁ ማድረግ ይገባል።

ቤተክርስቲያን እንደ የልጆች እናትነቷ ይህንን የማሳወቅ ተግባር እስከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ ከዚህ በበለጠ በግንባር ቀደምትነት ልታከናውን ይገባል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት አግዚቢሽኑን አስመልክተው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫና ኤግዚቢሽኑንም ሲከፍቱ ባዳረጉት ንግግር እንደገለጹት ይህ ዓይነቱ ኤግዚቢሽን ወደቋሚነት ተለውጦ ምእመናን ዕለት ዕለት እያዩ እንዲማሩና እነሱንና ቤተክርስቲያናቸውን እንዲጠብቁ መደረግ አለበት። አኀጉረ ስብከት እንደ ልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት አቃፊነታቸው ንዋያተ ቅድሳት በተገቢው ቦታ እንዲቀመጡና አድባራቱና ገዳማቱ የየራሳቸው ሙዝየም እንዲኖራቸው ማድረግ አለባቸው። ምእመናንም እንደባለሀብትነታቸው በአንዳንዶች ዘንድ የሚታየውን ለክብር ሲባል የተለያዩ ቅርሦችን በቤት የማስቀመጥ መጥፎ ልማድ ከአካባቢያቸው አስወግደው፣ንዋያተ ቅድሳቱን በመንከባከብ ዘብ መቆም አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ ከሰንበት ት/ቤቶች ጀምሮ ለሚደረገው ለእንዲህ ዓይነቱ ዝግጅት ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

የሰዓታቱን ሰልፍ ጠብቀው አግዚቢሽኑን ያዩት የቤተክርስቲያናችን ልጆች ብቻ አልነበሩም። የውጭ አገር ዜጎች፣የእስልምናና የሌሎች የእምነት ድርጅቶች ተከታዮች ሁሉ ናቸው። ይህም የቀረበውን ዝግጅት ከአንዲት ቤተክርስቲያን አልፎ ብሔራዊ ያደርገዋል። ይህንንም የባሕልና የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ወልደ ሚካኤል ጨሞ ንግግር፣ የከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆነ የውጭ አገር አምባሳደሮችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የጽሑፍ አስተያየት ይህንኑ ይመሰክራል። በመሆኑም መንግሥት ለእንዲህ ዓይነቱ ብሔራዊ ዝግጅት በልዩ ልዩ መልኩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። ቤተክርስቲያናችን ዕውቀቷና እንቅስቃሴዋ ሁሉ ብሔራዊ አልፎም ዓለም አቀፋዊ ናቸው። ስለዚህ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ላስተዋወቀች ቤተክርስቲያን ከዚህ በበለጠ አጋዥና አይዞሽ ባይ መሆን አለበት።

በመጨረሻም ይህ ኤግዚቢሽን ዕውን እንዲሆን ዝግጅቱን ስፖንሰር ያደረጉትን ድርጅቶች፣በጸሎታቸው፣በምክራቸው ፣በገንዘባቸውና በሙያቸው ለረዱን ግለሰቦችና ድርጅቶች፣ዝግጅቱን ለማየት ዕድል ላላገኙትም ባሉበት እንዲደርሳቸው ያደረጉትን የግልና የመንግሥት የመገናኛ ብዙኃንን እንዲሁም ረጅሙ ሰልፍና የሚወርደው ፀሐይ ሳያሰለቻቸው በእኛ ትእዛዝ መሠረት ፍጹም ክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ ራሳቸውን በማስተናገድ ኤግዚቢሽኑን ያዩ፣ካዩም በኋላ ደስታቸውን፣አስተያየታቸውንና ምክራቸውን የለገሱንን ምእመናን ሁሉ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን። አሁንም በቀጣዩ የአገልግሎት እንቅስቃሴያችን ሁሉ ከጐናችን እንደማይለዩን ጽኑ እምነት አለን ። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያናችንን ይጠብቅ ። አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## እግዚአብሔር ይባርካችሁ

እግዚአብሔር ፈቅዶ ከነቤተሰቦቼ ወደ ኢትዮጵያ መጥቼ በነበረ ጊዜ ላደረጋችሁልኝ ቃለ መጠይቅ የሰጠሁትን መልስ በሐመር መጽሔት 7ኛ ዓመት ቁጥር 5 እትም ላይ ሰፍሮ አየሁት ። በጥንቃቄ የሰጠኋችሁን መልስ ሳለመተላለፍ ያደረጋችሁትን ጥንቃቄ በእጅጉ አደንቃለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ይሁንና የሚከተሉትን ነጥቦች ምናልባት ማስተካከያ የምትሰጡበት አጋጣሚ የሚኖር ከሆነ እንዲስተካከሉ ይሁኑ ። በመግቢያው ላይ በ1965 ዓ.ም. ከአባታቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ መጡ የሚለው በ1958 ዓ.ም. ፤ ወረድ ብሎም «የሙንሺን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በብፁዓን አባቶች ብፁዕ አቡነ ዮሐንስና ብፁዕ አቡነ እንድርያስ» የሚለው በቀድሞዎቹ ብፁዓን አባቶች ብፁዕ አቡነ ዮሐንስና ብፁዕ አቡነ ኤልያስ/ ፤ አሁንም በዚያው ገጽ ዝቅ ብሎ «በቤተክርስቲያናቸው ጥላ ሥር እንዲሰባሰቡ ለማድረግ በኑርምበርግ፣ በሽቱትጋርት፣ <u>በባይቱነምበርግ</u>፣ <u>በጋትሮሴ</u>» በሚለው የተሰመረባቸው በባደቡተንበርግ፣ እና በካርልስሮሄ በሚል ይስተካከሉልኝ እላለሁ። ሰላመ እግዚአብሔር አይለያችሁ።

*ቀሲስ መስፍን ገብረማርያም*
*ሙንሺን ቅዱስ ገብርኤል*
*ቤተክርስቲያን /ጀርመን/*

## እንደእኔ እንደእኔ

በሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር 5 በደብዳቤዎቻችሁ ዓምድ «በመንፈስ ጀምሮ በሥጋ መጨረስ » በሚል አቶ በድሉ በኤድስ ፣ በሥራ አጥነት እና በድህነት ላይ እያደረጋችሁት ያለውን ትኩረት «በሥጋ መጨረስ» በማለታቸው በጣም አዝኛለሁ። እኔ ባለሁበት በጨንቻ ወረዳም በከተማው በሚገኘው ሰንበት ት/ቤት አንድ ዲያቆን ከኤድስ ስለመጠበቅ በማስተማሩ አንዳንድ የሰንበት ት/ቤቱ ተማሪ ዎች ተቃውሞ አስነስተውበት ነበር።ለመሆኑ ቤተክርስቲያን ራሷ ብዙ ሺ ብር መድባለት እየታገለችለት ሳለው ዓላማ የእኛ እንቅፋት መሆን ከየት የመጣ ነው? የተራበን ሕዝብ ለቁመተ ሥጋ የሚሆን ነገር ሳንሰጠው፣ በሽታ ሳንገርበበት ሕዝብም የሚጠበቅበትን መድኃኒት ቀድም ብለን ሳንነግረው እንዴት እንስበክህ ልንለው እንችላለን ? እንደእኔ እንደእኔ አሁንም ኤድስ፣ ረሃብ፣ ድህነት፣ ሥራአጥነት ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል።

*ዲ. ወንድወሰን*
*/ፊቢ ንቻ/*

## የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የምትሠሩት ሥራ የሚያስመሰግን ነው። እኔም የሐመር ማዕድ ተቋዳሽ ከሆንኩ ሰንብቻለሁ። «የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ» ሆነብኝና አስተያየቴን ልጽፍ ተነሳሁ ። በመጽሔቷ ልባስ /ሽፋን/ ላይ የሚወጡት ፎቶግራፎች የብዙዎቻችንን ትኩረት የሚስቡ ናቸው። ሆኖም ግን የሽፋን ፎቶግራፉን ሙሉ ገጽ እንደሽፋን ብታደርጉት፣ ስለፎቶው የሚያትተው ጽሑፍ፣ የማኅበሩ አርማ እና በውስጥ ገጾች ስለተተነተኑት ጉዳዮች ፍንጭ የሚሰጡ ጠቋሚ ሐረጎች ሊነበቡ በሚችሉ ቀለማት ቢሰፍሩበት ጥሩ ነው እላለሁ። ለዓይን የሚስብና ለንባብ የሚያጓጓ ይሆናልና። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሐመር 6ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም ናት። የእግዚአብሔር ረድኤትና የእመአምላክ እገዛ ከእናንተ ጋር ይሁን።

*የምሥራች ወ/ገብርኤል*
*መልካ ዋከና ኃ/ማ/ማቢ.የ*

## በዚሁ ይቀጥል

በ « እናስተዋውቃችሁ» ዓምድ ሥር የምታወጧቸው ጽሑፎች መንፈስን የሚጠግኑ ናቸው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። ይህን የሚመሰክረው ዓምዱን በትኩረት የሚያነበው ሁሉ ነው። በሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር 6 ላይ የሰፈረው የአባ አብርሃምና የጫማ ሰፊው ስምዖን ታሪክ በእውነቱ መንፈሴን ያደሰ ነው። ከጽሑፉም በዐቢይነት የተረዳሁት የተናቁ ከሚመስሉ ሰዎች ዘንድ ስለሚገኘው ድንቅ በረከት ነው። ልማድ ሆኖብን ድሆችን፣ አካለ ስንኩላንን... ምንም እንዳልሆኑና አንዳች እንደማይጠቅሙ አድርገን እናያቸዋለን። የእነ ስምዖን ጫማ ሰፊው ታሪክ ግን ተቃራኒውን በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የነአባ አብርሃም ምልጃ፣ ረድኤትና በረከ ታቸው አይለየን።

*ገ/ ኢየሱስ*
*ከርቤ ቅ/ገ/ክርስቶስ*
*ሰ/ት/ቤት ባሌ*

## በግንባርም ሆኜ አስባችዋለሁ

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን። (2ኛቆሮ 13÷14) እንደምን አላችሁ? ምንም እንኳን በጦር ግንባር ስለምገኝ ለጊዜው የመጽሔታችሁ እና የትምህርታችሁ ተካፋይ ባልሆንም በሀሳብ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። በቃለ እግዚአብሔር ብታጽናኑንና ብትመክሩንም እንወዳለን። ወደግንባር ከመሄዴ በፊት አስተምረው ሰው አድርገው የቀረጹኝን ሰንበት ት/ቤቶችንና መንፈሳውያን ወንድምና እኅቶቼንም በግንባርም ሆኜ አስባቸዋለሁ። ስለዚህም በሰሜን ጎንደር አዘዞ ከተማ ለሚገኙ ለደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል፣ ለደብረሰላም ለዛ ማርያም፣ ለደብረ ቅዱሳን አቡነ ተክለሃይማኖት ሰንበት ት/ቤቶች ሰላምታዬን አቅርቡልኝ።

*ወታደር አበራ ተስፋ*
*ከምስራቅ ትግራይ*
*እንትጮ ከተማ*

## በእናንተ በኩል...

እንደምን አላችሁ? በአገራችን በበረሃነቱ በሚታወቀው በአፋር ክልል የምኖር ወጣት ነኝ። ታዲያ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በክልላችን የክርስትና እምነት በሚፈለገው መልኩ የተስፋፋ አልነበረም። ምክንያቱም ያሉት ክርስቲያኖች ዕለት ዕለት ተምረው የሚጠነክሩበት ዕድሉ ስለሌላቸውና አካባቢውም እስልምና የተስፋፋበት ስለነበር ነው። አሁን ግን እሥራኤላውያንን በግብጽ ባርነት ባሉ



www.eotcmk.org

ጊዜ ያልረሳቸው አምላክ እኛንም ሳይረሳን በሀገረ ስብከቱ በተሾሙት አባታችን ብፁዕ አቡነ ዮናስና ረዳቶቻቸው አማካኝነት ስብከተ ወንጌሉ እየተጠናከረ፣ የጠፉት ሕዝቦች እየተሰበሰቡ፣ ሀገረ ስብከቱም የቤተክርስቲያናችንን ሥርዓቶች ሱታፌን እያገኘ መጥቷል:: እባካችሁ ይህ ለብፁዕነታቸው ከንቱ ውዳሴ አይደለምና ሌሎች የበረሃ አኅጉረ ስብከትም ከዚህ ትምህርት እንዲወስዱ ብፁዕ አቡነ ዮናስን አመስግኑልኝ:: ረጅም ዕድሜን ከሙሉ ጤንነት ጋር እንዲሰጣቸው ጸሎታችን እንደሆነ ግለጹልን::

*ከሀገረ ስብከቱ ነዋሪዎች*

## ይጠንቀቁ

ሐመሮች ሌሎች ወንድሞችና እኅቶች እንዲጠነቀቁ ይህችን ደብዳቤ ጽፌያለሁና ብታስተናግዱልኝ:: ነገሩ እንዲህ ነው፤ አንድ የማኅበረ ቅዱሳን አባል ነኝ የሚል ሰው ከዚህ ኮሌጅ ከ ዚህ ዩኒቨርሲቲ በዚህ ዓመተ ምሕረት ነው የተመረኩት እያለና በየቦታው የሚገኙትን የማኅበሩን አባላት ስም እየጠቀሰ በማጭበርበር ላይ ይገኛል:: ይህን ንም የተረዳሁት ይህ ሰው ባለፈው የካቲት ወር ላይ እኔ ወደምኖርበት አገር /መተሐራ / መጥቶ ነበር:: ተዲያ እንደመጣ ወደ ቤተክርስቲያን ጎራ ብሎ የመንግሥት ሠራተኛ የሆነ የቤተክርስቲያን ሰው አስተዋውቁኝ ይላል:: ሰዎች ከእኔ ጋር ያስተዋውቁታል:: ታዲያ ይህ ሰው ባሕር ዳር የሚሠራ የማኅበሩ አባል እንደሆነና በአሁኑ ወቅት የደረሰበትን ችግር ከተረከልኝ በኋለ ወደሥራ ቦታው የሚሄድበት ገንዘብ እንደሚፈልግ ነገረኝ:: እኔም የተወሰነ ብር ሰጥቼ ሸኘሁት:: በኋላ ስሰማ በአፋር ንዑስ ማዕከል የሚገኙትን የማኅበሩን አባላትም አታሎ ልብስና ብር ወስዶባቸዋል:: ስለዚህ የዚህን ወጣት ሥራ ሁሉም የማኅበሩ አባላት ዐውቀውት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አደራ እላለሁ::

*ወ/ትንሣኤ*
*ከመተሐራ*

<u>ከአዘጋጁ:</u> እንደዚህ ዓይነት ጥቆማዎች ሲደርሱን ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለምና በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ የማኅበሩ አባላት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ታደርጉ ዘንድ እናሳስባለን::

## ከአገር ርቀን

በ7 ኛ ዓመት ቁጥር 6 እትማ ችሁ ስለቤተክርስቲያናችን የውጭ እንቅስቃሴ ከአንድ አባት ጋር ያደረ ጋችሁትን ቃለ ምልልስ አንብቤ እጅግ ተደስቻለሁ:: በእውነቱ በቀሲስ ከፈለኝ አማካኝነት «በውጭው ዓለም የእኛ ቤተክርስቲያን የምትታየው በእሾህ መካከል እንደፈነዳች አበባ ነው::» በሚል ያስፈራችሁት መልእክት እጅግ አስተማሪ፣ በክርስትናም አጽንኦት የሚያ ቆይ ነው:: በተለይ ከአገር ርቀን ለምን ገኝ ኢትዮጵያውያን ሲከፋን መሸሸጊያና ተስፋ ስንቸገር መካሪ የሆነች ቤተ ክርስቲያናችን ምንጊዜም የምታኮራና የምታስመካ በመሆኗ ልንጠብቃት እንዲሁም ልናውቃት ያስጠፈልጋል:: እግዚ አብሔር ፀጋውን ያብዛላችሁ::

*ዮዲት ሽንቁጤ*
*ካይሮ ስ/ት/ቤት*

## አዘንባችሁ

የመጽሔታችሁ ደንበኛ ነኝ:: ባለፈው ባወጣችሁት ሐመረ ጽድቅ መጽሔት አንዳንድ ዓለማዊ ማስታወቂያዎችን /ከምንም በላይ ጣፋጭና የማይጠገበው የፈጣሪ ቃል በሚነገርበት ገጽ ላይ/ በማየታችን ያች የምንወዳት መጽሔት ሳትሆን ሌላ መስሎን ስንቸገር ነበር:: በእውነቱ አዘንኩባችሁ:: ምናልባት ከገቢ አንጻር የግድ መደረግ አለበት ከተባለም ከውስጡ አንዱን ገጽ ወይም ሁለቱን መጠቀም ስትችሉ በምንጓጓላቸው ገጾች እንደዚያ ያሉ ለሥጋ ብቻ የሚጠቅሙ ማስታወቂያዎችን ማውጣታችሁ ጥሩ አልነበረም:: ይህ ደግሞ እኛን ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን የመጽሔታችሁንና የጋዜጣችሁን አንባብያን ያነጋገረ ነው:: እባካችሁ አስቡበት::

*ሶስና መኮንንና ፀሐይ አለነ*
*/አዲስ አበባ/*

<u>ከአዘጋጆች:-</u>

የዚህ ዓይነት ይዘት ያላቸው አንዳንድ መልእክቶችም በተመሣሣይ ደርሰውናል:: ሁላችሁም ለሰጣችሁን አስተያየት ከልብ እያመሰገንን በስፖንሰርነት የተሳተፉ ድርጅቶችን በተመለከተ ማስተወቂያውን ያወጣንበትን ምክንያት ለመግለጽ እንወዳለን::

ልዩ እትሙ የወጣው ከመጋቢት 17-/1992 ዓ.ም ድረስ በተከናወነው ኤግዚቢሽን ሣምንት ነበር:: ማኅበሩም ይህንን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን አስተማሪ ዝግጅት ለማቅረብ የተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል:: ከነዚህ ዘዴዎች አንዱ ከትምህርተ ክርስትና ጋር ግጭት የሌላቸው ድርጅቶችን በስፖንሰርነት ማሳተፍ ነበር:: ድርጅቶችም በተሳትፎአቸው ከሚያገኙት ጥቅም መካከል በመጽሔቱ ላይ ራሣቸውን ማስተዋወቁ ዋነኛው ነው:: በመጽሔቱ ላይ የድርጅቶቹ መውጣት የዚህ ውጤት መሆኑን ትረዱልን ዘንድ በትህትና እንገልጻለን::

## ዋጋችሁን ይክፈላችሁ

በቅድሚያ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ:: ከመጋቢት 17–24 ቀን 1992 ዓ.ም. ያዘጋጃችሁትን ኤግዚቢሽን ተመልክቼዋለሁ:: የተሰማኝ ደስታና ኩራት ይህ ነው አይባልም:: በተለይም እንደእሸን የሚፈሉ የመናፍቃን ድርጅቶች በበዙበት በአሁኑ ወቅት ኤግዚቢሽኑ ትልቅ ድንጋጤና ራስ ምታት እንደሚሆንባቸው ግልጽ ነው:: በእውነቱ ይህንን ላሳየን አምላክ ክብር ምስጋና ይድረሰው:: የሥራው መገለጫ እንድትሆኑ ስለመረጣችሁም እስከመጨረሻው ህቅታ ፀንታችሁ እንድታገለግሉት ኃይሉንና ዕናቱን ይስጣችሁ:: በመጨረሻም እንዲህ ዓይነቱ ኤግዚቢሽን ከአዲስ አበባም ውጭ ቢዘጋጅ ብዙዎች ወገኖቻችንን ስለሃይማኖታቸው ከፍተኛ ዕውቀትና ግንዛቤ ያስጨብጣል ብዬ አምናለሁ:: በተረፈ እግዚአብሔር የድካማችሁን ዋጋ ይክፈላችሁ::

*ዓለማየሁ ታደሰ*
*ከጨርቆስ*

## ተከታታይነቱን ቢጠብቅ

በ7ኛ ዓመት ቁጥር 6 ዕትም ላይ በ«ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ» ዓምድ ባለሙያዎች በኤድስ ዙሪያ ላይ የሰጡትን አስተያየት ያቀረበው ዘገባ እጅግ ጥሩና ወቅታዊ ከሃይማኖትም አንፃር መካሪ የእግዚአብሔርንም መኖር እንድናውቅ የሚያደርግ ነው:: ሆኖም ግን ባልተለመደ መልኩ የገጽ አጠቃቀ ማችሁ የጽሑፉን ተከታታይነት በፍለጋ እንዲገኝ አድርጎታል:: ስለዚህ ለወደፊቱ ተከታ ታይነቱ ለአንባቢ አመ ቺ በሆነ መልኩ ቢሆን መልካም ነው እላለሁ::

*ተስፋዬ ገበየሁ*
*ከሞያሌ–ኢትዮጵያ*



www.eotcmk.org

# ችግረኛው ጩኸ እግዚአብሔርም ሰማው

*ከባሮክ*

በዚህች መሬት የሚኖር የሰው ልጅ ሁሉ በችግር የሚኖር መሆኑና ሰውና ችግርም ባልንጀራ ሆነው አብረው የዘለቁ መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባውም:: ችግር የአዳም ልጆች ሁሉ ገንዘባቸው ሆኖ ኖሯል፤ ከአባታቸው የወረሱት ሀብታቸው ነውና:: በመሆኑም ችግር ያልዳበ ሰውና የኑሮ ደጃፉን የሕይወት በሩን ያላንኳኳው የሰው ወገን አለ ለማለት የሚያስደፍር አይመ ስለኝም::

ችግር ስንልም በብዙ ጎብር ልንፈታው እንደምንችል ግልጽ ነው:: እንደሰዉ የችግሩም ዓይነት ልዩ ልዩ ነው:: ችግርን ግን በሁለት ዓበይት ክፍሎች ልንገልጠው እንችላለን:: ችግር ሥጋዊ /ቁሳዊ/፣ ችግር መንፈሳዊ:: ሥጋዊ ቁሳዊ ችግር የጸናበት ስለሀብቱ፣ ስለሹመቱ፣ ስለዝናና ክብሩ፣ስለቁመናውና ውበቱ፣ስለ እርጅናውና ስለወጣትነቱ ሲጨነቅ ይኖራል:: ችግር መንፈሳዊ የጸናበት ደግሞ ዕውቀት መንፈሳዊ ጎድሎት፣ የማስተዋል፣ የመታገሥ፣የማፍቀር፣ የቸርነት፣ የየዋህነት ፣ራስን የመግዛት፣ የሰላማዊነት፣እና የመሳሰሉትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች አጥቶ ሲንገላታ ይኖራል:: መንፈሳዊ ችግር ለምነው ወይም ተውሰው፣ወይም ተበድረው የሚወጡት ሳይሆን በተግባር ሆነው ብቻ መፍትሔ የሚሰጡት ረቂቅ ነውና ለየት ያለ አትኩሮት የሚሻ ነው::

ሰው የዕውቀት ችግረኛ ነው ሲባልም ዕውቀት መንፈሳዊ ወይም ዕውቀት ሥጋዊ የጎደለው ማለት ይሆናል:: ዕውቀት ሥጋዊ በመንፈሳዊ ዕውቀት ካልተቀመመና ለዕውቀት መንፈሳዊም የሚታዘዝ ካልሆነ ዕውቀትነቱ፣ጥበብነቱ ቀርቶ መርዝ ወደመሆን ሊለወጥ እንደሚችልና በዚህም ምክንያት ሀገርንም፣ትውልድንም የሚጎዳ ሊሆን የሚችል መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም:: ስለዚህም ዕውቀት መንፈሳዊ የጎደለው ሰው ችግር እርግጥ ከፍ ያለ መሆኑ እሙን ነው::

በተለይም ትምህርተ ሃይማኖትን፣ነገረ መለኮትን፣ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ካለማወቅ የተነሣ በሰው ሕይወት ላይ የሚደርሰው መንፈሳዊ ድቀትና ኪሣራ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ከባድ ችግር ነው:: ለሰው ልጅ ሕይወተ ነፍሱን በሕገ እግዚአብሔር መርቶ ለጽድቅ መብቃት ካለመቻሉ የከፋ ምን ችግር ሊገጥመው ይችላል? በሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ዙሪያ የሚከሰቱ ረቂቃን ችግሮች ሁሉ መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት ዕውቀት መንፈሳዊን ገንዘብ በማድረግ ነው:: በዚህ ምክንያት ነው ዕውቀት መንፈሳዊ የጎ ደለው ሰው ችግረኛ ነው ሊባል የሚችለው:: በዚህ የተነሣ ሰው ሁሉ ሊጨነቅ የሚገባው ከእግዚአብሔር መንግሥት ሊለየው ስለሚችለው ረቂቅ መንፈሳዊ ችግርና መፍትሔውንም ስለመሻት መሆን አለበት::

በዚህም መሠረት ቀደምት አበው በተለያዩ ጊዜያት ለገጠሟቸው ችግሮች መፍትሔ ለመሻትና ስለተጠደረገላቸው ቸርነትም ለማመስገን ወደ ፈጣሪአቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኸዋል:: ይህም ጩኸት ብዙ ኅብር ያለው ነው:: ልመና፣ብሶት፣ አድናቆት፣ ምስጋና ወዘተ ሊሆን ይችላል:: በግብፅ ባርነት ተገዝተው መከራ የጸናባቸው ቤተ እሥራኤል ነፃ እንዲያወጣቸው ብሶታቸውንና ልመናቸውን ለእግዚአሔር ያቀረቡት ዕንባቸውን በመርጨት ጮኸው ነው:: እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰምቶ ለነቢዩ ሙሴ በእሳት ነበልባል ውስጥ ተገልጦ ከአነጋገረው በኋላ ለእሥራኤል ነፃነት ምክንያት የሆኑ ገቢረ ተአምራትን በእጁ እንደገለጠ–ከግብፅም እንደአወጣቸው ተጽፏል:: ዘጸ.3÷7–10::

የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር ለምፀ ነውር የሆነበት ነቢዩ ኢሳይያስ «ወዮልኝ» በማለት ወደፈጣሪው በመጮኹ አምላኩ መላእክቱን ልኮ በእሳት ጉጠት ከናፍሩን እንዲዳስሱ አድርጎ ነውሩን አስወግዶለታል:– ነውሩ ከተወገደለት፣ በደሉም ከተደመሰሰለት በኋላ ቃሉን ለማወጅ የበቃ ሆኗል:: ኢሳ.6÷1–13::

በፈጣሪአቸው በእግዚአብሔር ፊት በመልካም እየኖሩ ጻድቃን የነበሩት ካህኑ ዘካርያስና ኤልሣቤጥ ልጅ ባለመውለዳቸው ይህ እንደነውርና ኃጢአት ተቆጥሮባቸው በመሰቀቅ የኖሩትን ያህል አምላካቸውን በመለመናቸውና ነውርን ወደሚያስወግደው ወደ እርሱ በመጮኻቸው የችግረኞችን ጩኸትና ልመና ሰምቶ ቸል የማይል እግዚአብሔር የተለመናቸው መሆኑን በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል አማካኝነት ሰምተዋል:: ሉቃ.1÷5–15::

ዓይነ ስውሩ በርጤሜዎስ ወደ ኢያሪኮ በሚወስደው መንገድ ላይ ተቀምጦ ምሕረትን ለመሻት አብዝቶ የጮኸው ወደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር:: ጩኸቱን ያደመጠው መድኃኔዓለም አፍአዊ ውሳጣዊ ብርሃኑን ሰጠው፤ አፈፍ ብሎም እንዲከተለው አደረገው:: ችግረኛው ወደ ፈጣሪው ጮኾ መልስም አገኘ፤ በደስታም ዘለለ:: ማር.10÷46–52::

ክርስቲያኖችን ለማሳደድ በደማስቆ መንገድ ላይ ሲንደረደር የነበረው ሳውል ያልጠበቀውና ሊቋቋመው የማይችለው ከባድ ፈተና በገጠመው ጊዜና እንደነጎድጓድ የሚያዝገመግመውን ድምፀ መለኮት ሰምቶ ተፍገምግሞ ከወደቀበት ሥፍራ ሆኖ «ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?» በማለት የጮኸው ወደ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ነበር:– ጩኸቱን የሰማው ክርስቶስ ሊያደርግ የሚገባውን አስተምሮታል:: የሐዋ.9÷1–18::

ነቢዩ ቅዱስ ዳዊትም በየጊዜው እየጮኸ–ለልመናው መልስ ያልነፈገውን እግዚአብሔርን «ጸሎቴን ያልከለከለኝ፣ ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ እግዚአብሔር ይመስገን» ብሏል:: መዝ.65÷20:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለቸርነቱና የሰው ልጆችን ልመናና ጩኸት ሁሉ እየሰማ በረከቱንና ምሕረቱን ከመስጠት ፈጽሞ የማይሳሳ ቸር ፈጣሪአችንን «ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን» በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ በማመስገን ለምስጋናም መጮኽ እንደሚገባ አስተምሯል:: 2ቆሮ.9÷15::

በዚህ አንፃር ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን አበው ሁሉ የሚቀድመው አዳም የእግዚአብሔር ቸርነት ከአእምሮው ስሌዳ ተፍቃ፣ትእዛዘ እግዚአብሔርን በየዋሕነትና በመጽናት መፈጸም ሞኝነት ሆኖበት፣ሰላማዊት ሕገ እግዚአብሔርም የቀንበር ሸክም ያህል ከብዶው ምክረ ከይሲን ሰምቶና ተከትሎ ያልሆነውንና ሊሆን የማይችለውን ለመሆን ሲሻ ራሱን ወደችግር ጣለ፤–ምስኪን ችግረኛም ሆነ:: ሞት ተፈረደች፣የሥላሴ ልጅነትን አጣ፣ከገነት ተባረረ፣ጸጋው ተገፈፈ፣ራቁቱን ሆነ፣ባለጸጋው እርሱ ድሀ–ምስኪን ችግረኛ ሆነ:–በገነት ያሉትን ጥፍረታት ሁሉ የሚገዛ የነበረው እርሱ የዲያብሎስ



www.eotcmk.org

ግዙተኛ ሆነ፣የሞትም ባሪያ:: ዘፍ. 31÷1-20::

ከፍጥረታት ወገን አዳምን ከዚህ ፍርድና ችግር ሊያድነው የቻለ ማንም አልነበረም:: ነገር ግን እንደ ቤተክርስቲያናችን ትምህርት ከገነት ከተባረረ በኋላ ለሰባት ዓመታት ያለቀሰው የንስሐ ለቅሶ ምክንያት ሆናው ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ የሚፈጸም የመዳን ተስፋ አግኝቷል:: በዚህ ኪዳን መሠረትም አምላክ ምሕረት መሆኑን ተገንዝበው፣ ልዕልናውን ዐውቀውና በእርሱም ታምነው ወደ እርሱ ለቀረቡትና ችግራቸውን ለነገሩት የሚራራና የሚቀበላቸው ልዑል እግዚአብሔር ለአዳም የገባውን ኪዳን አስቦ በቀጠሮው ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው በመሆን የአዳምን መከራ ተቀብሎ የአዳምን የዕዳና የግብርናት ደብዳቤ እንደሰም አቅልጦ እንደጉም አብንኖ በማጥፋት የተወሰደበትን ልጅነት፣ የተነሣውን ጸጋ መልሶ በመስጠት ነፃ አደረገው:: ይህ በወንጌል የተጻፈ ታሪክ ነው:: ይህንን ለማጠየቅ ነው ነቢዩ ዳዊት «ዝንቱ ነዳይ ጸርሐ ወእግዚአብሔር ሰምዖ» በማለት ትንቢት የተናገረው:: መዝ.33÷6::

ዛሬም ቢሆን በዚህች ዓለም የምንኖር ክርስቲያኖች የተለያየ መልክና ገጽታ ካላቸው ችግሮች ጋር የምንጋፈጥ መሆኑ እሙን ነው:: ችግር መጠኑ ቢበዛና ቢያንስ እንጂ የሰው ባልንጀራ መሆኑን ለመካድ አይቻልም:: ይህ ክፉ ባልንጀራ ከእኛ እንዲርቅ መሻታችንም የማይታበል ነው፡ የችግር ቁራኛ ሆኖ መኖር የሚፈልግ ማንም አይኖርምና:: ስለዚህም በመጀመሪያ የችግራችን ምንነት፣ምንጩ ምን እንደሆነ ማወቅ ከእኛ የሚጠበቅ ነው:: ከዚያ በመቀጠል የችግራችን ምንጭ የሚደርቅበት መድኃኒት የሚገኝበትን፡- ባለመድኃኒቱ ማን መሆኑን አድራሻውም የት እንደሆነ ማጥናት ተከታዩ ተግባራችን መሆን ይገባዋል:: ችግሩ ወይም በሽታው ከታወቀ መድኃኒት አይጠፋምና::

ችግራችን የዕውቀት መንፈሳዊ ከሆነ ፣የክርስትና ሕይወታችንን በልማድ የምንመራው ከሆነ፤ ስለሃይማኖታችን፣ስለሥርዓተ ቤተክርስቲያናችን፣ስለኦርቶዶክሳዊው መንፈሳዊ ውርሳችን ያልተረዳንና የማናውቅ ከሆነ፤ ሕገ እግዚአብሔር የሚነቅፈውን፣ ቀኖና ቤተክርስቲያን የማይደግፈውን፣ ክርስተያናዊ፣ኦርቶዶክሳዊ ባሕላችን የማይቀበለውን በግድየለሽነት የምንፈጽመው ከሆነ፣ያንጊዜ ችግር ያለብን መሆኑን ልብ ልንል ይገባል:: መፍትሔ መሻት እንዳለብን እናስተውል:: ያኔም መፍትሔ ወደሚገኝባት ወደ ቤተእግዚአብሔር እንሂድ፣ የችግረኞችን ልመና ወደሚሰማና አማናዊ መፍትሔ ወደሚሰጠው ሐኪም ወደ እግዚአብሔርም እንጩኽ:: ሰምቶ ቸል የማይል እርሱ ለልመናችን መልስ፤ ለችግራችንም መፍትሔ ሊሰጠን የታመነ ነውና:: ችግራችንንም ያስወግድልናል::

ልዩ ልዩ ፈተና በገጠመን ጊዜ፣የተለያዩ ችግሮች በመጡብን ጊዜ፣ ማስተዋልና ጥበብ በጎደለን ጊዜ ንጉሡ ሰሎሞንን፣ትዕግሥት ባጣን ጊዜ ጻድቁ ኢዮብን፣ስስት ባጣቃን ጊዜ የአብርሃምን ልግስና፣ መታዘዝ ባቃተን ጊዜ የይስሐቅን ታዛዥነት፣ሥጋ በፈተነን ጊዜ የዮሴፍን ጽናት፣የሐዋርያትን ገድል፣ ፍቅር ባጣን ጊዜ መድኃኔዓለም በመስቀል ላይ ለሰው የገለጠውን ፍቅር በማሰብ የዚህ ሁሉ ባለቤት የሆነውን አምላካችንን የጎደለንን፣ የተቸገርንበትን ነገር አንተ ሙላልን ብለን ልንለምነው ያስፈልጋል::

የለመንነውን እስክናገኝና ችግራችን እስኪወገድ ድረስ ብቻ ሳይሆን-ልመናችን ተሰምቶ ችግራችን ተወግዶ የምንሻው ከተፈጸመልን በኋላም ደግሞ ለምስጋና ወደ እግዚአብሔር መጮኽ የሚገባን መሆኑ መዘንጋት የለበትም:: ለመለመን የሚከፈተው አንደበታችን፣ለማልቀስ ለመጮህ የሚያንጋጥጠው አንገታችን፣ የሚርገበገበው እጃችንና የሚንበረከከው ጉልበታችን፡- ስለቸርነቱ ስለርኅራኄውና ስለስጦታው ሁሉ እግዚአብሔርን ለማመስገን እንዲሁ መትጋት ይኖርበታል:: ብዙዎቻችን አልቅሰን ችግራችን ከተወገደ በኋላ እግዚአብሔርን ማመስገንን እንዘነጋለን:: «ታሞ የተነሣ እግዜርን ረሳ» እንደተባለው እንዳንሆን ለውዳሴው፣ ተአምራቱን ለመናገር፣ እርሱን ለማመስገን መጮኽ የሚገባ መሆኑን አንዘንጋ::

በጠቅላላው ቅዱስ መጽሐፍ እንደነገረን፣ቀደምት አበውም በምግባር እንዳስተማሩን እኛ የምናውቃቸውን፣ ሰውም እኛም የምናያቸውን፣እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቃቸውን ችግሮቻችንንና ጉድለቶቻችንን፣መንግሥተ እግዚአብሔርን ለመውረስ እንቅፋት የሆኑብንን መሰናክሎች፣ የክርስትና ሕይወታችንን የሚያስነቅፉ ድክመቶቻችንን ሁሉ ይዘን ወደቸሩ አምላካችን ብንቀርብ፡- በልመናም ወደእርሱ ብንጮኽ የሚሰማንና መፍትሔውንም የሚሰጠን መሆኑን በሚገባ ተረድተን በዚህ መንገድ መጓዝ ይኖርብናል:: የችግረኞችን ጩኸት የሚሰማ እግዚአብሔር ልመናችንንና የተቀደሰ የሆነ መሻታችንን ተቀብሎ የሚገባንን ሊያደርግልን የታመነ ነው «ዝንቱ ነዳይ ጸርሐ ወእግዚአብሔር ሰምዖ-ይህ ችግረኛ ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው»ተብሏልና-ስለችግራችን፣ስለኃጢአታችን፣ ስለሕይወታችን፣ ስለቤተክርስቲያናችን፣ ስለሃይማኖታችን፣ ስለሀገራችንና ስለሕዝባችን ሁሉ የምናቀርበውን ጩኸታችንን ተሰሚ፣ ልመናችንን ጉዳይ ፈጻሚ አድርጎ እንዲቀበለን፣ለአበው ቀደምት የተለመነ እግዚአብሔር አምላካችን ለእኛም እንዲለመነን፡-በቅዱሳን በረከት እንዲጠብቀን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን አሜን::

ወይትባረክ እግዚአብሔር

## ማስታወቂያ

### ለአንባብያን በሙሉ

የካቲት /መጋቢት 1992 ዓ.ም በሚል ባለፈው መጋቢት ወር መውጣት የነበረባት መጽሔታችን መጋቢት/ሚያዚያ 1992 ዓ.ም በሚል ለንባብ ቀርባላችኋለች:: በመጀመሪያ ከተያዘላት የጊዜ ገደብ ዘግይታ በመውጣቷ ይቅርታ እየጠየቅን የዘገየችበት ምክንያት ባለፈው ወር የሁለቱም እትሞቻችን የጋራ ልዩ እትም የሆነችውን ሐመረ ጽድቅ መጽሔት በማውጣታችን መሆኑን እየገለጽን በዚህ አጋጣሚ መጽሐታችን የ8ኛ ዓመት የሐዋርያዊ ጉዞዋን መጀመሯን እናሳውቃለን::

# ቃል

*ባለፈው እትም «ቃል» በሚል ርዕስ ባቀረብነው የዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከቤተክርስቲያናችን አዕማደ ምሥጢራት አንዱ የሆነውን የምስጢረ ሥላሴን ትምህርት በመጠኑ ካየን በኋላ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ «ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ:: በመጀመሪያው /በቅድምና/ ቃል ነበረ» ያለበትን ሦስት ምክንያቶች ተመልክተናል:: ለማስታወስም አንደኛ የወልድ ቀዳማዊ መሆን፣ ሁለተኛ በሕልውና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ መሆን እና ሦስተኛም የወልድ /የቃል/ ፈጣሪነት የሚሉት ናቸው:: ዝርዝሩን ከእትሙ ያነቧል:: በዚህ እትማችን ደግሞ «ለምን ቃል አለው?»፣ ለምን«አምላክ፤ወልድ፤የበኩር ልጅ፤እዱ ለአብ፤መዝራዕቱ ለአብ» አላለውም? የሚሉትን እናያለን::*

ዲ.ደጀኔ ሺፈራው

# ለምን «ቃል» አለው?

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በወንጌሉ መጀመሪያ ድኅረ ዓለም በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ስለሆነው አምላክ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳማዊነት ሲጽፍ «አምላክ÷ ወልድ÷ እዱ ለአብ/ /የአብ እጁ/÷ መዝራዕቱ ለአብ /የአብ ክንዱ/ የማኑ ለአብ /የአብ ቀኙ/÷ ጥበቡ ለአብ /የአብ ጥበቡ/÷ ኅሊናሁ ለአብ/» ብሎ ከመ ጻፍ ይልቅ «ቃል» ብሎ የጻፈበት ምክንያት አለው:: ይኸንንም ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን::

1ኛ. ቅዱስ ዮሐንስ «ቃል» ከማለት ይልቅ «አምላክ» በማለት ጽፎ ቢሆን ኖሮ የባሕርይ አምላክነቱን ያላመኑ መናፍቃን ለጊዜውም ቢሆን መከራከሪያ ያገኙ ነበር:: ይኸውም÷ ከዘመኑ አርዮሳውያን እንደሚሰማው «እግዚአብሔርም ሙሴን አለው:- እይ÷ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፤... እኔ ግን አማልክት ናችሁ አልሁ፤» የሚለውን በመጥቀስ:- «ኢየሱስ ክርስቶስ የጸጋ አምላክ እንጂ የባሕርይ አምላክ አይደለም፤» /ሎቱ ስብሐት/ ባሉ ነበር:: ዘጸ.7÷1፣ መዝ.81÷6:: በመጽሐፍ ቅዱስ የጸጋ አማልክት የሚባሉት በጸጋ የከበሩ ቅዱሳን ናቸው:: በዮሐንስ ወንጌል እንደተጻፈው ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ ባነሡ ጊዜ:- «ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ?» ብሎ መለሰላቸው:: አይሁድም:- ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው እንጂ. ብለው መለሱለት:: ኢየሱ ስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው:- «እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፍ ሊሻር አይችልምና፤ እነዚያን የእግዚአ ብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው÷ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን:- ትሳደባለህ ትሉታላችሁን? እኔ የአባቴን ሥራ ባላ ደርግ አትመኑኝ ፤ ባደርገው ግን÷ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ /በሕልውና አንድ እንደሆንን/ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ:: /ይህን ሥራ የባሕርይ አምላክ ቢሠራው እንጂ. ፍጡር አይሠራውም ብላችሁ እመኑ::» ብሏቸዋል:: በዚህም ቅዱሳን የጸጋ አማልክት እንደሚባሉ እርሱ ግን አምላክ ወልደ አምላክ /የባሕርይ አምላክ/ መሆኑን አስረድቷቸዋል::

2ኛ. ቅዱስ ዮሐንስ «ቃል» ከማለት ይልቅ «የአብ የበኩር ልጅ» በማለት ጽፎ ቢሆን ኖሮ አሁንም የክርስቶስ ጠላቶች ነቃፊዎች የመከራከሪያ ነጥብ ባገኙ ነበር:: ከዚህም በመነሳት:- «ይኸስ ምን ያስደን ቃል? እስራኤልስ የእግዚአብሔር የበኩር ልጅ ተብለው የለ፤» በማለት የአብ የባሕርይ ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጸጋ ልጅ /ልጅነትን በጸጋ እንዳገኘ/ አድርገው በቆጠሩት ነበር:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ እስራኤል «እስራኤል የበኩር ልጄ ነው፤» ብሎአልና:: ዘጸ.4-23:: ለዚህም ነው አይሁድ:-«ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት አላ አሐዱ አብ ብነ ውእቱ እግዚአብሔር:: እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም፤ /በሩካቤ ዘበሕግ በሥላሴ ፈቃድና ቸርነት ከተ ወለደው በይስሐቅ ተወልደናል እንጂ. እንደ ሥጋ ፈቃድ ከተወለደው ከእስማኤል አልተወለድንም/፤ አንድ አባት አለን÷ እርሱም እግዚአብሔር ነው፤» ይሉ የነበረው::

ኢየሱስ ክርስቶስ ግን÷ አይሁድን:- «ሶበሰ እግዚአብሔር አቡ ከሙ እምአፍቀርክሙኒ ኪያየ÷ ወቃልየኒ እምአቀብክሙ::» እግዚአብሔር አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር÷ ቃሌንም /ሕጌን ትእዛዜን/ በጠበቃችሁ ነበር:: «እስ መአነ እምኀበ እግዚአብሔር ወጻ እኩ ወመጻእኩ::» እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ /ከአብ አካል ዘእምአካል፣ ባህርይ ዘእምባሕርይ ጥንት በሌለው÷ ዘመን በማይቆጠርለት ልደት ያለ እናት ተወልጄ/ መጥቻለሁና:: «ወአኮ ለልየ ዘመጻእኩ አላ ውእቱ ዘፈነወኒ::» እርሱ የባሕርይ አባቴ አብ እኔን የባሕርይ ልጁን ወልድን ውረድ ተወለድ ብሎ ላከኝ እንጅ ራሴ አልመጣሁምና:: /በእርሱ



www.eotcmk.org

ፈቃድ ከቅድስት ድንግል ማርያም
ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነስቼ
በመወለድ በተዋሕዶ ሰው ሆኜ መ
ጣሁ እንጂ በራሴ ፈቃድ አልመ
ጣሁም፤ በባሕርይ፥ በሕልውና፥ በሥ
ልጣን፥ በመለኮት አንድ ስለሆንን
ከአብ የተለየ ፈቃድ የለኝምና/::
«እፎ እንከ ተአምኑ ቃልየ? እስመ
ኢትክሉ ሰሚአ ነገረ ዚአየ::» በቃ
ሌ /በእኔ/ ማመን እንደምን ይቻ
ላችኋል? ትምህርቴን አትቀበሉኝ
ምና:: «አንትሙሰ እምአቡክሙ ሰ
ይጣን አንትሙ::» እናንተ ከግብር
አባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ:: «ወ
ፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግ
በሩ::» የግብር አባታችሁንም ምኞ
ት ልታደርጉ ትወዳላችሁ «ወውእ
ቱሰ ቀታሌ ነፍስ ሰብእ ውእቱ እም
ትካት::» እርሱ ከጥንት ከመጀመ
ሪያው ነፍሰ ገዳይ ነበረ:: /በቃየል
አድሮ አቤልን ገድሎአል/ «ወኢቀ
ውም በጽድቅ፥ እስመ አልቦ ጽድቅ
በኀቤሁ:: እውነት በእርሱ ስለሌለ
በእውነት አይቆምም:: /በሐሰት
አምላክ ነኝ ብሎአል፥ አዳምንም:-
በሐ ሰት፥ የዕፀ በለስን ፍሬ ብትበላ
አምላክ ትሆናለህ ብሎታል/:: «ወሶ
በሂ ይነብብ ሐሰተ እምዚአሁ ይነ
ብብ::» ሐሰት በተናገረ ጊዜ ከራሱ
አንቅቶ /አመንጭቶ/ ይናገራል::
«እስመ ሐሳዊ ውእቱ ወአቡሃ ለሐ
ሰት::» ሐሰተኛ የሐሰትም አባ ት
ነውና ብሏቸዋል:: ዮሐ.8÷41–44::

ጌታችን አይሁድን እንዲህ
ያላቸው ልጅነታቸውን አጽንተው
እንደ እግዚአብሔር ልጆች ሆነው
ባለመገኘታቸው ነው:: ምክንያቱም
ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን
አያደርግምና ነው:: ለዚህም ነው ሐ
ዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በመልእ
ክቱ:- «ልጆች ሆይ ማንም አያስታ
ችሁ፤ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን
የሚያደርግ ጻድቅ ነው:: ኃጢአትን
የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው ÷ ዲያ
ብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደ
ርጋልና:: ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ
እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ
ተገ ለጠ:: ከእግዚአብሔር የተወለደ
ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም÷ ዘሩ
በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔ
ርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያ
ደርግ አይችልም:: የእግዚአብ ሔር
ልጆችና የዲያ ብሎስ ልጆች በዚህ
የተገለጡ ናቸው፤» ያለው:: 1ኛ
ዮሐ.3÷7–10::

3ኛ. ቅዱስ ዮሐንስ «ቃል» ከማለት
ይልቅ «ወልድ» ብሎ ቢሆን ኖሮ÷ ይ
ህም የአብንና የወልድን አንድነት እንጂ
የሦስቱንም ማለት የአብን የወልድንና
የመንፈስ ቅዱስን አንድነት በግልጥ
አያስረዳልትም ነበር:: «ቃል» ግን የሦስ
ቱንም ማለት የልብን /የአብን/÷ የቃልን
/የወልድን/÷ የእስትንፋስን /የመንፈስ
ቅዱስን/ አንድነት በግልጥ ያስረዳል::
ምክንያቱም ከልብና ከእስትንፋስ ተለ
ይቶ በአፍአ /በውጭ/ ያለ /የሚኖር/
ቃል የለምና:: በመሆኑም ቃል ባለበት
ልብና እስትንፋስ አሉ::

ለምሳሌ እግዚአብሔር:- በመል
ኩና በአርአያው የፈጠረው ሰው የማሰብ
የመናገርና የመተንፈስ ችሎታ አለው::
ይህም የሚያስረዳን አንድ ሰው:- ልብ÷
ቃልና እስትንፋስ እንዳለ ው ነው:: እነዚህ
ም እርስ በርሳቸው ሳይነጣጠሉ አንዱ
ባለበት ቦታ ሁሉ ሌሎችም ይኖራሉ::
በመሆኑም የሰው ልጅ በልቡ ያስባል÷ በ
ቃሉ ይናገራል÷ በእስትንፋሱም ይተነፍ
ሳል፤ /በሕይወት ይኖራል/፤

ልብ:- ቃልን ይወልዳል፤ ይህም
ቃል ከልብ የሚወለደው ከልብ ሳይለይና
ሳይቈረጥ ነው:: ምክንያቱም ሰው ዝም
ብሎም ሆነ በሚናገር ጊዜ ቃሉ ከእርሱ
ጋር ነው– ከልቡ አይለይም ወይም
አይቋረ ጥም:: በዚህም ምሳሌ መሠረት
ወልድ /ቃል/ ከአብ ከልብ/ የተወለደው
በመለኮት÷ በሕልውና÷ በባህርይ ከአብ
ሳይለ ይ እንጂ ከተወለደ በኋላ በመለየት
አይደለም::

ልብና ቃል እስትንፋስ አላቸው፤
ይህም እስትንፋስ ሕይወታቸው ነው:: እን
ደዚሁ ሁሉ አብና ወልድም ሕይወት እስ
ትንፋስ አላቸው፤ እርሱም በባሕርይ÷ በሕ
ልውና÷ በሥልጣን÷ በመለኮት÷ በፈቃድ
ከእርሱ ጋር አንድ የሆነ መንፈስ ቅዱስ
ነው:: በዚህም መሠረት ቃል የሚኖረው
ከልብና ከእስትንፋስ ጋር ነው:: ልብም
የሚኖረው ከቃልና ከእስትንፋስ ጋር
ነው:: እስትንፋስም የሚኖረው ከልብና ከ
ቃል ጋር ነው:: በዚህም የአንዱ መኖር
የሌሎቹንም መኖር በግልጥ እንደ ሚያ
ስረዳ በሚገባ እናረጋግጣለን:: ስለሆነም:-
ሦስቱም በአንድነት ይኖራሉ እንጂ
አንደኛው ከሌላ ኛው ይቀድማል ወይም
ይከተላል÷ ይበልጣል ወይም ያንሳል አይባ
ልም::

4ኛ. ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ
ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳማዊ
ነትና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር
በባሕርይ በሕልውና አንድ መሆ
ኑን ለማስረዳት እዱ ለአብ
/የአብ እጁ/÷ መዝራዕቱ ለአብ
/የአብ ክንዱ/÷ የማኑ ለአብ
/የአብ ቀኙ/ ያላለበትም ምክን
ያት አለው:: ይኸውም:- እነዚህ
ሁሉ የአፍአ /የውጭ/ አንድነትን
እንጂ ውሳጣዊ /የውስጥ/ አንድነ
ነትን ስለማ ያስረዱ ነው::
ለምሳሌ እኛ÷ ልባችን ቃላችንና
እስትንፋሳችን ያለው እውስጣ
ችን ነው፡ እጃችን÷ ክንዳችንና
ቀኛችን ያለው ግን ከውጭ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ "እዱ፣
መዝራዕቱና የማኑ" የሚለው ወል
ድን አካላዊ ቃልን ነው:: ምክንያ
ቱም በእጅ ሥራ እንዲሠራ አብ
ም በልጁ ቃልነት የሚታየ ውንና
የማይታየውን ዓለም ፈጥሯል::
ዘፍ.1÷1–25፣ መዝ.32÷6፣ ዕብ.
11÷3:: በተለይም «እግዚአብ
ሔር አምላክ ሰውን ከምድር አፈ
ር አበጀው» የሚለው ቃል ነገራች
ንን ግልጥ ያደርገዋል:: ዘፍ.2÷7::
ምክንያቱም አዳምን የሠራ ያ
እጅ ወልድ ነውና:: ለዚህም ነው
ነቢዩ እግዚአብሔር ዳዊት «እጆ
ችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም፤» ያለው::
መዝ.118÷73:: እንዲሁም በክንድ
ኃይል እንዲገለጥ የአብም ኃይሉ
በወልድ ተገልጧል:: 1ኛ ቆሮ.
1÷18:: ከዚህም ጋር ወልድ የአብ
ቀኙ የተባለው በሥልጣን ከእርሱ
ጋር እኩል በመሆኑ ነው:: ይኸንን
የሚመለከቱ የመጽሐፍ ቅዱስ
ክፍሎችንም ከዚህ እንደሚከተለ
ው እናያለን::

ሀ. በግብፅ የባርነት ቤት በእስራ
ኤል ዘሥጋ መከራ በጸናባቸው
ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን:-
«በጸናች እጅ ይለቅቃችኋልና÷
በጸናችም እጅ ከምድሩ
አስወጥቶ ይሰዳቸዋልና÷ አሁን
በፈርዖን የማደርገውን ታያለህ ::
ስለዚህም ለእስራኤል እንዲህ
በላቸው:- እኔ እግዚአብሔር ነኝ
÷ ከግብፃውያንም ባርነት አወ
ጣችኋለሁ÷ከተገዥነታችሁም



www.eotcmk.org

አድናችኋለሁ፤ በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም አድናችኋለ ሁ» ብሎታል:: ዘጸ.6÷1፣6፤ እ ዚ.ህ ላይ እጅና ክንድ የተባለው ወልድ ነው::

እግዚ.አብሔር ጥንት እስ ራኤል ዘሥጋን በጸናች እጅና በተ ዘረጋች ክንድ ከግብፅ የባርነት ቤት አውጥቶ ባሕረ ኤርትራንም በደረቅ አሻግሮ ምድረ ርስት ከነዓንን እንዳ ወረሳቸው ሁሉ በኋለኛውም ዘመን በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ÷ ተጨ ምሮ ተፈርዶባቸው በሲ.ኦል ይማቅቁ የነበሩትን ነፍሳት በጸናች እጁና በተዘ ረጋች ክንዱ /በልጁ በኢየሱስ ክር ስቶስ ቤዛነት/ አድኗቸዋል÷ ከሲ.ኦ ልም አውጥቶ ጥንተ ርስታቸውን ገነ ትን አውርሷቸዋል:: እዚ.ህ ላይ የእስ ራኤል ዘሥጋ ከግብጽ መውጣት የነፍሳት ከሲ.ኦል መውጣት ምሳሌ ነው::

ለ ነቢ.ዩ ኤል.ያስ በጸሎቱ ኃይል ከሦስት ዓመት ከመንፈቅ በኋላ ለመጀመሪያ ጊ.ዜ ደመና በመታ የቱ:- «ዝናብ እንዳይከለክልህ ሰረ ገላህን ጭነህ ውረድ፤ ብሎ ለንጉሡ ለአክዓብ ላከበት:: ከጥ ቂ.ትም ጊ.ዜ በኋላ ሰማዩ ከደመናው ከነፋሱ የተነሳ ጨለመ÷ ብዙም ዝናብ ሆነ፤ አክዓብም በሰረገላው ተቀምጦ ወደ ኢ.ይዝራኤል ሄደ:: የእግዚ.አብሔ ርም እጅ በኤል.ያስ ላይ ነበረች:: ወገቡንም አሸንፍጦ ወደ ኢ.ይዝ ራኤል እስኪ.ገባ ድረስ በአክዓብ ፊት ይሮጥ ነበር::» 1ኛ ነገ. 18÷20–46::

ለነቢ.ዩ ለኤል.ያስ ይቃወ ሙት የነበሩትን የጣዖት አገል.ጋዮች ያሳፈረለትና የንጉሡን ሰረገላ ቀድሞ የሚሮጥበትን ኃይል የሰጠ ው በላዩ ላይ የነበረ የእግዚ.አብሔር እጅ ነው:: በኋላም ጠላቶቻችን አጋንንትን ያሳፈረልንና ዳግመኛም ድል እንዳንሆን /በአጋንንት እንዳ ንረ.ታና እንዳንቀደም/ ኃይል መንፈ.ሳዊን ያስ.ታጠቀን የእግዚ. አብሔር እጅ ኢ.የሱስ ክርስቶስ ነው::

ሐ. ነቢ.የ እግዚ.አብሔር ዳዊት «ፈኑ እዴከ እምአርያም÷ አድኅነኒ. ወባልሐኒ. እማይ ብዙኅ:: እጅህን ከአርያም ላክ÷ ከብዙ ውኆችም አድነኝ፤» ሲል ዘምሯል:: መዝ 143÷7:: የዚ.ህም ምሥጢ.ር:- እ ጅህን /ልጅህን/ ከጽርሐ አርያም ውረድ ከድንግል ማርያምም ተወ ለድ ብለህ ልከህ ከፍትወታት እኩያት ከክፉዎች የሥጋ ፍላጎቶ ች/÷ ከኃጢ.አት÷ ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ÷ ከፍዳ÷ ከ መከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ አድ ነኝ ማለት ነው:: «ቀን ሲ.ደርስ አምባ ይፈ ርስ፤» እንዲ.ሉ የተነገረው ትንቢ.ት የተቆጠረው ሱባዔ ሲ.ደርስ በዕለቱ በሰዓቱ እጁን ማለትም ተቀዳሚና ተከ.ታይ የሌለውን አንድ የባሕርይ ልጁን በሥጋ ማርያም ላከ:: እር ሱም በመንፈ.ስ ቅዱስ ግብር የዕ ለት ፅንስ ሆኖ በማኅፀነ ድን ግል ማርያም የጀመረውን የማዳን ሥራ በቀራንዮ አደባባይ በመልዕ ል.ተ መስቀል ፈጸመው:: በዚ.ህም ከመጠ ርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ከፍዳ ከኩነኔ ፈጽሞ አዳነን::

መ «የእግዚ.አብሔር ክንድ ሆይ÷ ተነሥ÷ ተነሥ÷ ኃይልንም ልበስ፤ በቀድሞው ወራት በጥንቱ ዘመ ን በነበረው ትውልድ እንደ ሆነው ተነሥ» ኢ.ሳ.51÷2:: ነቢ.የ እግዚ.አ ብሔር ኢ.ሳይያስ ይህን የትንቢ.ት ቃል የተናገረው ስለ ወልድ ስለ አካላዊ ቃል ነው:: ምክንያቱም መዝራዕቱ ለአብ /የአብ ክንዱ/ የሚ ባል እርሱ ነውና:: የትንቢ.ቱም ምሥጢ.ር:- የእግዚ.አብሔር ክንድ ሆይ÷ ከጥንት ጀምሮ ለአባቶቻችን በረድኤት እየተገለጥክ ኃይልህንም እያሳየህ ከጠላቶቻቸው ከአሕዛብ እጅ እንዳዳ ንካቸው አሁን ደግሞ በሥጋ ማርያም ተገልጠህ ከዲ.ያብሎስ ግዛት ከሲ.ኦል ባርነት እኛን ለማዳን ና ማለት ነው:: እንደ ተባለውም የእግዚ.አብሔር ክንድ የተባለ ወልድ አካላዊ ቃል በሥጋ ተገልጦ ዓለምን አድኗል::

ሠ «እነሆ የእግዚ.አብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም÷ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፤ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላ ካችሁ መካከል ለይ.ታለች÷ እንዳይ ሰማም ኃጢ.አ.ታችሁ ፊቱን /ገጸ ምሕረቱን/ ከእናንተ ሰውሮ.ታል::» ኢ.ሳ.59÷1–2:: ይህ ቃለ ትንቢ.ት የተነገረው ለጊ.ዜው ለእሥራኤል ዘሥጋ ሲ.ሆን ፍጻሜው ግን ለእስ ራኤል ዘነፍስ ነው::

ረ «የሰማነውን ነገር ማን አምኗል? የእግዚ.አብሔር ክንድ ለማን ተገል ጧ.ል?» ኢ.ሳ.53÷1:: የዚ.ህም ምሥ ጢ.ር:- የእግዚ.አብሔር ክንድ ማለ ትም የኢ.የሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት÷ ፈጣሪነት÷ ከአብ ከመጠ ንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮት፣ በሥል ጣን፣ በባሕርይ በፈ.ቃድ አንድ መሆኑ ለማን ተገልጧ.ል? ማለት ነው::

ነቢ.ዩ ኢ.ሳይያስ እንደተናገረው ለብዙዎች የእግዚ.አብሔር ክንድ /የኢ. የሱስ ክርስቶስ የባህርይ አ ምላክነት/ አልተገለጠላቸውም ነበር:: በፊ.ታቸው ብዙ ተአምራት አድርጐ ቢ.ያሳያቸ ውም አላመኑበትም:: ለዚ.ህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ:- «ነገር ግን ይህን ያህል ምልክት በፊ.ታ ቸው ምንም ቢ.ያደርግ፤ ነቢ.ዩ ኢ.ሳይ ያስ:- ጌ.ታ ሆይ÷ ማን ምስክርነ.ታ ችንን አመነ? የእግዚ.አብሔር ክንድ ለማን ተገለጠ? ብሎ የተናገረው ቃል ይፈ. ጸም ዘንድ በእርሱ አላመኑም፤» ሲ.ል በወንጌሉ የጻፈ:: ዮሐ.12÷37–39::

ሰ.«ጌ.ታ እግዚ.አብሔር እንዲ.ህ ይላል:: እነሆ እጄን ወደ አሕዛብ አነሣለሁ:: ዓላማዬንም ወደ ወገኖቼ አቆማለሁ::»

እግዚ.አብሔር ይህን ቃለ ትን ቢ.ት በኢ.ሳይያስ አንደበት በቀ ጥ.ታ ተናግሮ.ታል:: ምሥጢ.ሩም:- እጁን /ልጁን/ ለድኅነተ ምእመናን ወደ ዓለም እንደሚልክ የሚያመ ለክት ነው:: ዓላማ የተባለውም በቀራንዮ የሚተከለው ዕፀ መስቀል ነው:: ይኸ ንንም የምናረጋግጠው እግዚ.አ ብሔ ር ሙሴን:- «እባብን ሠርተህ በዓላማ /በመስቀል/ ላይ ስቀል፤ የተነደፈ ው ም ሁሉ ሲ.ያዩት በሕይወት ይኖ ራሉ፤» በማለቱ ነው:: ዘኍ. 21÷8:: ጌ.ታም በወንጌል:- «ሙሴም በምድ ረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲ.ሁ በእርሱ የሚ.ያምን የዘለዓለም ሕይ ወት እንዲ.ኖረው እንጂ. እንዳይ ጠፋ የሰው ልጅ /የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ/ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል፤» እንግዲ.ህ እስራኤል ዘሥጋ የተ ሰቀለውን የናስ እባብ በማየት በእም ነት ከደዌ ሥጋ እንደዳኑ ሁሉ በቀደ መው እባብ በሰይጣን በኃጢ.አት ተ መርዘው የነበሩ ነፍሳት ደግሞ በስ ቅለተ ክርስቶስ ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ ድነዋል::

የተወደዳችሁ አንባብያን:- «አምላክ÷ ወልድ፣ የበኩር ልጁ÷ እዱ ለአብ÷ መዝራዕቱ ለአብ» የሚለውን ይኸንን ያህል ከተነጋገርን በሚቀጥ ለው እትማችን ደግሞ «የማኑ ለአብ÷ ጥበቡ ለአብ÷ ኀሊናሁ ለአብ የሚለ ውን በዝርዝር እንመለከ.ታለን:: ለሁ ሉም የእግዚ.አብሔር ቸርነት የድጠ ንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን::

/ይቀጥላል::/





www.eotcmk.org

# በጎቹን ጠብቅ

*ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ አባል ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት ቤተክርስቲያናችን አሏት ከሚባሉ የሥርዓተ ቤተክርስቲያን መምህራን አንዱ ናቸው። ሊቀ ካህናት እንደዚሁ በጽሑፍ ከሚሰጡን ውጭ ለእኛ የከበዱንን ጥያቄዎች እንዲያብራሩልን ስንጠይቃቸው በታዛዥነት ይመልሱልናል፤ በምክራቸውም ያበረታቱናል። ለዚህም ዝግጅት ክፍላችን በአንባብያን ስም ለአባታችን ምስጋናውን እየገለጠ በዚህ እትም በጽሑፍ የሰጡንን ትምህርት እናቀርባለን። ሊቀ ካህናት ከዚህ ጽሑፋቸው የክህነት ሥልጣንና ኃላፊነቱ፣የካህናትና የንስሐ ልጅ ግንኙነት ምን መምሰል እንደሚገባው በአጠቃላይ ስለ «እረኝነት» አገልግሎት ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተዋል። መልካም ንባብ።*

በጎች እነማን ናቸው? በብሉይ ኪዳን በጎች እሥራኤል ዘሥጋ ነበሩ። እረኞችስ እነማን ናቸው? እረኞችም ካህናትና ነገሥታት ነበሩ። ይሁን እንጂ በዘመኑ የነበሩት እረኞች ለበጎቻቸው የማያዝኑና የማይራሩ ራስ ወዳዶችም ስለ ነበሩ የክፉዎችን እረኞች እንደ ክፋታቸው፣ የመልካሞቹን እረኞች እንደ መልካምነታቸውና እንደ ደግነታቸው ጠቅላላ እንደ ሥራቸው ነቢያት ትንቢት ተናግረውባቸዋል። ከእነዚህ ነቢያት መካከል ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ ክፉ እረኞች የሚከተለውን ትንቢት ተናግሮባቸዋል። «ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእሥራኤል እረኞች ወዮላቸው፣ እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ፣ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ የወፈሩትንም ታርዳላችሁ፣ በጎቹን አታሰማሩም፤ የደከመውን አላጸናችሁም፣የታመመውን አላከማችሁትም፣የታሰረውንም አልጠገናችሁትም፣ የባዘነውንም አልመለሳችሁትም፣ የጠፋውንም አልፈለጋችሁ ትም፣ በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው እረኛም በማጣት ተበተኑ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ» ብሏል። ሕዝ .34÷2/።

ነቢዩ ዘካርያስም በዚያ ዘመን ለነበሩት ሰነፍ እረኞች የሚከተለውን ትንቢት ተናግሮባቸዋል። «ከሕዝቦች ሁሉ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን አፈርስ ዘንድ ውበት የተባለችውን በትሬን ወስጄ ቆረጥኩ፤ በዚያም ቀን ተሰበረች፤ እኔን የተመለከቱ የመንጋው ችግረኞች የእግዚአብሔር ቃል እንደ ነበር ዐወቁ። በይሁዳና በእሥራኤል መካከል ያለውንም ወንድማማችነት እሰብር ዘንድ ማሠሪያ የተባለችውን ሁለተኛይቱን በትሬን ቆረጥሁ፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር የሰነፍን እረኛ ዕቃ ውሰድ አለኝ፤ የወደቀውን የማይረዳ የተበተነውንም የማይሰበስብ፣ የቆሰለውን የማያድን፣የጸነውንም የማያቀና፣የሰባውን ግን የሚበላ፣ ቅልጥሙንም የሚመኝ እነሆ በዚህ አለ፤ ሰነፍና ያለዐዋቂ የሆነ እረኛ አስነሣለሁ፤ መንጋውን ለሚተው እረኛ ወዮለት ሰነፍ በክንዱና በቀኝ ዐይኑ ላይ ይሆናል፣ ክንዱም አጥብቃ ትደርቃለች፤ ቀኝ ዓይኑም ፈጽማ ትጨ ልማለች» ይላል። ዘካ.1 1÷17።

እንደ ሕዝቅኤል ትንቢት ካህ ናቱ በየሰፈሩ፣በመንደሩ፣በየገጠሩ እየዞሩ በምግባር በእምነት የደከመውን አያድኑም በኃጢአት ወድቆ የተሰበረውንም በንስሐ በትምህርት አክመው አይፈውሱትም፤ ከእግዚአብሔር ሸሽቶ ከጽድቅ ርቆ የጠፋውን ኃጢአተኛ በትምህርት ፈልገው ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ አያደርጉትም፤ አሥራቱን በኩራቱን ተቀብለው ይመገባሉ በትምህርት ግን ሕዝቡን አይጐበኙትም በየቤቱም እየዞሩ ሳያስተምሩ ሀብታሞ ችንና ድሆችን ብቻ ሳይሆን ፣ጠም አዳሪዎችን መበለት ሳይቀር የጾም ቆሎ የበዓል ዶሮ እያሉ ገንዘብ ለመቀበል ይሽቀዳደሙ ነበር። ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንና ሕግ ያለውን ዋና ነገር ሁሉ ባለማክበራቸው ክፉዎች እረኞች መሆናቸውን ያሳያል።

እንደ ዘካርያስ ትንቢት ችግረኞች ንዑሳን ካህናት ሲሆኑ መንጎች ደግሞ ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉት እሥራኤል ዘሥጋ ናቸው። ዕቃ የተባለው የዘላኖች ገንዘብ ነው። ዘላኖችም የተባሉት እህል ውኃ ይገኝበታል ወደ ተባለው ቦታ የትም የሚዞሩና የሚያስተምሩ ሰነፎች መምህራን ናቸው። ሥራ የማይሠራበት ሥልጣንና ዕድገት የማይታይበት ሹመት ተብሎ ሊተረጐም አይችልም። ሰነፍ እረኛም የተባለው ላይሠራበት፣ ላያስተምርበት በቀኝ እጁ የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍ በግራ እጁ መቋሚያ የሚይዘው ነው። ክንዱ አጥብቃ ትደርቃለች ያለው ነገር ካልሆነ በቀር መልካም ነገር መሥራት ደስ አይለውም ማለት ነው። ዓይኑ ይጨልማል ያለው ደግሞ መልካም ነገር ማየትን ይጠላል ማለት ነው፡ ይህም የተነገረው ትንቢት በእሥራኤል መምህራን ላይ ተፈጽሟል። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በጎች እሥራኤል ዘነፍስ የተባሉ ምእመናን ክርስቶስ ሲሆኑ እረኞች የሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ወራሾች የሆኑት በራሱ በባለቤቱ የተሾሙትና ሥልጣንን የተቀበሉት ሐዋርያት ፣ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው። በአጠቃላይ አነጋገር ካህናተ ክርስቶስ ናቸው። ዮሐ .21÷15-17።

ሐዋርያት በሥልጣናቸው ያሥ ሩ ይፈቱ ነበር /ማቴ.18÷18፣ 1ኛ ቆሮ 4÷12፣ 2ቆሮ.5÷20፣ ማቴ. 16÷18፣ ማቴ.20÷23/ የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑት ኤጲስ ቆጶሳትና ቀሳውስትም ያሥራሉ ይፈታሉ።

የሚያሥሩት ኃጢአተኛውን፣ መናፍቁን ከሀዲውን ሲሆን የሚፈቱት ደግሞ ተነሣሒውን አማኒውን ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትውፊት ማንኛውም ምእመን ከአጥቢያ ቀሳውስት ውስጥ መምህረ ንስሐ መርጦ ይይዛል። ይህም የነፍስ አባት ይባላል። ቄስ ለምእመናን የነፍስ አባት፣የንስሐ አባት፣መምህረ ንስሐ ይባላል። ምእመኑም ለቄሱ የነፍስ ልጅ የንስሐ ልጅ ይባላል። ቄሱ በመከራም ሆነ በደስታ ጊዜ ከነፍስ ልጆቹ አይለይም። እነሱም የጠም ቆሎ፣ የበዓል ዶሮ፣የሻሽ ይሉታል። የነፍስ ልጆች ምእመናን ጥፋታቸውን የሚናዘዙት በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት በግል በምሥጢር ነው። የቄሱና የምእመናኑ ግንኙነት ይህ ሆኖ ሳለ አሁን ግን ከትምህርት ማነስ የተነሣ አንዳንድ ምእመናን ሲወልዱ ለማስጠመቅ፣ሲሞቱ ለፍታት ካልሆነ በቀር ኃጢአትን በየጊዜው ለመናዘዝና ሥርየተ ኃጢአትን ለማግኘት ወደ ቄሱ የሚሄድ የለም።

መስቀል ተሳልሞ ይፍቱኝ የሚል ሞልቷል፣ታዲያ ምእመኑ ከኃጢአት ማሠሪያ የሚፈታው ኃጢአቱን ተናግሮ ቄሱ በቤተክርስቲያን ስም የሚሰጠውን ቀኖና ሲፈጽም እንጂ መስቀል ተሳልሞ ይፍቱኝ በማለት ብቻ ኃጢአት አይወርድም። በርግጥ የሐልዮን ኃጢአት ሊያስተሠርይ ይችላል። ለነቢቡና ለገቢሩ ኃጢአት ግን ቀኖና ያስፈልገዋል።

ይህም የንስሐና የኑዛዜ ሥርዓት ሊሠራ የቻለው ቀሳውስት የንስሐ ልጆቻቸውን በሚገባ ባለማስተማራቸውና በትምህርተ ኖሎት ባለመጠበቃቸው ሲሆን ምእመናንም ካህኑ እረኛቸው መሆኑን ዐውቀው ድምፁን ሰምተው ባለመከተላቸው ማለት ለካህኑ ባለመታዘዛቸውና የሌላው ታዛገሮች በመሆናቸው መሆኑ ግልጥ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በጎቹ ድምፁን ይሰሙታል፤ በጎቹንም በየስማቸው እየጠራ ያሰማራቸዋል፣ በጎ ቹንም በአሰማራቸው ጊዜ በፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ይከተሉታል። ድምፁን ያውቃሉና ሌላውን ግን ይሸሹታል እንጂ አይከተሉትም፤ የሌላውን ድምጽ አያውቁምና» ነበር ያለው። ነገር ግን ዛሬ በጎቹን የሚያውቅ



www.eotcmk.org

በጐቹ የሚያውቁት እረኛ እየታጣ ነው:: ዮሐ.10:3-5

አንድ እረኛ በሚገባ ሊከታተላቸው፥ ሊያሰማራቸው፥ ሊፈቅዳቸው የሚችላቸውን በጐች ወይም ፍየሎች ሊይዝ ይገባል:: ያ ሳይሆን ቀርቶ ግን ከአቅሙ በላይ የሆኑ በጐች ቢይዝ ለተኩላና ለሌሎች አውሬዎች ይጋለጣሉ:: እንደ ዚሁም ሁሉ አንድ ካህን ሥራው እረኝነት ነውና ሊቆጣጠራቸውና ሊያስተምራቸው የሚችላቸውን ልጆች ብቻ ወስኖ ሊይዝ ይገባዋል:: ዛሬ ዛሬ እንደምናየው ግን ካህኑ ምእመናን እንወድሃለን ስላሉት ወይም ከአንተ ሌላ የለም ስላሉት ብቻ ከሚችለው በላይ የበዙ ነፍሳት እረኝነት ኃላፊነት ላይ ሲወድቅ ይታያል:: በእውነቱ ይህ የማይገባ በቤተ ክርስቲያኗ የሥርዓት መጽሐፍም ያልተጻፈ ነው:: በመሆኑም ይህንን የተሣሣተ ሂደት በማስቆም በኩል ካህናትም ሆኑ ምእመናን በንቃት ሊሳተፉ ይገባል::

እረኛ በጐቹን ከአውሬ የሚጠብቅበት ልዩ ልዩ መሣሪያ መያዝ እንዳለበት ሁሉ አንድ ካህንም የምእመናን ልጆቹን ነፍሳት የሚጠብቅበት መሣሪያ ሊኖረው ይገባል:: ይህም በፍትሐ መንፈሳዊ ምዕራፍ 6 እንደተጻፈ አንድ ካህን የአም ላካውያት መጻሕፍት /የብሉያትና የሐዲሳት/ ዕውቀት ሊኖረው ያስፈልጋል:: በመጽሐፍ እንደተደነገገው በልጆቹ ለሚመጡባቸው መናፍቃን እንዲሁም ከራሳቸው ለሚመጡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚያስችል ዕውቀት የሌለው ካህን ወደ መቅደስ ገብቶ መቀደስ አይችልም:: ስለዚህ ካህን ብሉያትን ከሐዲሳት አደላድሎ ያወቀ መሆን አለበት::

ነገር ግን የአሁኑ ካህን ድምፁን ሰምተው ምእመናን እንዲከተሉት ድምፁን የሚያሰማ የለም አያስተምርም፣ አይመክርም ተደብቆ ነው የሚኖር:: የበጐቹን ምእመናን ስም እየጠራ ለመምራት ስማቸውን መዝግቦ አልያዘም:: ሊቆጣጠራቸው ሊመግባቸውም ሊጠብቃቸውም እያቃተው ነው:: ከዚህም የተነሣ በጎች አልተከተሉትም:: በጎችም የእረኛውን ድምፅ እየሰሙ ባለመከተላቸው እየባዘኑና በአራዊት እየተበሉ ነው:: ከእረኛው የተለየ በግ በአውሬ ከመበላት በስተቀር ሌላ ዕድል የለውምና:: ሰነፍ እረኛም በጎቹን አውሬ ከማስበላት በቀር ሌላ ፋይዳ የለውምና::

ካህኑ የንስሐ ልጆቹንም ሆነ ጠቅላላ ምእመናንን በትምህርተ ወንጌል መጠበቅ በአራዊት ከተመሰሉት መናፍቃን ማዳን አለበት:: ሕፃንም ሆነ አዋቂ የተማረም ሆነ ያልተማረ ፣ድሀም ሆነ ሀብታም በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ከተወለዱ በኋላ ሁሉም እኩል ስለሆኑ ወንጌልን የሚያስተምር ካህን ለእነዚህ ሁሉ የሚገባቸውን ትምህርት እያዘጋጀ ማቅረብ አለበት::

በሀገራችን ሕፃናት የሃይማኖት ትምህርት አያስፈልጋቸው ይመስል ካህናትም ሆኑ ወላጆች እንደ ትርፍ ነገር ይቆጥሩዋቸዋል:: አንዳንድ ወላጆች ካልሆኑ በቀር ብዙዎች ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ቤተርስቲያን እንሂድ ብለው በሚነሡበት ጊዜ እንኳ ደግሞ የልጅ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ምን ሊያደርግ ነው? እያሉ ይከለክሏቸዋል:: ይልቁንስ እንዳ ይበርዳችሁ ከአልጋችሁ እንዳትነሡ ብርድ ልብስ ለብሳችሁ ተኙ ይሉዋቸዋል:: ካህናትም ወላጆች ይህን አስተሳሰባቸውን እንዲለውጡ በመምከርና በማስተማር ፊንታ ሕፃናት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ እንደቁም ነገር አድርገው አይቆጥሩዋቸውም::

ይህም የካህናትና የወላጆችን የዕውቀት ጉድለኑት የሚያመለክት ነው:: የእነዚህ ልጆች ናቸው እንግዲህ የመናፍቃን መስጊድና ቤተ ጸሎት አሚማቂዎችና አዳማቂዎች የሆኑት::

አንዳንድ ወላጆች ግን ካህናት ትም ሆኑ ምእመናን ልጆቻቸው ቡራኬ እንዲያገኙላቸው ጠዋት ከዕንቅልፋቸው እየቀሰቀሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወስዷቸዋል:: በወንጌል ሕፃናትን ለማስባረክ ወደ ጌታ ሲያቀርቡዋቸው ሕፃናትን ከቁም ነገር ባለ መቁጠራቸው ሐዋርያት ተቃውመው ነበር:: ነገር ግን ጌታ ወደርሱ እንዲቀርቡና እንዲባርካቸው ከመፍቀድ በላይ መንግሥተ ሰማያት እንደእነሱ ላሉ የምትሰጥ መሆኑዋን በዚያ ለነበሩት ሁሉ አስተማረ:: ዮሐ.19÷13 አሁንም ካህናት የሕጻናትን ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት እንደቀላል ነገር ሊቆጥሩት አይገባም:: ይልቁንም ወላጆች ልጆቻቸውን ጥለው ወደ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ወደ ክርስቲያኖች ጉባኤ ቤት እንዳይመጡ አጥብቀው መስበክ አለባቸው:: ሕጻናት በልጅነት ወራት ሃይማኖታቸውንና ታሪካቸውን ያጠኑት እንደሆነ ለሀገራቸው ለቤተ ክርስቲያ ናቸው ምርጥ ዕቃ ይሆናሉ::

ወደ ብሉይ ኪዳን ታሪክ ብንመለከት ነቢያት ሃይማኖታቸውንና ታሪካቸውን የሚማሩት በሕጻንነት ነበር::

ለምሳሌ እነ ዳንኤል፣እነ ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ ተማርከው በሄዱበት በባቢሎን አገር የንጉሡን የናቡከደነፆርን ግርማ ሳይፈሩ አምላካችን ያድነናል ብለው ወደ እሳት ለመወርወርና ከእሳቱም በአምላካቸው ረድኤት ድነው የሃይማኖታቸውን ኃይል ለገዢዎች ያሳዩት አምላካቸውንም ያስመሰገኑት በልጅነታቸው ሃይማኖታቸውን ስለተማሩ ነው:: /ዳን.ም 3/

በአዲስ ኪዳንም የክርስቲያን ልጆች በሕጻንነታቸው ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚሰጠውን ትምህርትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እየተከታተሉ በማደጋቸው ለክርስትና ትምህርት ምስክሮች እየሆኑ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያደረጉ አነስተኛ ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም::

ስለዚህ የንስሐ አባቶች በቤትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን በሚሰጡት ክርስቲያናዊ ትምህርት ልጆችን ከወላጆች መለየት የለባቸውም:: ለቅዱስ ጴጥሮስ የተሰጠው አደራ አውራ በጎችን እንዲጠብቅ ብቻ ሳይሆን ጠቦቶቹንና ግልገሎችንም እንዲጠብቅ ነው::

በመጨረሻም የንስሐ ልጅ ከንስሐ አባቱ የሚሰናበትባቸውን ምክንያቶች በመጠኑ እንመልከት ዮሐ.21÷15-1::

በተለያዩ ምክንያቶች አንድ የንስሐ ልጅ ከአባቱ ሊሰናበት ይቻላል:: ሲሰናበትም የነረበት አባት ወዶ ፈቅዶ ማሰናበቱን፣የሚሄድበት አባትም በሰላም ተቀብሎ እረኛው እንዲሆን የሚያትት ደብዳቤ ካልተጻፈለት እንደተሰናበተ አይቆጠርም:: በእርግጥ እንደዚያ ማድረግ የማያስችሉ ምክንያቶች በንስሐ አባቱ በኩል ከደረሰ /ለምሳሌ ድንገተኛ ሞት/ ተነሣሒው የመረጠውን አባት ሊይዝ ይችላል::

አንድ ተነሣሒ አባቱን ለቆ ለመሄድ የሚጨበጡ ምክንያቶች ሊኖሩት ያስፈልጋል:: በፍትሕ መንፈሳዊ ከተገለጡት ውስጥ ሁለቱን እንደሚከተለው እናያለን

ሀ. ተነሳሒው አገር ለቆ የሚሄድ ከሆነ ነፍስ በቅርብ እየተከታተለ የሚጠብቃትና የሚያስማራት እረኛ ያስፈልጋታል:: እንዲያውም ክርስቲያን ሄዶ ባደረበት አገር ሁሉ በአካባቢው ወዳለ አንድ ካህን ቀርቦ ራሱን አስመርምሮ ማደር እንዳለበት ሊቃውንት ያስተምራሉ:: ስለዚህ አንድ የንስሐ ልጅ በሥራ ወይም በሌላ አጋጣሚ አገር ለቆ የሚሄድ ቢሆን በሚኖርበት አገር ሌላ የቅርብ ንስሐ አባት ለመያዝ ከቀድሞው የንስሐ አባቱ ሊሰናበት ይገባዋል:: የንስሐ አባትም እንደዚሁ አገር ቢለቅ ይዞአቸው የነበሩት ልጆቹን በሙሉ ቢችል ለሌላው አባት አስረክቦ ካልቻለ ደግሞ ልጆቹን ሁኔታውን ነግሮ ሌላ እንዲይዙ መክሮ ሊያሰናብታቸው ይገባል::

ለ. ካህኑ የማያስተምረው ሲሆን ክህነት ነፍሳትን የመጠበቅ ኃላፊነት እንደመሆኑና ይህንን ሥልጣን የሰጠው «ትጉህ ኖላዊ ዘኢይነውም» አምላክ እንደመሆኑ ካህኑ የልጆቹን መንፈሳዊ ሀብት በትጋት የሚጠብቅ መሆን አለበት:: ልጁን በተለያዩ መንገዶች ወደእሱ እያቀረበ፣ካለበትም /ቤቱ/ ድረስ እየሄደ ሊያስተምረው፣ ሊመክረው ይገባል:: ነገር ግን ያ ሳይሆን ቀርቶ ልጁን የማያስተምረው፣የማይመክረው፣ቤቱን የማይባርክለት ከሆነ ሊሰናበት ይችላል:: ሰነፍ እረኛ በጎቹን ቀበሮ ያስበላልና::

ስለመሰናበት ስናነሣ ብዙ ጊዜ ሊከሰት የሚችልን አንድ ነገር ማንሣት ይገባል:: አንድ የንስሐ ልጅ ከላይ በተጠቀሱት ወይም ሌላ አሳማኝ ምክንያት በማንሣት የንስሐ አባቱን ሄዶ አሰናብተኝ ሲለው እንቢ ሊለው ይችላል:: በዚህ ጊዜ ልጁ አባቱን ለደብሩ አለቃ ይከሰዋል:: የደብሩ አለቃም ባለው ሥልጣን ተጠቅሞ እንዲለቀው ይነግረዋል:: ይህ ሆኖም ካህኑ እንቢ ካለ በጉባኤ /በደብሩ አለቃና የሰበካ ጉባኤ አባላት / ይወሰንበታል:: ያንን ውሳኔ የመቀበል ግዴታ ስላለበት ካህኑ የማሰናበቻ ደብዳቤውን ይጽፋል::

## ማጠቃለያ

የንስሐ አባትና ልጅ ግንኙነት ይህንን የሚመስል ገጽታ አለው:: ስለሆነም የንስሐ አባቶች የተጣለባቸውን ከባድ ኃላፊነት በመገንዘብ በእነርሱ በኩል ሊሟሉ የሚገባቸውን አሟልተው መገኘት ይጠበቅባቸዋል:: የንስሐ ልጆችም ለንስሐ አባቶቻቸው አንዳንድ መጻሕፍትን በመግዛት እያነበቡ ኃላፊነታቸውን እንዲረዱ ማድረግ መልካም ነው::

አንዳንድ ምእመናን የንስሐ አባት የሚይዙት ለምን እንደሆነ ጠንቅቀው አያውቁም:: በንስሐ አባት አለመጠቀም ማለት ግን የመግቢያውን በር ቁልፍ እንደመጣል ነውና መለስ ብለው ሊያስቡበት ይገባል:: ሰላመ እግዚአብሔር አይለያችሁ::





www.eotcmk.org

# ሃሁ ለሁፍ

## ሰው መሆንም ቀረ

ዓለምና ሐሰት
ጋብቻ መስርተው
«ውሸት» የሚሉትን
«ቀጣፊ» ልጅ ወልደው
ሲኖሩ...ሲኖሩ..ሲኖሩ...
ተዋደው
ፍቅራቸው ሲደራ
ተጎራብቱና ከዲያብሎስ ጋራ
ያው የጥንቱ «ውሸት»
ረቀቅ አለና
የልጅ ልጅ አፈራ
በእባብ ልቡና፣
እባብም ተማርኮ
በውዳሴ ከንቱ
አዳም «እምቢ» ቢላት
ነግራ ለሴቲቱ
ቀንጥሰው ጎረሷት
እፀ–በለሲቷን
ሊበልጡት እግዜሩን
አልሆነም ነገሩ
አልሰመረም ምክሩ
የተገላቢጦሽ ሆነ–አዳም አፈረ
እንኳን እግዜር ሊኮን
ሰው መሆንም ቀረ፡፡

ሰሎሞን ወ/መድኅን

## ለመጀመሪያዎች ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት

*በ1921/ና1922 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ለተሾሙት አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ጥር 23 ቀን 1923 ዓ.ም ስለሀገረ ስብከታቸው ከንጉሡ ነገሥቱ ከተጻፈላቸው*

«... ስለ አቀማመጥና አስተዳደር

*ሀ/ አቡነ ሳዊሮስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ*
ራሱ የወበሬ ድንበር፡ እግሩ የጐሃርም ድንበር.
..የጽሕፈት አድራሻዎ ጳጳስ ዘደቡብ ኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘደብረ ሊባኖስ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ተ/ሃይማኖት ይባል

*ለ/ አቡነ ይሥሐቅ ዘሰሜን ኢትዮጵያ*
ራሱ ጨጨሆ፡ እግሩ እስከ ኤርትራ ወሰን
...አድራሻዎ ጳጳስ ዘሰሜን ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሚመኤል ይባል

*ሐ/ አቡነ አብርሃም ዘምዕራብ ኢትዮጵያ*
ራሱ ጎንደር፣እግሩ መተማ እንግሊዞች ወሰን ድረስ
...አድራሻዎ ጳጳስ ዘምዕራብ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ሐራ ይባል፡፡

*መ/ አቡነ ጴጥሮስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ*
ራሱ በሻሎ መለስ፡ እግሩ አቦክ ፈረንሳዊ ወሰን ድረስ
... አድራሻም ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞአ ይባል፡፡

*ሠ/ አቡነ ሚካኤል ዘአዜበ ኢትዮጵያ*
ራሱ ጉደር፡ እግሩ እንግሊዝ ወሰን ድረስ
...አድራሻዎ ጳጳስ ዘአዜ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ዜና ማርቆስ ይባል»

ምንጭ ባለምባራስ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል፣ዝክረ ነገር፣አዲስ አበባ፣1923፣ ገጽ 546–554

## አክፍሎት

❖ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድ «ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፡፡ በዚያ ጊዜ ይጾማሉ» እንዳለ ደቀመዛሙርቱ ከተያዘበት ቀን እንደጾሙ እኛም ያንን ለማስታወስ ከዚያ ጊዜ ጀምረን እናክፍላለን፡፡

❖ በፍትሐ ነገሥት እንደተጻፈው የክርስቶስን መከራ ለማስታወስ «የቻለ ሁለት ቀን ይጹም፡ ያልቻለ ግን አንድ ቀን ይጹም ተብሎ በተጻፈው መሠረት እናክፍላለን

❖

❖ ጌታችን 40 ቀንና 40 ሌሊት እንደጾመ፡ እኛም ያንን ለማስታወስ ለ40 ሰዓታት ከእህልና ከውኃ ታቅበን እንጾማለን /እናክፍላለን/፡፡

ምንጭ ድምፀ ተዋሕዶ.ሚያዚያ 15 ቀን 1971 ዓ.ም

## ስእኔም ጥበብ ስጭኝ

ሰዓሊው ሲስልሽ
ዘማሪው ሲያዜምሽ
የቆሎ ተማሪው
ቅኔ ሲቀኝልሽ
የዚህ ሁሉ ምንጩ
አንቺ በመሆንሽ
ለእኔ ጥበብ ስጭኝ
ድንግል ላመስግንሽ

ሱናማዊት



www.eotcmk.org

# ደብረ በልበሊት ኢየሱስ ገዳም

በዚህ እትም ይዘን የቀረብነው በሰሜን ሸዋ/ደብረ ብርሀን/ ሀገረ ስብከት በአንሣር ወረዳ የሚገኝ ገዳም ነው:: የገዳሙ አስተዳዳሪ መምህር ሐረገ ወይን አድ ማሱ ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ያመጡልንን የገዳሙን ታሪክ ለመጽሔት በሚ ሆን መልኩ እንዲህ አቀናብረነዋል::

ዘመኑ የአቡነ ሳሙኤል የመንፈስ ቅዱስ ልጆች ቆመው በትጋት እየጸለዩ እንዳለ ነው:: ቀድሞ መካነ ቅዱሳን አሁን በልበሊት እየተባለ ከሚጠራው ቦታ ላይ ከምድር እስከ መንበረ ጸባኦት የወርቅ መሠላል ተተክሎ አዩ:: በዚያ የወርቅ መሰላል ላይ መላእክት ከመንበረ ጸባኦት ወደ ምድር ከምድር ወደመንበረ ጸባኦት እየተመላለሱ ሲያጥኑና ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ ተመለከቱ:: ምድራቱም በገነት አምሳል በተለያዩ አበቦችና ፍራፍሬዎች አሸብርቃ በልምላሜ ተውባ በአድናቆት አስተዋሉ:: እጅግ ተደሰቱ፤ እናም ወደ ፈጣሪያቸው «አንተ ሁሉን የፈጠርክ ከወዲያኛው ዓለም ወደዚኛው ዓለም መጥተህ የእኛን ሥጋ የለበስህ፤ ተወግረህ፣ተሰቅለህ ሞተህ በሶስተኛው ቀን ሙስና መቃብርን አጥፍተህ የተነሣህ እኛን ፍጡሮችህን ለማዳን ስትል ነው :: አሁንም ጌታችን አምላካችን ፈጣሪያችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በግንባራችን ተደፍተን አንተን የምንለምንህ የቦታውን ክብር እንደገለጽክልን እንድንኖርበት ካልሆነም በረከት ተቀብለን እንድንመለስ ፈቃድህ ይሁን» ሲሉ ለመኑ:: እግዚአብሔርም ንጹሕ ልቦናቸውንና ልመናቸውን አይቶ ደመና ጠቅሶ ደመና ጭኖ አምስት ሺ መነኮሳት አምጥቶ ከተመኙበት ቦታ ሰውሮአቸዋል:: መካነ ቅዱሳን ዋልድቢት ገዳም ተብሎ የተሰየመበት ምክንያት ለዚህ ነው::

ማኅበሩ በአንድ ርዕሰ መምህር የሚተዳደር በዘጠኝ የተከፈለ ነበር:: ዘጠኝ ደወልም ነበረው:: የተለያዩ የቤት እንስሳት ሲኖሩት መልካቸውም በሙሉ ነጭ ነበር::

ደብረ በልበሊት ኢየሱስ የተባለበት ምክንያት ደግሞ፤ ፊቅጦር የተባለ ሰው ከአረብ አገር ወደ ኢትዮጵያ እየተመላለሰ ይነግድ ነበር:: በግመል እያጓጓዘ የወርቅ ግመጃ ሲነግድ በዚህ የተቀደሰ ቦታ ደረሠ:: በአካባቢው ዛፎቹ በተለያዩ አበቦች ደምቀው፣ ፍራፍሬዎች ተንዠርግገው፣ ሳርቅጠሉ ለምልሞ ውኃ በየስርቻው ሲፈስስ በት አየ:: በዚህ ቦታ ግመሎቹን ፈትቶ ጭነታቸውን አራግፎ፣ግመሎቹን ሳር አብልቶ፣ ውኃ አጠጥቶ እሱም ከድካሙ ትንሽ አረፍ ብሎ ሊሄድ አሰበ:: አስቦም አልቀረ ግመሎቹን ፈትቶ ሸቀጡን አራግፎ ውኃ እንዲጠጡ ሳር እንዲበሉ ለቀቃቸው:: እርሱም እረፍት አደ ረገ::

ከእረፍት በኋላ ሳይመሽ ጉዞውን ሊጀምር ተነሥቶ ግመሎቹን ቢመለከት አጣቸው:: በድንጋጤ ወዲያና ወዲህ እየተሯሯጠ ፈለጋቸው:: ጠፉበት ከግመሎቹ መጥፋት ይልቅ ሸቀጡ በክቶና ተባላሽቶ መቅረቱ በሱ ጥፋተኛነት መሆኑን አምኖ አዝኖ ሲያለቅስና ሲተክዝ የተሰወሩ ቅዱሳን አባቶች ተገልጸው አነጋገሩት:: «ወንድማችን ሆይ ከወዴት መጣህ? ወዴትስ ትሄዳለህ?» በማለት ጠየቁት:: ፊቅጦርም የደረሰበትን ችግር ሁሉ አስረዳቸው:: እነርሱም አግዚአብሔር ከእርሱ ፊት ግመሎቹን በመሠወሩ እየተገረሙ «አንተ ሰው በዚች የተቀደሰች ቦታ ላይ እግዚአብሔር የቸርነቱን ሥራ ሊሠራልህ ነው:: እስቲ ዘወር በልና ተመልከት» አሉት::

እንዳሉትም ዘወር ብሎ ሲመለከት ግመሎቹን እየበሉ አያቸው:: በዚህ ጊዜ ከደስታው ብዛት የተነሳ ከእግራቸው ስር ወድቆ ሰገደ:: በመጨረሻም ቅዱሳኑ እየረዱት ጓዙን አጫጭነውት ለመሄድ ከተዘጋጀ በኋላ «እናንተ አባቶቼ ስላደረጋችሁልኝ ቸርነት አመሰግናችኋለሁ:: በሀገሬ ብዙ ነገሮች ይገኛሉ:: የሚያስፈልጋችሁን ነገር ንገሩኝና ላምጣላችሁ» አላቸው:: እነርሱም «ፈቃድህ ከሆነ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚሆን የወርቅ ጽዋ፣የወርቅ ጻህል ፣የወርቅ ጽህና፣የወርቅ መስቀል፣ የወርቅ ግምጃ አምጣልን» አሉት:: እሱም «በሰላም ወደ አገሬ ደርሼ እንድመለስ በጸሎታችሁ አስቡኝ:: አትርሱኝ:: ያዛችሁኝን ሁሉ አመጣለሁ» በማለት ተሰናብቷቸው ሄደ::

ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትን የንግድ ሥራ ጨርሶ ወደ አገሩ ሲመለስ አባቶች ያዘዙትንና ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ከታዘዘው በላይ ጨምሮ ገዛና ለጉዞ ተሰናዳ:: ከእናቷ ማኅፀን ስትወለድ ጀምሮ ዓይነ ስውር የሆነች እናት ነበረችው:: እናቴን የእነዚህ ቅዱሳን አባቶች አምላክ ይፈውስልኛል በማለት ያለመጠራጠር አምነዋል:: እናም እናቱንና ሁለት ወንድሞቹን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞ ጀመረ:: ከዚያ የተቀደሰ ቦታ በደረሱ ጊዜ «አባቶች ያላዘዙኝን ይገፄ መጥቼአለሁና

---

ጠበሉ ከምድር ወደ ሰማይ እየፈላ ዛሬም ህሙማን እየተፈወሱበት ይገኛል:: ከውጭ አገር ሳይቀር መጥተው ብዙዎቹ ከበሽታቸው እየተፈወሱ ሄደዋል:: በሀገር ውስጥም በሐኪም ተስፋ የሳችሁም ከተባሉ በኋላ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ወደዚህ ጠበል በመምጣት፤ በማኅፀን ካንሰር፣በአስም እንዲሁም በተለያዩ በሽታዎች ሲሰቃዩ ቆይተው ጠበሉን በመጠመቅና በመጠጣት የተፈወሱ ምእመናን ብዙ ናቸው::

---

እናንተ ከዚህ ቆዩ» ብሎ እናትና ወንድሞቹን ከገዳሙ አጠገብ ትቷቸው ብቻውን ወደ ገዳሙ ገባ፡፡ ከእነዚያ እጅግ ብዙ ቅዱሳን አባቶች ጋር ተገናኘ፡፡

ስለጉዞው ስለደኅንነቱ ጠየቁት፡፡ «በእናንተ በአባቶቼ ጸሎት በእግዚአብሔር ቸርነት ከዚህ ደረስኩኝ» ማለት ከእግራቸው ላይ ወድቆ እጅ ነሳ፡፡ «አባቶች ለቤተ ክርስቲያን እንድ ገዛ ያዘዛችሁኝን ሁሉ ገዝቼ አምጥቼአለሁ» ብሎ አስረከባቸው፡፡

እነርሱም የሰጣቸውን ዕቃ ከተቀበሉ በኋላ «ያመጣኸው ዕቃ ይህ ብቻ ነውን? ሌላ አላመጣህ ምን? » ቢሉት ግራ ገብቶት «ሌላ ይገኤ የመጣሁት የለም ይኸው ነው» አላቸው፡፡ «ሌላ ያመጣኸው ነገር አለ፡፡ ለእኛ ይታየናል፡፡ አስቀድመን ከምንነግርህ አንተው ንገረን » አሉት፤፤እርሱም የእናቱ ነገር ትዝ አለውና «ያላዘዝንህን ነገር ለምን ወደ ዚህ አመጣህ ትሉኛላችሁ ብዬ ነው፡፡ እናቴ ስት ወለድ ጀምሮ ዓይነ ስውርነች፡፡ እኔም ያለመጠራጠር በጸሎታችሁ ትፈውሱልኛላችሁ በማለት እናቴንና ሁለቱን ወንድሞቼን ይገኤያቸው መጣሁ፡፡ ከዚህ ስደርስ ግን ያልታዘዝኸውን ለምን ይዘህ መጣህ ትሉኛላችሁ በማለት ፈርቼ ከሁለቱ ልጆቿ ጋር በውጭ አስቀምጫታለሁ» አላቸው፡፡ ወደ እነሱ እንዲያመጣቸው ፈቀዱለትና እናቱን ለማምጣት ሲሄድ አባቶች በአንድነት ጸሎት ያዙ፡፡

« ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህችን የተቀደሰች ቦታ ከሁሉ በላይ እንድትሆን ያደረግህ አንተ ነህ፡፡ በቅዱሳኖችህ ላይ አድረህ የቸርነትህን ሥራ የምታሠራ አንተነህ፡፡ ስለዚች የተቀደሰች ቦታና ስለእኛ ስለኃጢአተኞች ባሮችህ ስትል የቸርነትህን ሥራ ሥራልን፡፡ የፈውስ ምልክት አሳይልን» እያሉ በጸሎት እንዳሉ እናቱንና ወንድሞቹን አስከትሎ መጣ፡፡ ቅዱሳን አባቶችም እናቱን በእግዚአብሔር ስም በመስቀል ምልክት አማትበው እፍ ቢሉባት ዓይኗ በርቶላታል፡፡

ነጋዴው ፈቅጦር ከሁለት ጠበብት ወንድሞቹ ጋር ቤተክርስቲያን እንዲሠሩ በአባቶች ታዘው ያላቸውን ሀብትና ንብረት በማምጣት ፣በህንደኬ አገር የወርቅ ግምጃ ሲነግዱ እንዳዩት አድርገው፣ በዕንቁ፣በእብነበረድ፣በወርቅና ሕብሩ ባማረ ቀለም ሁለት አብያተክርስቲያናት አነጹ፡፡



ደብረ በልበሊት ኢየሱስ ገዳም

ደብረ በልበሊት ኢየሱስ ናዝራዊ እና ሀገረ ናዝሬት ገሊላዊት ማርያም ይባላሉ፡፡ እነዚህ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት እንደ ታነጹ ይነገራል፡፡ አብያተ ክርስቲያናቱ ከታነጹ በኋላ በጻድቁ በአቡነ ዜና ማርቆስ መንበር የነበሩት አባ ገብረ ክርስቶስ ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ በርቶሎሜዎስ ጋር ተገኝተው ቀድሰው ባርከዋቸዋል፡፡ እንደ አባ እንጦንስ፣ ተክ ለሃይማኖት፣ዜና ማርቆስ አድርገው ሥርዓት ሠርተውላቸዋል፡፡ ይህ የተቀደሰ ቦታ ርዕሰ ቅዱሳን ተብሎ እንዲሰየምና በፈቅጦር እናት ስም ደብረ በልበሊት ኢየሱስ ተብሎ እንዲጠራ ተደረገ፡፡

ከዚህ በኋላ አባ መዝራእተ አብ፣አባ ማትያስ፣አባ ፈቅጦር የተባሉ የአቡነ ዜና ማርቆስ የመንፈስ ቅዱስ ልጆችም ሕገ እግዚአብሔርን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በዚህ ቦታ ሲያስተ ምሩ ኖረዋል፡፡ አባ ፈቅጦርን አባ በርቶሎሜዎስ ሊቀጳጳስ ከአባ ገብረ ክርስቶስ በታች ለሁለት አብያተ ክርስቲያናት መምህር አድርገው ሾመዋቸዋል፡፡ አባ ፈቅጦርም የአባታችን የአቡነ ዜና ማርቆስን ፈለግ በመከተል ለመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውና ለወገኖቻቸው የወንጌል ቃል ሲያስተምሩ ኖሩ፡፡

በ13ኛው ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ ታላቁ ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አቡነ ዜና ማርቆስን ሲያገለግሉና ሲረዱ ቆይተው በረከት ተቀብለውና ተሰናብተው ጥንት ዜጋ አመል አሁን ደብረ ሊባኖስ ወደሚባለው በዓታቸው ሲሄዱ ቡርቃ በተባለ ቦታ አልፈዋል፡፡

ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ከዚሁ ቦታ ላይ ቆመው፣ «አንቺ ቦታ የተባረክሽ የተቀደስሽ ሁኚ፡፡ ብዙ ሥራ የሚሠራብሽ ምስጢር የሚገለጽብሽ፣ መናንያን የሚኖሩብሽ ሁኚ፡፡ ጠበል ይፍለ ቅብሽ፣ጸበሉም ለዘለዓለም ሕሙማንን የሚፈውስ ይሁን፡፡ የሚያለማውም አትክልት ለመናንያን ምግብ ሆኗቸው ይኑር፡፡» በማለት ባርከው መቋሚያቸውን ነቅለው ሦስት ቦታ ላይ እየደጋገሙ ሲወጉት ጸበል ፈልቆላቸዋል፡፡

ጻድቁ አባታችን ተአምራቱን ከተመለከቱ በኋላ አሁን መናንያን አሉበት ከሚባልበት ዋሻ ፈልፍለው ለአራት ወራት ያህል ተቀምጠው ብዙ ተዓምራትና ትሩፋት ሠርተው ወደ ደብረ ሊኖስ ገዳም እንደ ሄዱ የአባታችን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድል ያስረዳል፡፡

ጠበሉ ከምድር ወደ ሰማይ እየፈላ ዛሬም ህሙማን እየተፈወሱበት ይገኛል፡፡ ከውጭ አገር ሳይቀር መጥተው ብዙዎቹ ከበሽታ ቸው እየተፈወሱ ሄደዋል፡፡ በሀገር ውስጥም በሐኪም ተስፋ የላችሁም ከተባሉ በኋላ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ወደዚህ ጠበል በመምጣት፣ በማኅፀን ካንሰር፣ በአስም እንዲሁም በተለያዩ በሽታዎች ሲሰቃዩ ቆይተው ጠበሉን በመጠመቅና በመጠጣት የተፈወሱ ምእመናን ብዙ ናቸው፡፡ /ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል/



www.eotcmk.org

ሆይ መጥፎ ሃሳብ በአእምሮህ ተመላልሶ ልቡናህን መሳት ደረጃ ብትደርስም ዝም በል፤ አታጉረምርም» በማለት ይመክር ነበር። በቤተክርስቲያን ውስጥ የበለጠ አፍአዊና ውሳጣዊ ዝምታ የሚገባ መሆኑን አስመልክቶም «በቤተክርስቲያንም ውስጥ ቅዱሳት ምሥጢራት የሚፈጸሙበት ቦታ መሆኑን ተገንዝበን ከምንጊዜ ውም በላይ ጸጥታንና አርምሞን እንያዝ» ብሎ አስተምሯል።

አባ ዮሐንስ ኀጺር ራስን የመግዛት ጥቅምን በሚመለከት ም «አንድ መነኩሴ ከፍጹምነት ደረጃ መድረስ የሚችለው መላ ሕዋሳቱን ጠብቆ በልቡናው ተዘክሮተ እግዚአብሔርን ሲይዝ ነው» ብሏል። ከዚህ እምነቱ የተነሣም ስለጊዜያዊ ደስታ ማሰብና ማውራትን ይጠላ ነበር። በዚህም ፈንታ አፍአዊና ውሳጣዊ ሕዋሳትን መሰብሰብ በተለይ ለመነኰሳት የሚገባ መሆኑን በመግለጥ ያስተምር ነበር። የዚህንም ምክንያት «ሰው አብዝቶ ሕዋሳቱን በገዛ ቁጥር በልቡናው የሚመላለሱ ምክንቶች ከ ውስጡ እየጠፉ ይሄዳሉ። ይህም ልቡናን ሰላማዊና የተረጋጋ ያደርጋል» በማለት ያስረዳ ነበር።

አባ ዮሐንስ ይህን በመሰለ መንፈሳዊ ተጋድሎ በርትቶ ሳለ አበምኔቱ አባ ባሞይ ለአሥራ ስምንት ዓመታት በደዌ ዘእሴት ክፉኛ ተይዘው ነበርና። እርሳቸውን ያስታምም ነበር። በስተመጨረሻም አባ ባሞይ ሊሞቱ ሲሉ የገዳሙን መነኰሳት አስጠርተው «አባ ዮሐንስን አክብሩት፣ ታዘዙለት፤ እርሱ በምድር የሚኖር መልአክ ነው እንጂ ሰው አይደለም» በማለት ክብሩ ከሰማያውያን መላእክት ደረጃ መድረሱን መሰከሩለት።

በእንዲህ ዓይነት ተጋድሎ ጸንቶ ሳለ በአካባቢው የሚገኙ አረማውያን መነኰሳቱን ሊያርዱ፣ ሊያቃጥሉ መጡ። ዮሐንስም ወደ አባ እንጦንስ ገዳም ወደ ቁልዝም ሄደ። መሄዱም ሞትን ፈርቶ ለመሸሽ አልነበረም። ነገር ግን በአረማዊው ወንድሙ እጅ ሞቶ እርሱን በመግደላቸው ለዘላለም ሞት እንዳይዳረጉ በማዘን ነበር። በቁልዝም ገዳምም ዋሻ አዘጋጅቶ በብሕትውና ተጋድሎ ውን ተያያዘው።

በአንድ ወቅትም የገዳሙን ምርት በመሰብሰብ ላይ ሳሉ አልታዘዝ ብሎ መነኰሳቱን ያስቸገረ አንድ መነኩሴ ይመክረው ዘንድ ለአባ ዮሐንስ አቀረቡለት። እርሱም አልታዘዝ ያለውን መነኩሴ «ይቅርበለኝ» እያለ ያለቅስ ጀመር። ዓመት ሙሉ ጥቂት ጨው ብቻ ያላት ቁራሽ ደረቅ ዳቤ እየበላ አልታዘዝ ስላለው መነኩሴ አለቀሰ። «ጌታ ሆይ ፍጥረትህን ሳላውቅ አናድጄዋለሁ። አሁንም አንተ ይቅር በለኝ» በማለት ብዙ ጸለየ። በዚህ ጸሎቱም በደለኛው ውን ወደ ታዛዥነት መለሰው።

አባ ዮሐንስ በጸሎቱ በለቅሶው ወደ እግዚአብሔር ከመለሳቸው ኃጥአን መካከል አትናስያ አንዷ ናት። አትናስያ ምእመናንን የምትረዳ ደግ ሴት ነበረች። ሰይጣን በዝሙት ድል ነሣት። በዚህም ቀደም ሲል ታደርገው የነበረውን ምግባር ትሩፋት ሁሉ አስታጎለች። በዚህ ያዘኑ መነኰሳት «ሰይጣን ልጃችንን ቀማን፤ በተቻለን ሁሉ እርዳን» ብለው ለአባ ዮሐንስ ላኩበት። ልመናቸውን ተቀብሎ የሚችለውን ሊያደርግ ወደ አትናስያ ሄደ። ወደቤቷ ገብቶ ከፊቷ ተቀምጦ ፊቷን እያየ ያለቅስ ጀመር። «ምነው ታለቅሳለህሳ? አለችው። መልከ መልካም ነሽና ብታ ሳዝኚኝ ነው» ብሎ መለሰላት። ነገሩ ቢገርማት «ይህማ ያስደስታል እንጂ ያሳዝናልን» ብላ ብትጠይቀው «መልከ መልካም እንደሆኑ መቅረት የት አለና። መፍረስ መበስበስ፣ በእግዚአብሔር ፊት በሠሩት ሥራ መከሰስ መወቀስ ፍርድንም መቀበል ስላለ ያሳዝናል እንጂ» አላት። ኃጢአቷ በሙሉ ታሰባት። ምን ማድረግ እንዳለባትም ጠየቀችው። ከተቀመጠበት ተነሥቶ «ተከተይኝ» አላት። ከኋላ ተከትላው ወጣች። ልትደርስበት ስትሮጥ እግሯ ቆሰለ። ከለበሰችው ልብስ እየቀደደች እንደጫማ በእግሯ ጠምጥማ ትከተለዋለች። ከብዙ ድካም በኋላ ከዮሐንስ በአት ደረሱ። እሳት አንድ ዶላት ጸሎቱን ያደርስ ጀመር። እርሷ ግን ከተቀመጠችበት ነፍሷ ከሥጋዋ ተለየች። የብርሃን መሰላል ተዘርግቶ መላእክት ነፍሷን ሲያሳርጉ አየ። ዮሐንስም ከጸሎቱ ሲመለስ አትና ስያ ሞታ ቢያገኛት እጅግ አዘነ። «ለንስሐም ሳትበቃ ቤቷንም ጥላ መጥታ ... ከሁለት ያጣች አደረኳት» እያለ ያለቅስ ጀመር። በዚህም ጊዜ መልአክ ተገልጦ «አይዞህ አትዘን እሷ'ኮ ፈጣሪዋን ለማግኘት ከቤቷ ለመውጣትና አንተን ለመከተል ስትቆርጥ ገና ከቤቷ ደጅ ሳለች ጸድቃለች» አለው። ዮሐንስም የብርሃን መሰላል ተዘርግቶ መላእክት ነፍሷን ሲያሳርጉ አየ።

በዚህ ዓይነት ኃጥአንን ከእግዚአብሔር እያስታረቀ በአካባቢው ያሉትን ጉሳዎች እያጠመቀ በቅድስና ዘመኑን ፈጸመ። በዘመኑ ፍጻሜም ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው የመጨረሻ ምክሩን እንዲሰጣቸው ለመኑት። ብዙ ከመከራቸው በኋላ «...የራሴን ሥጋዊ ፍላጎት በፍጹም አልከተልም። በራሴ ያልሠራሁትንም ሥራ ሌሎች ይሠሩ ዘንድ በፍጹም አልመከርም» በማለት ከተሞክሮው አካፈላቸው። ብዙ ቃል ኪዳን ከፈጣሪው ተቀብሎ በክብር ባረፈባት ዕለት ቅዱሳን መላእክት በመዘመር በይባቤ ክብርት ነፍሱን ወደ ገነት አሳረጓት። የአባ ዮሐንስ ኀጺር ረድኤት በረከት አይለየን። / ምንጭ- ስንክሳር/

## ደብረ በልበሊት...

/ከገጽ የዞረ/

በዚህ የተቀደሰ ቦታ እግዚአብሔር ለፈቀደለት ሰው ቅዱሳን ተገልጸው ይታያሉ። አንዳንድ ጊዜም ከዋሻው ብርሃን ሲወርድ ይታያል። ከተሰወረውም ቤተ ክርስቲያን የከበሮ፣ጸናጽል፣ደወልና የስብሐተ እግዚአብሔር ድምጽ ይሰማል።

በዚህ ሁኔታ ከተመሠረተ በኋላ ብዙ መናንያንና ባሕታውያን ገዳሙን እያገለገሉ ሲኖሩ፤ ግራኝ መሐመድ የተባለ ሰው አብያተ ክርስቲያናትን ሊያቃጥል እንደሚመጣ አውቀው የአባታችን የአቡነ ዜና ማርቆስ የመንፈስ ቅዱስ ልጆች አባ ጴጥሮስና አባ አምደ መስቀል አስቀድመው ትንቢት ይናገሩ ነበር።

አፄ ናአድም ግራኝ መሐመድ እንደሚመጣ የተነገረውን ትንቢት ሰምተው የአባታችን የአቡነ ተክለሃይማኖትን አፅም በደብረ ጽጌ አስቀምጠውት ነበር። ግራኝ መሐመድም ደብረ ሊባኖስን ሲያቃጥል ደብረ ጽጌን ሳያቃጥላት ቀረ።

ግራኝ መሐመድ ደብረ ሊባኖስን ካቃጠለ በኋላ ገርባ ጊዮርጊስን፣ እምብስ ኮት እግዚአብሔር አብን፣ደብረ አርባእቱ እንስሳን እያቃጠለ ከነሠራዊቱ ደብረ ብስራት ደረሰና ቤተክርስቲያኑን አቃጥላለሁ ሲል ከቤተክርስቲያኑ ጉልላት ላይ ተርብ ተነስቶ የግራኝ መሐመድን ሠራዊት እየነደፈ አባረራቸው። ሠራዊቱ በሚሸሽበት ጊዜ ገደል የገባ የተሰበረ የሞተም አለ።

ግራኝ መሐመድ ሞረት ቆላ አፋፍ ሆኖ በሩቅ ሲመለከት በልበሊት ገዳም በእንቁ፣በእብነበረድ፣ባማረ ወርቅ የ ተሠራውን ቤተክርስቲያን አየ። ያንንም ቤተክርስቲያን ለማቃጠል ወርዶ ከቦታው ሲደርስ ተሰወረበት ። እንደገና ሞረት አፋፍ ወጥቶ ፊቱን ዘወር አድርጎ ሲመለከት ቤተክርስቲያኑን እንደዚያው አምሮ አየው። እንደገና እዚያው ድረስ ወርዶ ቢፈልግ ተሰወረበት። የቤተክርስቲያኑ ንዋያተ ቅድሳትና የቦታው ታሪክ፣የገዳሙ ሥርዓት ሁሉ ቤተክርስቲያኑ ሲሰወር አብሮ ተሰውሮአል።

ከተሰወረው ቤተክርስቲያን በኋላ ቅዱሳን አባቶች በአንድ ሰው ቤተክርስቲያን እንደሚሠራ ትንቢት ይናገሩ ነበር። ትንቢቱም ደርሶ ስማቸውን ለመጥቀስ በማይፈልጉ ምእመን በእግዚአብሔር ፈቃድ ቤተክርስቲያኑ ተሠርቶ ይገኛል።

በአሁኑ ሰዓት ይህ መንፈስ ቅዱስ የረበበበትና ታሪካዊ ቦታ በውኃ ተከቦ በአደጋ ላይ ይገኛል። የአካባቢው ልምላሜ አትክልቶቹ በጐርፍ እየተነቃቀሉና እየተጠረጉ በመሄድ ላይ ናቸው። ስለዚህ የቤተክርስቲያን ተቆርቋሪ የሆንን ሁሉ ይህን የተቀደሰ ስፍራ አድኖ ቅድስናውንና ታሪኩን እንደጠበቀ ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ ይጠቅብናል። ውኃውን ወደነበረበት መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልግ በባለሙያዎች ተገምቷል። ገዳሙ ደግሞ ይህንን ለማሠራት አቅም ስለሌለው የጸሎት፣ የገንዘብ ፣ የቁሳቁስ፣የጉልበት ርዳታ እንዲደረግለት መንፈሳዊ ጥሪውን ያስተላልፋል።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

# ጠባሳ

የአማርኛው መምህር ቀሲስ ልሣነ ወርቅ 40 የመልስ መስጫ ወረቀቶችን ታቅፈው ወደ አንደኛ «ለ» ክፍል አመሩ:: ተማሪዎቻቸው ከመቀመጫቸው በመነሣት ተቀበሏቸውና «እንደምን ዋላችሁ» ለሚለው አባታዊ ሰላምታ ለዛ ባለውና በተባበረው ድምጻቸው «እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነን» ሲሉ መለሱላቸው::

*«ዛሬ ምን እናደርጋለን ነበር ያልኳችሁ»*

«ፈተና» ለመምህራቸው መልስ የሚሰጡ ሳይሆን ዓለም በሙሉ ፈተና መኖሩን እንዲያውቅ የሚያውጁ ነበር የመሰሉት:: የመልስ መስጫ ወረቀቶች ታደሉ:: «ልጆች ስማችሁን፣ክፍላችሁን ቁጥራችሁን መጻፍ እንዳትረሱ እሺ.»

*«እ–ሺ.» የኅብር ድምጽ*

ልጆቹ የታዘዙትን እስኪፈጽሙ ቀሲስ ልሣነ ወርቅ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ሁለት ጥያቄዎችን አሠፈሩ:: አሥፍረውም ዘወር አሉ:: የአርባዎቹ ሕፃናት ዓይኖች በርሣቸው ዙሪያ ይንከራተታሉ::

*«ጥያቄዎቹ ይነበቧችኋል?*

*«አ–ዎ»*

*«ዓለሙ እስቲ የመጀመሪያውን ጥያቄ አንብልኝ»*

«አባት– ማለት –ምን– ማለት– ነው? »

«ጐበዝ ልጅ! ለዚህ ጥያቄ ስለአባት የምታውቁትን ሁሉ ትጽፉላችሁ . »

*«ለምለም» አንቺ ደግሞ ሁለተኛውን አንብቢ »*

«እናት ማለት ምን ማለት ነው?»

«ጐበዝ ልጅ! ለዚህ ጥያቄ ደግሞ ስለእናት የምታውቁትን ሁሉ መጻፍ ነው::

*በሉ ጀምሩ»*

ጸጥ ባለው ክፍል ውስጥ መምህሩ ይዘዋወራሉ:: ያልገባቸውን ይረዳሉ:: የጨነቃቸውን ያበረታታሉ:: የጨረሱትን የመልስ ወረቀት ይቀበላሉ::

ፈተናው ----- አበቃ:: መምህሩም ተሰናብተው ወጡ::

ማታ ቀሲስ ልሣነ ወርቅ ፎቴ ወንበራቸው ላይ ተቀምጠው የተማሪዎቹን መልሶች ማረም ጀመሩ::

አንዴ ፈገግ፣አንዴ ሣቅ፣ሌላ ጊዜ ራሳቸውን በአግራሞት ነቅነቅ፣አንዳንዴ ደግሞ «ወይ ግሩም» እያሉ እርማቱን ቀጠሉ:: ሃያ አንደኛው የመልስ ወረቀት ላይ ሲደርሱ ግን ደንግጠው አቆሙ:: ድንጋጤው ሲያልፍላቸው ከሁለቱ ዓይኖቻቸው መንታ መንታ ሆነው ዕንባዎች ወረዱ:: አንገታቸውን አቀረቀሩ:: እንኳንስ ይህን አግኝተው እንዲያውም ዕንባቸው ለዓይን ቅርብ ነው:: ለረዥም ሰዓት መሆኑን ያወቁት በኋላ ነው::

«ቀሲስ ምን ሆንክ?» አሉ ባለቤታቸው ግራ ተጋብተው፤ቀሲስ ቀና አሉና የመልሱን ወረቀት ለባለቤታቸው ሰጧቸው::

1. *«አባት ማለት ማታ ቆይቶ–ቆይቶ የሚመጣ:: በእማዬ ላይ በጣም የሚጮህ:: ጮኾ ጮኾ ደግሞ የሚማታ፣ከዚያ ደግሞ እማዬን በማታ የሚያስወጣ:: ከዚያ በኋላ ወደቤት አልመጣችም:: የት እንዳለች አላውቅም::*

2. *እናት ማለት – ማታ–ማታ – ቁጭ ብላ አባዬን የምትጠብቀው:: አባዩ በጣም– በጣም ሲጮህባት መሬት መሬት የምታይ፣ከዚያ ከዚያ ሲመታት ደግሞ የምታለቅስ– አንድ ቀን ሊታ ደግሞ ሲመታት በማታ ወጥታ ሄደች– የት እንዳለች እኔ እንጃ...»*

*እንባው በባለቤታቸው ባሰ:: ስቅስቅ ብለው አለቀሱ:: «ታዬለሽ የዚህችን ልጅ ጠባሳ? የውብዳር» አሉ ቀሲስ ዕንባ በዓይናቸው ቸርፈፍ ብሎ «ስታድግ ምን ልትሆን እንደምትችል:: ልጆቹን እንዴት አድርጋ እንደምታሳድግ... »*

*«አይ ቀሲስ መጀመሪያ ካገባች ነውኮ ይኸ ሁሉ ሊሆን የሚችለው» አሉ ወ/ሮ የውብዳር ዕንባቸውን እየጠረጉ::*

የመልሱን ወረቀት ከባለቤታቸው ተቀብለው ስሙን አዩ:: «ሰላማዊት ሙሉጌታ»

በነጋታው ወደ ት/ቤት እንደገቡ የተማሪ ሰላማዊትን ፋይል አወጡ:: የአባትዋን የመሥሪያ ቤት ስልክ መዘዙና ደወሉ:: ከዚያም ከሥራ በኋላ ቤት ሊገናኙ ተቃጠሩ::

«አቶ ሙሉጌታ ዛሬ ድፍረት ካለሆነብኝ የመጣሁት ከባለቤትዎ ጋር መታረቅ እንዳለብዎ ልነግርዎ ነው» አሉ ቀሲስ:: ነገሩ ድንገተኛ ስለሆነባቸው አቶ ሙሉጌታ ደንገጥ አሉና ፊታቸው ተለዋወጠ::

«ቀሲስ ይኼማ የሞተ ነገርኰ ነው»

*«አልሞተም:: ደግሞም ቢሞትም እናስነሣዋለን»*

«ያስታርቁኝ ብላ ላከችዎ እንዴ?»

*«የለብትንም አላውቅ እንኳን ሊልኩኝ»*

« አይ ቀሲስ አንጀቴ ቆርጦልኛል ካሁን በኋላ እኔና እርስዋ ሰው የምንኳኋን አይመስለኝም:: እኔ ካሁን በኋላ ልጄን እያሳደግኩ መኖር ነው የምፈልገው:: የት ገባህ፣ የትወጣህ ብሎ ጭቅጭቅ ሰልችቶኛል»

*ቀሲስ ዝም ብለው ሲያዩዋቸው ቆዩ:: ከዚያም ፀጥታ በመሐላቸው ነገሠ::*

«እርስዎ መቼም የሕግ ሰው ነዎት» አሉ ቀሲስ የፀጥታውን ጅንበር ጥሰው «አዎ» አቶ ሙሉጌታ ምን ሊሉኝ ነው በሚል ስሜት ፊታቸውን ጨፍገግ አድርገው አዩአቸው::

*«ነፍሰ ገዳይ ቢያንስ ቢያንስ ምን ያህል ዓመት ይፈረድበታል»*

«አ–ሥ–ር» ገርሟቸዋል::

*«እንግዲያስ እርስዎም አሥር ዓመት መታሠር ይገባዎታል»*

«እርስዋን ስላባረርኩ! ጨቅጫቃና ነዝናዛን ማሰናበትኰ ነፍስ መግደል አይባልም»

*«የልጅዎን ነፍስ ግን አጥፍተዋል »*

«ምን?» አቶ ሙሉጌታ ይበልጥ ግራ ተጋቡ

ቀሲስ የሰላማዊትን የመልስ ወረቀት አወጡና እጃቸውን ዘረጉላቸው::

«ምንድን ነው? መጥሪያ ነው?» አቶ ሙሉጌታ ግራ መጋባታቸው እንዳይታወቅ ፈገግ ለማለት ሞከሩ

«ያንቡት»

*« ሰላማዊት ሙሉጌታ*
*ክፍል 1ኛ ለ*
*ተራ ቁጥር 21*
*የአማርኛ ፈተና*

ቀጠሉ ማንበብ ...ፊታቸው የኀዘን ደመና እያጠላ እያጠላ ሄደ:: አንገታቸው ፀሐይ እንደጠፋችበት የሱፍ አበባ እየተሰበረ እየተሰበረ ሄደ:: እንደተኰነነች ነፍስ ሽምቅቅ–



www.eotcmk.org

ኩርምት አሉ፡፡ ቀናብለው ቀሲስን ለማየት ፈሩ፡፡ የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደበት ወንጀለኛ ባሉበ ት ደርቀዋል፡፡

ዕንባ -እንደ ሴት ልጅ ተን ሰቅስቀው አለቀሱ፡፡ እናታቸው ስት ሞት እንኳን ያላደረጉትን በ ሁለት እጃቸው አናታቸውን ይዘው አለቀሱ፡፡

መሬቱ ላይ «ጮኸ -ጮ ኸ ደግሞ የሚማታ- ከዚያ ደግ ሞ- ከዚያ ደግሞ እማየን በማታ የሚያ ስወጣ ከዚያ በኋላ» በትል ልቁ ተጽፈው የሰላማዊት መልሶች አንተ -ነህ- አንተ-ነህ የሚሏቸው መስ ላቸው፡፡

«ልጄ-ልጄ-ገድዬሻለሁ፡፡ እውነትም ገድዬሻለሁ» ቤቱን ልቅሶ ቤት አስመሰሉት፡፡ ቀሲስ ቀስብለው ተነሡና ይበቃል፡፡ ይበቃል፡፡ ልቅሶ አሁን አያግለግለንም፡፡ ተግ ይበሉ» አቶ ሙሉጌታ ተቆጥተው ዝም አስኟቸው፡፡

«አሁንስ አቶ ሙሉጌታ ከሚስትዎ ጋር አይታረቁም?»

«እታረቃለሁ ቀሲስ እታ ረቃለሁ፡፡ እስቲ ይኼን ጉድ እርስዎም ይንገሯት፤ ....

ቀሲስ» ዕንባቸው ቀደማ ቸው፡፡

ቀሲስና አቶ ሙሉጌታ በአቶ ሙሉጌታ መኪና ወደ ባለቤ ታቸው ወላጆች ቤት አቀኑ፡፡

«እርስዎ እዚህ ይጠብቁኝ» አሉ ቀሲስ ወደ ግቢው ዘለቁ፡፡

ወ/ሮ ፀሐይ መስቀል ተሳ ልመው እንደተቀመጡ «ዛሬ ምን እግር ጣለዎት» አሏቸው፡፡

*«የልጅ እግር ጣለኝ» አሉ ቀሲስ*

«ወ/ሮ ፀሐይ! የመጣሁት ወደቤትዎ እንዲመለሱ ለመለመን ነው»

«በስማም ምነው አባ» አባ ጨ ጓሬ የሄደባቸው ይመስል ኩሰኩሳቸው

«ደግሜ ከርሱ ጋር- ሞት ይሻላል»

«ሞትማ ጥሩ ነው- መግ ደል ግን» አሉና ቀሲስ ጀምረው ተውት

«ማንን ነው የምገድለው ያንን»

«የለም የለም የገዛ ልጅ ዎን»

«ማ እኔ አይ ቀሲስ የዋሕነዎት

«አዎ እርስዎ»

«ቀሲ -ስ»

«በዚህ ጉዳይ እንኳን ብዙ ባይደክሙ ደስ ይለኛል የሞተ-ነገር- ነው»

ቀሲስ የሰላማዊትን የመልስ ወረቀት ሰጧቸው

*«የምን ደብዳቤ ነው»*

*«የክስ»*

*«ማ-እኔን»*

*«አዎ እርስዎን»*

*«ማነው ከሳሹ»*

*«ልጅዎ !»*

*«ቀሲስ እየቀለዱ ነው»*

*«አይደለም የምሬን ነው»*

*ወ/ሮ ፀሐይ ተቀበሉና ማንበብ ጀመሩ፡፡*

መሐል ላይ ሲደርሱ ጭን ቅላታቸውን ጉልበታቸው ላይ ደፉና ተንሰቀሰቁ፡፡ «ወይኔ ልጄ ልጄን ልጄን!»

«የኔ መንከራተት ሳያንስ ልጄን አሰቃየኋት» ከአንድ ዐረፍተ ነገር በላይ ለመናገር ዕንባቸው ፋታ አልሰጣቸውም፡፡

«እናንተ ተለያይታችሁ የም ትቀሩ ከሆነ ከዚህ የባሰ ጥፋት ገና ይከተላል፡፡ እናንተ ልብ ገዝታችሁ የምትታረቁ ከሆነ ግን ሁሉም እንደገና ይስተካከላል፡» አሉ ቀሲስ፡፡

«ቀሲስ እኔ ኮ መ-መ-ለሱ ባል -ከበ-ደኝ ግን ተመልሶ ያውነው፡፡

«አቶ ሙሉጌታ ከርስዎ በላይ አዝነዋል፡፡ ተጸጽተዋል፡፡ አልቅሰዋል፡፡

«እንግዲያ እኔማ- ቤ-ቴ-ን ጠል-ቼ ነው፣ ልጄን- ጠል-ቼ ነው፣ ትዳሬን ጠል-ቼ ነው»

የወ/ሮ ፀሐይ ቤተሰቦች የሰላምን መልስ ሲያነቡ ከቀሲስ ጐን ቆመው ባልና ሚስቱን ወቀሱ በተለይ የወ/ሮ ፀሐይ አባት ነገሩ እንደ እግር እሳት ነው ያንገበገባቸው «ልጆች ዐዋ ቂዎች ሲሆኑ ዐዋቂዎች ልጅ የሚሆኑበት ዘመን» አሉ፡፡

«ልጆችን ማሳደግ የሚቻ ለው በመናገር፣ጥሩ ት/ቤት በማስገ ባት፣ልብስና ጫማ በመግዛት፣የ ሚበ ሉትን በመስጠት ብቻ አይደለም» አሉ ቀሲስ «መልካም አርአያ በመሆን ጭምር እንጂ፡፡ የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ነው፡፡ አብርሃም ለእግዚአብሔ ር በቅንነት ሲገዛ ቢያይ ይስሐቅም አርአያውን ወረሰ፡፡

*ሁሉም ፀጥ ብሎ ያዳምጣል፡፡*

«የልጆች አእምሮ ነጭ ወረቀት ማለት ነው፡፡ ባልና ሚስት ሲፋቀሩ፣ሲረዳዱ፤ ቤተክርስቲያን ሲስሙ በሕገ እግዚአብሔር ሲኖሩ ካዩ ልጆች በቅድስና መንገድ ያድጋሉ፡፡ ያለበለዚያ በጭቅጭቅና በንዝንዝ፣በድ ብድብና በክስ ቤት ካደጉ የዘላለም ጠባሳ ይዘው ይኖራሉ፡፡ ለሀገር ለቤተክርስቲያንም ፀር ይሆናሉ፡፡

* * *

ወ/ሮ ፀሐይና አቶ ሙሉ ጌታ እንደገና ሀ' ብለው ትዳራ ቸውን ጀመሩ፡፡ አቶ ሙሉጌታ ከሥ ራ ወጥተው ወደ ቤት ይመጡና ከባ ለቤታቸውና ከልጃቸው ጋር ወደ ቤተክርስቲያን ያመራሉ፡፡ የሠርክ ጉባኤ ሲያበቃ ደግሞ ወደቤታቸው ተመልሰው ባለቤታቸውን በሥራ ያግዛሉ፡፡ ወይም ከልጃቸው ጋር ስለ ትምህርት ይነጋገራሉ፡፡

ወ/ሮ ፀሐይ ባለቤታቸው ትንሽ ከዘገዩ ሥጋት ይገባቸውና ሳያስቡት እስከ ግቢው በር አንድ- አንድ- እያሉ ተጉዘው ይጠብቋቸ ዋል፡፡ እርሳቸውም ከመኪናቸው ዱብ ሲሉ ለቤታቸው የሚሆን አንድ ነገር ማንጠልጠላቸው አይቀሬ እየሆነ መጥቷል፡፡

* * *

ቀሲስ ልማነ ወርቅ በሁለ ተኛው ወር ሌላ ፈተና እንደ ገና ተማሪዎቻቸውን ፈተኗ ቸው፡፡ ጥያ ቄዎቹ እነዚያው ነበሩ፡፡ ተማሪዎቻ ቸው ትንሽ ግር አላቸው «አባ» አለ አንድ ተማሪ «አቤት የኔ ልጅ»

« ይኼኮ ባለፈው የተፈተ ነው ነው»

«አዎ ዛሬ ደግሞ እንደገና ትጽፋላችሁ»

ተማሪዎቹ አቀረቀሩ ብዕራ ቸውና ወረቀታቸው ብቻ ማውጋት ያዙ፡፡

ቀሲስ ከክፍል ሲወጡ ፈጠ ን ብለው የሰላማዊት መልስ ፈልገው ተመለከቷት

«አባት ማለት ወደቤት ሲመጣ ዳቦ፣ስኳር ቀይሥር እ-እ- ደግሞ ልብስ ገዝቶ ከዚያ ከዚያ እማየን ያግዛትና ለኔ ደግሞ -እ-እ አስጠንቶኝ -ደሞ ደሞ ቤተክርስ ቲያን በመኪና የሚወስደን እኔና እማየን እሑድ እሑድ ደሞ አስቀ ድሰን ስንወጣ ሽርሽር በመኪና -እን ደ ድ-ሮው ማ-ታ የማይመ ጣና በእማየ ላይ ደሞ-ደሞ የማይ ጮህባት

እናት ማለት አባየ ሲመጣ ከበር ከግቢው በር ትቀበለውና ከዚያ ከዚያ ጉንጬን ሳም ታደርገውና ምሳ ታቀርብለትና -እኔን ታጉ ር ሰ ኝ ና - አ ብ ረ ን ቤተ ክርስቲያን እንሄድና-እንደ ድሮው የማታለቅስ ደሞ ደሞ ትታኝ የማትሄድ ....

*ቀሲስ የደስታ ዕንባ በዓይናቸው ሞላ፡፡*



www.eotcmk.org

# ዓላማ ያለው የወጣትነት ሕይወት

## የሦስት ወጣቶች ሕይወት ለአብነት

/ያተሱ ጉደታ/

«ዓላማ ያለው የኦርቶዶክሳዊነት ሕይወት» ን ግዘፍ በነሣ መልኩ ለአንባብያን ለማቅረብ ብዙ ሳስብ ከርሜ በመጨረሻ ነበር አስተማሪ ሕይወት ያላቸውን ሰዎች ለማነጋገር የወሰንኩት። ሦስት ሰዎች መረጥሁ። ስለነርሱ የሚያውቁ ሰዎች አነጋገርኩና በግሌ የማውቀትን መረጃዬን አጠናከርኩ።

ከነርሱ ሐሳቦችን በማሰባሰብ ለሐመር ጽሑፍ ለማዘጋጀት መፈለጌን ስነግራቸው በመጀመሪያ ሦስቱም ፈቃደኛ አልሆኑም። «ደግሞ የኛ ሕይወት ምን አርአያ ይሆናል?» አሉኝ፣ በተለያየ አነጋገር በአንድ መልእክት። ኦርቶዶክሳዊ ትሕትና። አትሕቶ ርእስ መሆኑን መች አጣሁትና።

አጥብቄ ያገኳቸው። ለውዳሴ ከንቱ ሳይሆን በተለይ ለታናናሾቻቸው ሊሰጥ የሚችለውን ጥቅም አበክሬ ገለጽኩላቸውና እያቅማሙም ቢሆን ተስማሙ። እንግዲያማ ላስተዋውቃችኋ። ሁለቱን ወይዘሪቶች ዳግማዊት ግርማይንና ስብለ መንገሻን እንዲሁም ወ/ሮ ዘውድነሽ አሰፋን።

ዳግማዊት የ25 ዓመት ወጣት ናት። ከአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በዲፕሎማ ተመርቃ ወደ ሥራ ከተሰማራች በኋላ ተቀጥራ የሠራችው አንድ ዓመት ለማይሞላ ጊዜ ነበረ። ወዲያው ወደ ትምህርቷ ተመለሰች። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባች። በ19 91 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪዋን በንግድ ትምህርት አገኘች። ዛሬ በአባቷ ስም የተቋቋመውን የ «ዶ/ር ግርማይ ብርሃኔ ቢታኒያ አፀደ ሕፃናት» እና «ዳግም አምሳል የአጸደ ሕፃናት መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም»ን ቀጥ አድርጋ ታስተዳድራለች። አጸደ ሕፃናቱን ወደ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ከፍ አድርጋዋለች። በአስተዳደር ብቻ ሳይሆን በአስተማሪነቱም የራሷን ክፍል ይዛለች። በሳምንት አስራ ስድስት ሰዓታት እንደምታስተምር አጫውታኛለች። ንግግሯ፣ሥራዋና አሁን የደረሰችበት ደረጃ በብዙ መልኩ ከዕድሜ እኩያዎቿ ጋር አይመጣጠንም። ከዕድሜዋ ብዙ የቀደመች፣በጥቂት ዓመታት ብዙ የኖረች ወጣት መሆኗን የሚያውቋት ሁሉ ይመሰክሩላታል።

ወ/ሮ ዘውድነሽ ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት ናት። የቤተሰብ ኃላፊና አስተዳዳሪ። የበፊት ዓላማዋ ዩኒቨርሲቲ መግባት ነበር። በዚያች በመጨረሻዋ ዓመት፣12ኛ ክፍል ላይ አባቷ በማረፋቸውና እናቷም በመጠለፏ ያላሰበችው ችግር ተደቅኖባት ወደ ቤተሰብ አስተዳዳሪነቱ ባትገባ ኖሮ። በትምህርቱ ባትገፋም ንግዷን ተያያዘችው። አገር ቆርጣ ባሕር ማዶ ድረስ መመላለስ ጀመረች። ንግዱን አሳካች። ኑሮን አሸነፈች። ለዓላማ ኖራ ግቧን መታች። ለበለጠ ድልዛሬም ትሮጣለች።

ሌላዋ የዚህ ዓምድ እንግዳዬ ስብለ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ፋኩሊቲ የኤሌክትሪካል ምሕንድስና ትምህርት ዘርፍ መምህርት /Lecturer/ ናት። ተወልዳ ያደገችው፣ ተምራም የጨረሰችው መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም አጥቢያ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪዋን በ1987 ዓ.ም.፣ሁለተኛውን በ1991 ዓ.ም አግኝታለች። ብዙ ሰዓታት ታስተምራለች፣ ከክፍል ውጪም በየዕለቱ ለምታስተምረው ትምህርት ራሷን ታስተምራለች /ትዘጋጃለች ከማለት ብዬ ነው/ ፤ የፒ.ኤች.ዲ. /ዶክትሬት ዲግሪ/ ትምህርቷን ለመቀጠል የሚጠቅማትን ትሰንቃለች። ገና ሃያ ስድስት አመቷ ነው። በሥራዋ ግን ገፍታለች። ለበለጠ ሥራ፣ለበለጠ ውጤት ሁሌም ትደክማለች።

የየንዳንዳቸው ሕይወት ብዙ ቁም ነገር ያለውና ሰፊ ቢሆንም ከአምስት ባልበጡ ዋና ዋና ርእስ ጉዳዮች ላይ የሰጡኝን ሐሳብ ማቅረቡን ብቻ መርጫለሁ። ተከታተሏቸው።

### ሀ./ ስኬታማነት

ሦስቱም ወጣቶች ካለሚቸው ግቦች ዋና ዋናዎቹን መምታታቸውን ያምናሉ። ነገር ግን እስከአሁን በሠሩት መልካም ሥራ ከመመካት የቀራቸውን ወደ መመልከቱ ያዘነብላሉ። ከዚህ ደረጃ መድረሳቸውን እንዴት እንደሚገመግሙት፣ለነርሱ በሥራ ስኬታማ /sucessful/ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆን ስጠይቃቸው የመለሱልኝም በዚሁ መልክ ነበር።

ዳግማዊት ይህንን ጥያቄ የተመለከተችው ሦስት ነጥቦች አስቀምጣ ነው። «አንደኛ በትምህርቴና በሥራዬ፣ሁለተኛ በቤተሰቤ ውስጥ ባለኝ ሥፍራና በሦስተኛ ደረጃ በማኅበራዊ ግንኙነቴ በሕይወቴ ስኬታማ /sucessful/ መሆን አለመ ሆኔን እገመግምበታለሁ» ትላለ ች።

«በቤተሰቤ ግንኙነት ስኬታማ መሆን ማለት ከቤተሰብ ጋር ባለኝ ግንኙነት ጥሩ መሆን ፣ለቤተሰብ ጊዜ መስጠትና ከቤተሰቦቼ ጋር በእምነት አንድ መሆን ነው። በሃይማኖት አንድ መሆናችን የመግባባታችን፣ የመደማመጣችን፣የመፋቀራችን መሠረት ነው። ከቤተሰቤ ጋር ያለኝ የግንኙነት ገመድ የጠበቀውም ለዚህ ነው። ስለ ሥራዬ ፣ ስለ ትምህርቴ በጠቅላላው ስለ ሕይወቴ አወያዩቸ ዋለሁ። በምን ደረጃ ላይ እንዳለሁ እነግራቸዋለሁ። ረዳቶቼ ናቸውና ሕይወቴ ከነርሱ የተደበቀ አይደለም። የሥራ ሰዓቴ ብዙ ሆኖ ከሌላ ሰው ጋር ለመገናኘት ባይተርፈኝም ለቤተሰቤ ግን ጊዜ እንዲኖረኝ የግድ ነው። »

«በሌላ በኩልም በማኅበራዊ ሕይወቴ ጥሩ ደረጃ ላይ ነኝ ያለሁት ማለት እችላለሁ። ወደ ትምህርቱና ወደ ሥራው ዓለም እኩል መግባቴ /እየተማረች ሠራተኛም እንደነበረች ለመግለጽ ነው/፣ የቤተሰብን ኃላፊነት መቀበሌ፣ ሁሉ ንም በልጅነት መረከቤ ፣ማኅበራዊ ሕይወቴን ብዙ አልጎዳብኝም። አቻችዬዋለሁ። ስለዚህም ደስተኛ ነኝ።»

«በተጨማሪም በትምህርቴና በሥራዬ ስኬታማ ሆኛለሁ ብዬ አስባለሁ። በትምህርቴ መጨረሻ



www.eotcmk.org



ወ/ሪት ሰብለ መንገሻ

ላይ ደርሻለሁ ባልልም ለሥራዬ ማከናወኛ፣ መንደርደሪያ የምት ሆን ዕውቀት ገብይቻያለሁ ብዬ አስባለሁ:: በሥራዬም መዶ በመቶ የተሳካ ሥራ ሠርቻለሁ ባል ልም ከጠበቅሁት በላይ ግን ሆኖ ልኛል::»

ዘውድነሽ ይህንን የስኬ ታማነት ነገር የምትመለከተው ከሌላ አቅጣጫ ነው:: ወጥ_ታ—ወርዷ፣ደክማ፣ ጥሪት ማቆየ ቷን ፣ቤተሰቧን መታደጓን ብቻ ውን ከስኬት /suceecss/ አትቆጥ ረውም:: «ገና ነኝ!» ትላለች:: «የቤቴን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ለባለቤቴ ሰጥቼ መቀመጥ አል ፈልግም:: ኃላፊነቱን ልጋራው እፈልጋለሁ:: ለቤተክርስቲያን ማድረግ ያለብኝ ገና ብዙ ነገር እንዳለ አውቃለሁ:: በተለይም ወላጅ ለሌላቸው የሙት ልጆች አንዲት ነገር ያደረግሁ ቀን የኔ ዓላማዬ ተሳክቷል ማለት እችላለሁ» ብላኛለች::

«እስካሁን የሠራሁትና ስኬታማ የሆንኩበት አንድ ነገር ትምህርቴ በመሆኑ በሕይወቴ ሙሉ ስኬታማ ነኝ ብዬ ለመና ገር አልደፍርም» ያለችኝ ሰብለ ናት:: «ለአገሬም፣ለቤተሰቤም ሠራሁ የምለው፣ሚዛን የሚደፋ ብዙ ነገር የለኝም:: እስካሁን ለአገሬና ለቤተሰቤ ልጠቅም ባት የምችለውን መሣሪያ ስሰ በስብ ቆይቻለሁ:: መሥራት የምጀምረው ከአሁን በኋላ ነው» አከለችበት::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳው ሎስ «ስለቤተሰቦቹ የማያ ስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምን ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው» እንዳለው /1ኛ ጢሞ.5÷8/ በሕይወታቸው ስኬታማ የመሆናቸው ጉዳይ አንደኛው መመዘ ኛቸው ከቤተሰባቸው ጋር ያላቸው ግን ኙነት፣ ለቤተሰባቸው የሚከፍ ሉት ውለታ ነው:: ከዚህም ባሻገር ለአገራ ቸው የሚያደር ጉትን፣ ሊያደርጉት ያቀዱትንና ያላደረጉትን በመመርመር ስኬታማ መሆን አለመሆ ናቸውን ያዩበታል::

## ሀ/ መንፈሳዊነት በሕይወ ታቸው ውስጥ ያለው ሥፍራ

ባለፈው እትማችን እንደ ተመ ለከትነው የብዙ ሰዎች በሃይ ማኖት የመኖር ዓላማ ልዩ ልዩ ነው:: ከቤተ ሰቦቻቸው ብቻ ስለተቀበሉት የሚከ ተሉት፣ ለችግራቸው የሕይወት ጥያቄ



ወ/ሮ ዘውድነሽ አሰፋ

መልስ ለመሻት የገቡበት፣ የመናፍቃንን አፍ ለመዝጋት ጥቅስ ፍለጋ የመጡ ወዘተ የሚሉትን ለአብነት ማንሣታችን ይታ ወሳል:: መነሻ ውንና መድረሻ ውን፣ ዓላማውን ጠንቅቆ ተረድቶ ለሚከተለው ግን ክር ስትና ሕይወት ነው:: ለእን ግዶቻ ችንም ይህንን ጥያቄ አቅር በላቸው ነበር:: «መንፈ ሳዊነት ምን ጠቀማችሁ? ምን ረባችሁ?»

«ከባድ ጥያቄ ነው» ስትል ጀመረች ሰብለ:: «የእ ግዚአብሔርን ሕግጋት እፈጽ ማለሁ? ብዬ ራሴን ስጠይቅ እንዱንም የማላሁ /የጠበቅሁ/ አይመስለኝም:: መንፈሳዊ ነኝ:: ብዬ ለመናገር እፈራ ለሁ:: ግራ ይገባኛል:: መንጠ ፈሳዊ ለመሆን በመውተርተር ላይ እንዳ ለሁ ነው የሚገባኝ:: ገና ጀማሪ ነኝ ብዙ የሚ ቀረኝ::»

ራሷን «ጀማሪ» ብትለ ውም የክ ርስትናን ጣእም ቀም ሳ እንዳጣጣመች ሕይ ወቷ ይመሰክራል:: «በእምነት መኖ ር ደስታ ነው» ያለችኝም ለዚህ ይመስለኛል:: «በእምነት መኖ ር በተስፋ መመላለስ ነው:: ችግር ሲገጥመኝ በቀላሉ ተስፋ አልቆርጥም:: ከዚያ ችግር እን ዲ ምወጣ ይሰማኛል:: በተጨ ማሪም በእምነት መኖር ራስን ለሥነ ምግባር ማስገዛት ነው:: ከራስ ጋር ትግል መግጠም፣ ያልሆነውን ነገር ላለማድረግ፣ መልካሙን ለመፈጸም መታ ገል ነው::»

«ለምሳሌ መጾም፣ ከሃ ይማኖታዊ ትርጉሙ ባሻገር ስመለከተው፣ራስን ለማሸነፍ መታገል ነው:: እስከዚህ ሰዓት ድረስ አልበላም ብሎ መወሰን ን ይጠይቃልና:: ስለዚህ ራስን መቆጣጠርን ራስን መግዛትን ያስተምራል:: ለብስለት አንድ ነጥብ፣ አንድ ደረጃ ነው ብዬ አስባለሁ::»

በንግዱ ዓለም ለተሰማ ራችው ለዘውድነሽ በሃይማኖት መኖር ብዙ ትርጉም ፣ብዙ ጥቅም አለው:: «ሰዎችን እን ዴት በፍቅር ማስተናገድ እንዳ ለብኝ ያስተማረኝ ክርስትና ነው:: ነጋዴ ብሆንም ራሴን ከሥርቆት ፣ከውሸትና ከማጭበ ርበር የምቆጥበው በሃይ ማኖት መኖር ስላለብኝ ነው:: »

« ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት የምደፍረው በእም ነት ስለምጀምረው ነው ብዬ



ወ/ት ዳግማዊት ግርማይ

አምናለሁ:: "ሴት ልትሠራው አይገ ባም" የሚባ ለውን ሥራ ሁሉ ለመሥራት፣በራሴ ለመ ተማመን ችያለሁ:: ለዚህ ሁሉ



www.eotcmk.org

ደግሞ ክርስትና መሪዬ ነው::
ለመነገድ ፈልጎ መነሣት ደግሞም
«ክፉ» የተባለውን ነገር መተው
ቀላል አይደ ለም:: ለምሳሌ አለመጠ
ስረቅ፣ አለመዋሸት፣ አለማጭ
በርበር እንዲህ ቀላል አይደለም::
በተለይ የገንዘብ ድሀ ለሆነ ሰው::
ይሁን እንጂ ጨክኖ "ኃጢአት
ነው?" ማለት ራሱ ለሌላው ትልቅ
ትም ህርት ነው::»

ዳግማዊትም በበኩሏ ሃይማ
ኖተኝነትን፣መንፈሳዊነትን፣ ክርስ
ትናን «የዳግማዊትነቴ ትርጉሜ
ነው» ትለዋለች:: «ክርስ ትና
ማንነቴ /Identity/ ነው:: ጠንክሬ
እንድሠራ የሚያደርገኝ ፣ተስፋ
የሚሰጠኝ፣አካባቢዬን የምረዳበት
ሚዛኔ ክርስትናዬ ነው:: ለማኅበራዊ
ሕይወቴ፣ ለቤተሰብ ግንኙነቴ ፣
ለትምህርቴም ... መሠረት ነው::
በሥራ ላይ ቀናነት፣ቀጥተኛነትና
ስኬታማነት የሚመጡት ከዚህ
ነው::»

«በርግጥ ክርስቲያን ያልነ
በርኩበት ጊዜ ቢኖር ኖሮ አነፃዕሬ
ለመናገር ያስችለኝ ነበር:: ወደዚህች
ምድር ስመጣ፣ ስጠመቅ፣ ይህንን
ማንነት በሰጡኝ ወላጆች መካከል
ሳድግ የማውቀው ነገር ሁሉ ክር
ስትና ስለሆነ ከሌላው ጋር ለማ
መዛዘን ራሱ ይከብደኛል:: ያሁኑን
ማንነቴን የሰጡኝ ወላጆቼ ናቸው::
የእነርሱ የሕይወታቸው መሠረት
ደግሞ ክርስትና ነው:: በአጠቃላይ
ክርስትናን ለእኔ የምመራበት መመ
ሪያ /principle/ ፣አቋሜን፣ ተስፋ
ዬን የማስተካክልበት ነው:: በአ ቋም
መኖርን፣ በተስፋ መመላለስን፣
ራእይ ያለው ሰው መሆንን የሚያ
መጣው ክርስትና ነው:: ማድረግ
የሌለብኝን ነገር ላለማድረግ የምወስ
ነው ለዚያ ነው:: በኃጢአት መን
ገድ ሳይ መላለሱ መኖር እንደ
ሚቻል ማሳየት የሚቻለው በክርስ
ትና ጎዳና ሲጓዙ ብቻ ነው:: ይህም
እኔ አካባቢዬን በክር ስትና እንድ
መዝን ብቻ ሳይሆን ሰውም እኔን
በዚያ እንዲመለከተኝ ያደርገ ዋል::
በተጨማሪም በምሠራው ሥራ ሁሉ
ራስ ወዳድ እንዳልሆን ፣ለአገሬ፣
ለቤ ተሰቤ፣ለወገኔ እንዳስብ ያደርገ
ኛል::»

## ሂ/ ክርስትና...ዘመናዊነት... ዘመናዊ ሕይወት

ዘመናችን «ዘመናዊነት»
የዘመነበት ስለ መሆኑ አገር አው
ቆት ፀሐይ እንደሞቀው የአደባ ባይ
ምሥጢር ሆኗል:: ዘመናዊነት
መሰልጠን፣ለየዘመኑ የሚያ
ስፈልገውን ዕውቀ ትና ጥበብ ሰንቆ
መገኘት መሆኑን ብዙ ሰው ይስማ
ማበታል:: «መሰይጠን» ግን ከዘመና
ዊነት ሳይሆን «ከኃጢ አት» ነው
ክፍሉ:: ይህንን ያደባለቁት ጊዜ
ክርስትናና ዘመናዊት አብረው አል
ሔድ ይላሉ:: ብዙ «ዘመናውያ ን»
ሰዎች ደግሞ «ዘመናዊ» መሆን የሚ
ፈልጉት በሁሉም በኩል ነው:: ሃይ
ማኖቱ ራሱ «ዘመናዊ» ካልሆነ አይስ
ማማቸውም:: ደረጃቸውን አይመጠ
ብቅላ ቸውም:: በተለይም በወጣት
ነቱ የዕድሜ ደረጃ ያሉ፣ «የተማሩ
ናቸው» በሚባሉት ተርታ የተጠ
ሰለፉት ይህ ነገር ጎልቶ የሚታ
ይባቸው መሆኑም ግልድ ነው::
የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ
ቲያንን ለመተቸት የሚነሱ አንዳ
ንድ ሰዎችም ቤተክርስቲ ያናችንን
«ዘመና ዊት አለመሆኗን» በማንሣት
መጀመር ይቀናቸዋል:: ክርስትና
በየዘመኑ ከሚመጡ የሰየጠኑ ሳይ
ሆኑ የሰለጠኑ አስተሳሰቦች ጋር
ይጋጭባቸዋል:: ስለዚህ መሰልጠኑን
ሽተው ይሰየጥኑና ከክርስትና
ይርቃሉ:: ሦስቱ ወጣቶ ችስ?

«ክርስትና ከዘመናዊነት
ጋር አይጋጭብኝም:: ከውጪ ሆነው
የሚ መለከቱ ሰዎች ምናልባት ሊጋ
ጭባቸው ይችል ይሆናል:: ምክንያ
ቱም የሥልጣኔ ምንጪ ቤተክርስ
ቲያን እንደነበረች አይገ ነዘቡምና::
ለምሳሌ ትምህርትን ማንሳት እንች
ላለን:: የትምህርት ሚኒስቴርን
ሥራ ስትሠራ የነበረችው ቤተክርስ
ቲያን ነበረች:: ሌሎችም ብዙ ምሳ
ሌዎችን ማንሣት ይቻላል::ከዚያ
ሁሉ አንፃር ስንመለከተው ዘመና
ዊነትና ክርስትና የሚጋጩበት
ጉዳይ አይኖርም:: ችግሩ ከእኛ አመ
ለካከት ነው:: የቤተክርስቲያንን
የዘመናዊነት ምን ጭነት ካልተቀ
በልን በርግጥም ሊጋጭብን ይችላል»
ያለችኝ ዳግማ ዊት ናት::

ሰብለም በበኩሏ አንዳንድ
ሰዎች የቤተክርስቲያን ትምህርት
መማርን ኋላቀርነት አድርገው እንደ
ሚወስዱ ትጠቅሳለች:: «እንደነዚህ
ዓይነት ሰዎች የተማረ ሰው ሆኖ
ለቤተክርስቲያን ማሰብ አይስማ
ማቸውም:: በእንግሊዝኛ የሚሰበ
ክበት ከውጪ የመጣ እምነት ያለ
በት ቦታ ቢያስገቧቸው በደስታ
ይቀበሉታል:: አጋጣሚ ውን አግኝቶ
ዘመናውያን መሆናቸው የጥንታ
ዊቷ ቤተክርስቲያን እምነት ተከ
ታዮች ከመሆን እንደማያግዳቸው
ማስረዳትን የመሰለ ጥሩ ነገር
የለም::»

በዓላማ የሚኖሩት ሕይወት
ላላቸው በየዘመኑ የሚዘምነው ዘመ
ናዊነት አይለዋወጣቸው:: ምክንያቱም
አበላሉ፣አለባበሱ፣ አሠራሩ በሙሉ
በዚያ በዓላማቸው የሚስተካከል
ነውና:: ሙከራቸው በየዘመኑ የሚመ
ጣውን «ዘመናዊነት እንዴት እንጠ
ቀምበት?» ነው እንጂ የዓላማ ለውጥ
ጉዳይ አይደለም:: ስለዚህ ለእንግ
ዶቹ ዘመናዊነቱን ከክርስትናቸው
ጋር ማጣጣሙ ወይም በዘውድነሽ
አባባል «ዘመናዊነትን ለክርስትና
ማስገዛቱ» የሚከብድ አይሆንም::
ክርስቲያናዊ የሕይወት ሚዛን ላለው
ሰውም ይህ የሚጸንን አይደለም::
ምንም የሕይወት መመሪያ ለሌ
ለው፣ክርስትናን /የኦርቶዶክስ ተዋ
ሕዶ ቤተክርስቲያንን/ በአሻገር
ሲመለከታት ለቆየ ሰው ግን በርግ
ጥም ሁለቱን ማስማማቱ «ሰማይን
በጭ ራሮ» ሊሆንበት ይችላል::

## ሃ/ ሕይወት እሽቅድምድም...

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ
«ታገኙ ዘንድ ሩጡ» እንዳለ ሕይ
ወት ሰዎች ያገኙ ዘንድ የሚሮጡባት
«የእሽ ቅድምድም ሥፍራ» ናት::
የማይሮጥ ፣የማይሽቀዳደም፣ሌላው
ሲሮጥ ዳር ተቀምጦ ፣ጥግ ይዞ የሚ
መለከት የለም:: ሩጫው ሩጫ የሚ
ሆነው፣ ውድድሩም ውጤት የሚያገ
ስኘው ግን አቅጣጫውን በደንብ
ተገንዝቦ፣ መጨረውንና ሽልማት
መቀበያን ለይቶ መሮጥ ሲቻል ብቻ
ነው:: በተለይም ክርስቲያን ሌላው
ስለሮጠ የሚሮጥ ፣ ሽልማት ለሌለ
በት ፉክክር ላቡን የሚያፈስ አይደ
ለም:: ውጤት ላለው ፣ አክሊል
ለሚያቀዳጅ፣ ሽልማት ለሚያ ሰጥ
እንጂ:: «ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ
/ያለ ዓላማ/ እንደሚሮጥ ሁሉ
እንዲሁ አልሮጥም» ነፋስን እንደሚ
ጐስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም»
ይላል ክርስ ቲያን /1ቆሮ.9÷26÷/::

ቆርጦ ለገባበትና ለመወዳ
ደር ለወሰነ ሰው ደግሞ መጨረሻ
ውን ፣ ዓላማውን ግሩም አድርጎ
ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም:: ጠንካራ
ተፎካካሪ ለመሆን መዘጋጀትም ያስ
ፈልጋል:: የዓምደ ወራዙት የዚህ
እትም እንግዶች ለዚህ አብነቶች
ናቸው:: የሚሽ ቀዳደሙበትን መን
ገድ ፣የመጨረሻ ግባቸውን ለይተ
ዋል:: በነርሱ ደረጃ ካሉት ጋር ለመ
ወዳደርም ራሣቸውን አዘጋጅተዋል::
ሮጠዋል:: ኃይል እንዲሆናቸው አም
ላካቸውን በጸሎት ለምነዋል:: እስ
ካሁንም በተወዳደሩበት አሸንፈዋል፣
በሥራዎቻቸው ስኬታማ ሆነዋል::
ለበለጠው ሽልማት እየተጉ ነው::



www.eotcmk.org

በሕይወት ስክታማ ለመሆን ራስን ማዘጋጀት ከሚያስፈልግ ባቸው ተግባራት መካከል «ጊዜን በአግባቡ መጠቀም» ግንባር ቀደሙ መሆኑን እንግዶቼ ይስማ ማሉ:: «ጊዜው የማያቋርጥ ትምህርትን /ዕውቀት መገብየትን/ ይፈልጋል:: የማያቋርጥ ንባብን፣ ጥናትን፣ምርምርን ይሻል:: ክርስትና ወደ ኋላ የሚያስቀር ከሚመስላቸው ጋርም ተወዳድሬ ከነርሱ አንሼ አልገኝም» የሚለውን የዳግማዊትን መልስ ሁሉም ይጋሩታል::

ስለዚህም «ባለው ጊዜ መጠቀም፣ የአንድ ቀንን ሃያ አራት ሰዓታት ከፋፍሎ በሥርዓቱ መጠቀም» ዋና ነገር መሆኑን አብክረው ይገልጻሉ::

## ሂ ፈተናዎቻቸው... መፍትሔዎቻቸው

በተማሪነት ዘመናቸው፣ ሥራ ዓለምም ከገቡ በኋላ አንድ ርምጃ ጋር ለመራመድ ወይም ከአንድ ደረጃ ወደሌላው ለማለፍ መንገዶች ሁሉ አልጋ–በአልጋ አይደሉም:: አልነበሩምም:: ይህ ደግሞ በየትኛውም የሕይወት መስክ ያለ እውነታ ነው::

በሕይወታቸው ስኬታማ የሆኑትን ካልሆኑት፣ በእሽቅድምድሙ አሸናፊ ናቸው ብለን የምንመለ ከታቸው ሁሉ አሸናፊ ለመሆን የቻሉት የአሸናፊነት ልዩ ጸጋ አስቀድሞ የተሰጣቸው ስለሆኑ አይደሉም:: ከሽንፈቶቻቸው፣ ባለፈው ሊያልፉት ከተማናቸው ፈተናዎ ቻቸው በመማራቸው ፣ስሌላው ሽንፈት ትምህርት በመቅሰማ ቸው እንጂ::

ለመማር ለፈለገ ሰው በአካባቢው የሚገኘው እንቅስቃሴ ሁሉ ጥሩ መምህር ነው:: ከአስተማሪውና ከትምህርቱ ገበታ ተስፋ ቆርጦ ይመለስ ለነበረው ለትንሹ ያሬድ ዛፍ ወጥቶ ቅጠል መብላት ተስኗት ብትወድቅ ስትነሣ የቆየችው፣ በትግዕሥቷ ብዛት በመጨረሻ የፈለገችውን ለመመገብ የቻለችው ምጢጢ ትል ትልቅ ትምህርት ቤት ሆነችው:: ወደ በዓቱ መለሰችው፣ለቅድስና አበቃችው፣ለእኛ ሊተርፍ የበቃው ሰማያዊ ዜማ ባለቤት አደረገችው::

የሚገርመው ሌላው ሌላው አይደለም:: ትንሿን ፍጥረት ለመመልከት አፍአዊውን ከውስጣዊው ዓይን አንድ ማድረጉ ነው–የሚደንቀው:: ያቺን ትንሽ ነገር ንቆ ቸል አለማለቱ::

ዘውድነሽ አሁን ያለችበትን የተረጋጋ ሥራ ገንዘብ ለማድረግ የወጣችው ብዙ ዳገት– የወረደችው ብዙ ቁልቁለት አላት:: ለሰብለና ለዳግማዊትም ቢሆን እንዲሁ:: ሴትነታቸው በራሱ በተወሰነ መልኩ «በእሽቅድምድሙ» መሰክ የሚያሳድረው /ያሳደረው/ ተጽእኖ ለመኖሩ ብዙም ምርምር አያሻውም:: ቁልፉና ዐቢዩ ቁምነገር ግን የነርሱን ፈተናውን ለማለፍ መቻል፣አንድ ጊዜ አልሆን ሲል ደግሞ «ለፈተናው ለመቅረብ» አለ መሰልቸት ነው:: ለነርሱ የፈተና ዎቻቸው ሁሉ መፍትሔዎች «ትዕግሥት ፣ተስፋና ፍቅር፣ ቢወድቁም መነሣት እንዳለ ማመን» ናቸው::

ብዙ ወጣቶች አሉን–የ12ኛ ክፍልን ፈተና ከአንድ ጊዜ በላይ ለመውሰድ ምለው የተገዘቱ አምርረው ጠልተው «ዓይኑን ላፈር» ያሉት:: ከእናታቸው ማኅፀን አንድ ጊዜ እንደመውጣት እርግጥ አድርገው የተውት:: በሌላው የሥራ ዓለም ሁሉ አንድ ጊዜ የሞከሩት ሥራ አልሳ ካላቸው በማለቱ የአባታቸው ገዳይ ይመስል ዞር ብለው ላለማየት በመሐላ የሚለያዩት:: ሕይወት መቼ እንዲህ ሆነችና! የሦስቱ ወጣቶች ሕይወት ለዚህ ጥሩ አብነት ይሆናል::

## ህ/ ምክር– ስኬታማነትን ለሚሹ

ዓላማ ያለው ሕይወት ለመኖር ለሚሹ ወጣቶች የስኬታማነትን በር መክፈቻው ቁልፉ በእጃቸው ነው:: የቁ ልፉን በእጃቸው መኖር ያልተገነዘቡ ግን አያሌ ናቸው:: በትምህርት ዓለም ያሉት እንዴት መማር እንዳለባቸው፣ሠራተኞ ቹም ሥራቸውን በምን መልኩ እንደ ሚያስተካክሉት ከመንፈሳዊው ትምህርት ጋር ተስማምቶ ሊሰጣቸው እንደሚገባ የዓምዴ እንግዶች እምነት ነው:: ለአብነት በትምህርት ዓለም የተሰማሩትን አስመልክቶ ሰብለ ያነሣችውን ሐሳብ ላካ ፍላችሁ::

እንደ ሰብለ አስተያየት «የብዙ ተማሪዎች ዋነኛው ችግር የማቴሪያል እጥረት፣የጊዜ ጥረት ወይም የአቅም እጥረት አይደለም:: የሞራል ማጣት ነው:: ይህንን ደግሞ ማስተካከል ይቻላል:: ቢያንስ በተወሰኑ ቀናት ፕሮግራሞችን እያዘጋጁ የጥናትና የምርምር ሞራላቸውን መገንባት ያስፈልጋል:: ክትትልም መኖር አለበት:: በሴሚስተሮች መጨረሻ ያመጡትን ውጤት መከታተል ይገባል:: መቾም ይህንን ማድረግ ያለበት መንግሥት ነው የሚል እምነት የለኝም:: ለራሣችን ልጆች መድረስ ያለብን እኛው ነን::»

«ታላላቆቹ ታናናሾቹን መርዳት አለባቸው:: መወያየት ይኖርባቸዋል:: ለምሳሌ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሆኑ ወጣቶች በትምህርት ደረጃቸው ከነርሱ ያነሱትን /ለምሳሌ ከ12ኛ ክፍል በታች ያሉትን/ ማስጠናት ይችላሉ:: ለነርሱ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መረዳታቸው ራሱ /ከታች ላሉት/ ትልቅ ትርጉም አለው::»

ዳግማዊትም በበኩሏ ስኬታማ ሆኖ ለመገኘት «ፈተናዎችን ተጋፍጦ ለማለፍ መወሰን» ወሳኝ መሆኑን አበክራ ትገልጻለች:: ወጣቶች «በኅብረት የመሥራት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል:: ብዙ ልምድ ያገኙበታል:: ተማሪዎች ከሆኑ ከጎበዝ ጓደኞቻቸው ጋር ቢያጠኑ ይጠቀሙበታል» ትላለች::

እንደ ዘውድነሽ አስተያየት ደግሞ « ስኬታማ ያለመሆን ትልልቆቹ እንቅፋቶች ተስፋ መቁረጥ እና ነገሮችን ከዳር ለማድረስ ቆርጦ አለመነሣት» ዋናዎቹ ናቸው:: «እነዚህን ድል የነሣ ሰው ስኬታማ ሕይወትን ገንዘብ ያደርጋል::»

## ህ/ ለማጠቃለል የጸሐፊው ማስታወሻ

ዓላማ ያለው የወጣትነትን ሕይወት በነዚህ ሦስት እንግዶቼ ሕይወት ተምሬበታለሁ:: ትጉሆች ናቸው:: የያዙትን ነገር ዳር ካላደረሱ ወደኋላ አይ ሉም:: እርፍ ይዘው ወደኋላ አያርሱም:: በመንፈሳዊውም፣ በሥጋዊውም የሕይወት መስመር፣ ዓላማ አበጅተው ከዚያ ለመድረስ የሚተጉ ወጣቶች ናቸው:: ለቤተሰባቸው የሚያደርጉትንና ለአገራቸው የሚያከናውኑትን በጥሙና ያጤናሉ::

አብነታቸው ለብዙ ኦርቶዶክሳውያን የሚበቃ ነው:: በሥራ ሳይጠመዱ፣በትምህርት ሳይተጉ «አቤቱ አቤቱ» በማለት መና የሚወርድላቸው የሚመስላቸው ሰዎች በበዙበት በአሁኑ ጊዜ የሦስቱ ወጣቶች ሕይወት በርግጥም አርአያ መሆን ይችላል:: አገሪቱ ከልብ የሚያዝንባት እንጂ የሚያዝንላት በመነመነበት፣ ያላትን መዝረፉና የራስን ካዝና መሙላቱ ከሙያ በተቆጠረበት፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ራስን ማረቁ ካለ መሰልጠን በታየበት ጊዜ የነርሱ ሕይወት በርግጥም አርአያ ነው::

ክርስትና ፈቃደ እግዚአብሔርን መለመንን ግድ ቢልም በዓላማ ከመኖር ጋር አይጣላም:: «ጌታ ፈቅድ ብንኖርም...» በሉ ተባለ እንጂ ዛሬን ብቻ እየኖራችሁ ነገ እንዳልተፈጠረና እንደማይመጣ ቁጠሩት አልተባለም:: ስለዚህ ዓላማ ይኑረን:: ለመሆኑ እርስዎ ዓላማ አለዎት? ራስዎን ይመርምሩ!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# የሥነ ልቡናና የማኅበራዊ ሣይንስ ባለሙያው... በኤች. አይ. ቪ.. ኤድስ ዙሪያ

ባለፈው እትማችን በዚህ ዐቢይ ርዕስ ላይ የቤተክርስቲያን አባትና የሕክምና ባለሙያው ያወያየንን ማስነበባችን ይታወሳል፡፡ በዚህ እትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥነልቡና ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑትን አቶ ጉበና ዳንኤልን አነጋግረን ከሙያቸው አኳያ ያካፈሉንን እንዲህ አቅርበነዋል፡፡

*/ግርማ ወልደሩፋኤልና አሥራት ከበደ/*

__*ሐመር፡-*__ *ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የማን ችግር ነው?*

__*አቶ ጎበና፡-*__ እንደሚባለው የግለሰቡ ችግር አይደለም፡ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ብቻ ችግርም አይደለም፡ የኅብረተሰቡ ችግር ነው፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ ችግር ስንል በራሱ ምን ማለት ነው? እንደእኔ ችግርን በማጣት ወይም ከዐቅም ጋር አያይዞን አንድ ሰው ገንዘብ ቸገረው፣ አጣ ልንል እንችላለን፡፡ ወይንም በአንድ አስቸጋሪ ውን መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር እያወቅን ፈልገን የገባንበት ነገር ሁሉ ችግር አይደለም፡፡

የኤች አይቪን ችግርነት ከዚህ አንጻር መመልከት ያስፈልጋል፡፡ እንደኔ አመለካከት የኤች አይ. ቪ. ቫይረስ መኖር በራሱ የመጀመሪያ ችግር አይደለም፡፡ ቫይረሱ ባለበት እኛም ባለንበት ተከባብረን በሰላም መኖር እንችላለንና፡፡ ለምሳሌ ኤች. አይ. ቪን ብዙ ጊዜ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር እናያይዘዋለን፡፡ አንድ ሰው በቫይረሱ

---

እኔ ሳስበው አንድ ሰው በኤች. አይ. ቪ./ኤድስ ተያዘ የሚባለው በዚያ ሰው ደም ውስጥ የኤች. አይ. ቪ ቫይረስ ሲገባ ነው፡፡ ይህ ጥሬ ትርጉሙ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሰው አካል ብቻ ያለው ፍጡር አይደለምና፡፡ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ነው፡፡ አንዱ ከአንዱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተደጋግፎ የሚኖር ነው... መንፈሳዊ ሕይወትም አለው፡፡ አንድ ሰው ማኅበራዊ ኑሮው ከተናጋ እንደእኔ አመለካከት በቫይረሱ ተጠቅቷል፡፡ ምን አልባትም ትክክለኛውን ማኅበራዊ ኑሮ የሚ ያበላሽ በሽታ **/Social Immuno Deficiency Virus/** ልንለው እንችላለን፡፡

---

ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ከዚያ ችግር ውስጥ ለመውጣት መፍትሔ አጣ ለት፥ አቃተው፥ ቸገረው እንላለን፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ሳይሆን የሚከተለውን እያወቀ በራሱ ላይ አደጋ ከፈጠረ ያንን ችግር ልንለው አንችልም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ከሌሎች እንስሳት ሁሉ ለይቶ የሚያስብበትን አእምሮ ሰጥቶታልና፡፡ በመሆኑም አንድ ነገር ከማ ድረጉ በፊት፥ እያደረገ እያለና ካደረገ በኋላ ምን ይመጣል? ምን እየመጣ ነው? ምን መጣ? የሚለ የሚያዝበትን መንገድ እያወቀ ከአቅም በላይ በሆነ መንገድ ለምሳሌ ከእናት ወደ ልጅ /ዕንስ/፣ በመርፌ፣ በተበከለ ደም ወዘተ... የሚመጣ ውን ሣንጠቅስ ልቅ በሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሽታውን ቢያመጣ ችግር ነው ልንለው አንችልም፡፡ የጅብ መኖር በራሱ ችግር ሊሆን አይችልም፡፡ ነገር ግን በሩን ሳይዘጋ ለተኛ ሰው ችግር ሊፈጥርበት ወይም ሊበላው ይችላል፡፡ ታዲያ እንደዚህ ዓይነቱ ነገር ምን ሊባል ይችላል?

ስለዚህ ኤች. አይ. ቪን በጥቅሉ «ችግር ነው» ብሎ ማስቀመጡ ተገቢ አይመስለኝም፡፡ በራሳችን ላይ ያመጣነው ነገር ነውና፡፡ የጅብን መኖር ከማውገዝ በርን መዝጋት ወይም ማጥበቅ ያስፈልግ ነበር፡፡ ለእኔ ኤች. አይ. ቪ /ኤድስ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ የራሳችንን ማንነት የት እንደምንውልና ምን እንደምንሠራ እያወቅን ተራ ነገሮች ውስጥ ገብተን «የማን ችግር ነው? የእኔ ችግር ነው? አይደለም?» የሚሉ ነገሮች ላይ ማተኮራችን ትክክል አይመስለኝም፡፡ ኤድስ እንደማንኛውም በሽታ የወቅቱ አደጋ ነው፡፡ ለዚህ አደጋ መስፋፋት ከፍተኛ ውን ሚና እየተጫወትን ያለ ነው ደግሞ ሁላችንም ነን፡፡

ምን አልባት «ችግር ነው» ብለው ለሚያስቡት ሰዎችም ችግር የሚሆነው መድኃኒት ስላልተገኘለት ብቻ መሆን ያለበት አይመስለኝም፡፡ መድኃኒት የተገኘላቸው በሽታዎችም በሰው ልጅ አኗኗር ውስጥ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉና፡፡ ችግሩ ለእኔ እንደሚመስለኝ ከጀርባው ያለው የማኅበራዊ ሕይወት ውድቀት፥ የሞራል መሸርሸር፥ የመንፈሳዊ ሕይወት መበላሸት ነው፡፡ ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ የእነዚህ ችግሮች ውጤት ነው፡፡ ሞራላችን ላሸቀ፥ ግብረ ገብነታችን ተበላሸ፥ አኗኗራችን መረን ወጣ፥...ይህም ኤች. አይ.ቪ/ ኤድስን የመሳሰሉና አሁን ችግር የተባሉ ነገሮችን ወለደ፡፡

ሁልጊዜም የሚገርመኝ ይህንን ሁሉ እንደ ችግር አለማየታችን ነው፡፡ ኅብረተሰቡ ድሮ ሊጋብቻ የነበረውን ክብሬታ ሲተወው፥ ከትዳር ጓደኛው ውጪ ሲማግጥ ፥ ፍቺ ሲበራከት... ችግር አልተባለም፡፡ አካባቢው ሲቆሽሽ ችግር ካልሆነ፥ ማንም ሰው ቆሻሻ እያወጣ ከቤቱ ደጃፍ ሲደፋና ሽንቱን በየመንገዱ ሲሸና እንደ ችግር ካልታየ ጉንፋን ሲይዘን ችግር የሚሆንበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ ከዚሁ ጋር የሚያሳዝነኝ ነገር ለኤች. አይ. ቪ. መድኃኒት ተገኘለት ቢባል ብዙ ሰዎች ተመልሰው ወደነበሩበት የቆሸሸ አኗኗር



www.eotcmk.org

እንደሚገቡበት ሳስብ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን ችግር ተደርጐ የታየው ቫይረሱ እንጂ የእኛ የሰው ልጆች የችግሩ ፈጣሪ መሆን አይደለምና፡፡

ልክ እንደ ኤች. አይ. ቪ./ኤድስ አሁን ማየት ያልቻልናቸው ነገር ግን ማየት ያለብን ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ መልካም የሆነው ማኅበራዊ አኗኗራችን መተሳሰባችን ሲላላ፣ ሃይማኖት እንደሞኝነት ሲቆጠር፣ መከባበር መረዳዳቱ እንደባዶነት ሲታይ... የደነገጠ ሰው የለም፡፡ በእነዚህ ችግሮች ዙሪያም የተካሄዱ ወርክሾፖች ትዝ አይሉኝም፡፡ ኤች. አይ. ቪ./ኤድስ መጥቶ አካላችን መሞት ሲጀምር ነው መጨነቅ የጀመርነው፡፡ ለምን አካላዊ ችግራችንን <u>/ባዮሎጂካል ኢሚዩኖ ዲፊሸንሲ አችንን/</u> ብቻ እንመለከታለን? ለምን ሰውነትን የሚያከሳውና፣ በሕመም የሚገድለው ብቻ ይታየናል? ለምን ምንም ሳይታወቅ በቁም በድን የሚያደርገውን የማኅበራዊ ትስስራችንን መላላት፣ የሞራል መጥፋትን፣ ማየት ተሳነን? እንደእኔ ኤች. አይ. ቪ./ኤድ ስን ብቻ ነጥሎ ማየት የሚቻል አይመስለኝም፡፡

ስለዚህ ኤች. አይ. ቪ./ኤድስ የብዙ ችግሮች ውጤትና የሌሎች ችግሮችም መነሻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ችግር ከሆነ ችግርነቱም የአንድ ሰው ወይም የተወሰኑ ሰዎች ችግር ሳይሆን የሁሉም ችግር ይሆናል፡፡ አንድ ሰው ራሱን ችሎ ብቻውን ሊቆም አይችልምና፡፡

*<u>ሐመር፡-</u>ለእርስዎ አንድ ሰው በኤች. አይ. ቪ./ኤድስ ተያዘ ማለት ምን ማለት ነው?*

<u>*አቶ ኀበና፡-*</u> እኔ ሳስበው አንድ ሰው በኤች. አይ. ቪ./ኤድስ ተያዘ የሚባለው በዚያ ሰው ደም ውስጥ የኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ ሲገባ ነው፡፡ ይህ ጥሬ ትርጉሙ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሰው አካል ብቻ ያለው ፍጡር አይደለምና፡፡ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ነው፡፡ አንዱ ከአንዱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተደጋግፎ የሚኖር ነው... መንፈሳዊ ሕይወትም አለው፡፡

አንድ ሰው ማኅበራዊ ኑሮው ከተናጋ እንደእኔ አመለካከት በቫይ ረሱ ተጠቅቷል፡፡ ምን አልባትም ትክክለኛውን ማኅበራዊ ኑሮ የሚያበላሽ በሽታ /Social Immuno Deficiency Virus/ ልንለው እንችላለን፡፡ አካላችን በቀጥታ በቫይረስ ባይያዝም፣ በሐኪሞች ብንመረመርና ነጻ ብንመስልም እንኳ ትክክለኛውን የአኗኗር ሁኔታ /ኑሮአችንን/ ማዛባት የቻለ በሽታ አለብን ማለት ነው፡፡ ኢኮኖሚአችንም ከወደቀ እንደዚያው፡፡ ለምሳሌ መርፌ ለመወጋት የራሳችንን መርፌ ገዝተን ወደ ሐኪም ቤት ስንሄድ ሐኪሙ የእኛን መርፌ አስቀምጦ ሌላ ሰው በተጠቀመበት መርፌ ቢወጋንና የእኛን እየጠራቀመ ቢሸጠው ለእኔ ይህ ሰው ጤነኛ አይደለም፡፡ በደሙ ውስጥ ቫይረስ ባይገኝም ከጤነኛው ሰው የማይጠበቅ ተግባር እየፈጸመ በመሆኑ <u>ኢኮኖሚካል ኢሚዩኖ ዶፊሸንሲ</u> /.Economical Immuno deficiency ወይም ስፕሪቹአል ኢሚዩኖ ዶፊሸንሲ /Spiritual Immuno Deficiency/ ሊባል በሚችል በሽታ ተይዟል፡፡

በመሆኑም ከኤች. አይ.ቪ.. ደም ውስጥ መግባት ቀድመው የሚመጡ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ አመንዝራነት በሽታ ነው፡፡ ባል ከሚስቱ፣ ሚስት ከባሏ ውጭ ሲያመነዝሩ የአመንዝራነት በሽታ ይዟቸዋል ማለት ነው፡፡ ለገንዘብ ሲል በወገኑ ላይ የክፋት ሥራ የሚሠራውም ጤነኛ አይደለም፡፡ እንግዲህ እንደዚህ ዓይነት ምልክቶች ናቸው በአካል ገዝፈው ኤች. አይ. ቪ.. ሆነው የሚመጡት ወይንም ምክንያት የሚሆኑት፡፡

በመሆኑም በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጠንካራ መሠረት ላይ ላለ ሰው የአካሉ በኤች. አይ.ቪ./ኤድስ መያዝ ማለት ምንም ማለት አይደለም፡፡ እርስ በርስ ያለን ትስስርና ፍቅር መሠረት ከያዘ ኤች. አይ.ቪ. ተራ ነገር ይሆናል፡፡ ነገር ግን እኔን የሚያሳስበኝ ሌሎቹን ነገሮች ሁሉ ትተን ለኤች. አይ .ቪ./ ኤድስ ብቻ ትኩረት መስጠታችን ነው፡፡ የበለጠ ማተኮር ያለብን የኤች. አይ.ቪ..ን መስፋፋት ሊገቱ በሚችሉትና ኅብረተሰቡ ይዟቸው በነበሩት ማኅበራዊና ባሕላዊ እሴቶቻችን፣ ሃይማኖታችን፣ ወዘተ... ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ነገሮች ካሉን በኤች. አይ. ቪ./ ኤድስ መያዝ ማለት የሁሉም ነገር መጨረሻ እንዳልሆነ እንጠረዳለን፡፡ አንድ ሰው ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በደሙ ውስጥ ቢኖርም መሥራት ይችላል፡፡ ራሱን ጠብቆ ለሌሎችም ምክንያት እንዳይሆን ተጠንቅቆ ያሰበውን የጀመረውን መልካም ነገር ከፍጻሜ ለማድረስ የሚከለክለው ነገር የለምና ነው፡፡

*<u>ሐመር፡-</u>አገራችን አሁን ካለችበት ሁኔታ አንጻር የኤች. አይ.ቪ./ኤድስን ሥርጭት መከላከል ይቻላል?*

<u>*አቶ ጐበና፡-*</u> አዎ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ኢኮኖሚያችን /ድህነታችን/ ብቻ ታይቶ «መከላከል አንችልም» የሚል ሃሳብ ካለ ትክክል አይደለም፡፡ ያልተያዙ ሰዎች እንዳይያዙ፣ የተያዙትም እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ እንችላለን፡፡ ለዚህ ደግሞ ገንዘብ ብቻ አይደለም የሚያስፈልገው፡፡ ከገንዘብ በላይ የሆኑ ነገሮች አሉ፡፡ ስለኤድስ በቂ ግንዛቤ ማግኘት፣ እያንዳንዱ ሰው የችግሩ ተቋዳሽ መሆኑን ማመንና፣ ቀድሞ የነበሩትን መልካም ባሕሎች እንደገና ማምጣት ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ችግራችን ስለ ኤች.አይ. ቪ./ኤድስ የተቀመጠ ፓሊሲ ቢኖርም በቂ ግንዛቤ አለ መያዛችን ነው፡፡ ሁሉም በየራሱ መንገድ ይጓዛል፡፡ ለምሳሌ «በኤች. አይ. ቪ./ ኤድስ የተያዙና ያልተያዙ» የሚል የማይገባኝ አባባል አለ፡፡ ዝሙት በተስፋፋበት፣ ባልተቀቀለ መርፌ መጠቀም እንደ ሕግ በሆነበት አካባቢ /Enviro nment/ እየኖሩ ነፃ ነኝ ማለቱ የግንዛቤ ማነስ ይመስለኛል፡፡ ቢያንስ አእምሮዬ ነፃ አይደለም፡፡ ኅሊናዬ ውስጥ መረበሽ አለ፡፡ ውስጤ ሰላም የለውም፡፡ በቀጥታም ቫይረሱ በአካላችን ውስጥ ባይኖርም ልጆች ያለ አሳዳጊ ቀርተዋል፤ ትዳር ተናግቷል፡፡ ኢኮኖሚያችን ደቋል፡፡ ማኅበራዊ ኑሮአችን ምስቅልቅሉ ወጥቷል፡፡ ስለዚህ በቀጥታ ባንያዝም በተዘዋዋሪ የቫይረሱ ተጠቂዎች /atta cked/ ነን ማለት ነው፡፡

ሌላው ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን መቆጣጠር እጅግ ከባድ የሚመ



www.eotcmk.org

ስለን ከኢኮኖሚ አንፃር ሳይሆን ራሳችንን /ማንነታችንን/ ስለምናውቅ ነው:: ማኅበራዊ ትስስራችን እንደላላ፣ ተነጋግረን መደማመጥ እንዳቃተን፣ አባት ልጁን ቢመክረው እንደማይቀበለው፣ ባል ለሚስቱ– ሚስትም ለባሏ ታማኝነት እንደ ቀረ፣ ስለምናውቅ ተስፋ እንደሌለን እናስባለን::

የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከል ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል:: ወደ ኋላ ተመልሰን መልካም ምግባራችንን ፣ እግዚአብሔርን መፍራት፣ እርስ በርስ መከባበራችንን፣ መረዳዳት መጠያየቃችንን ፣ ታማኝነታችንን... እንደ ገና ማምጣት መቻል አለብን:: ነገር ግን ካለፈው ልምዳችን ማየት እንደሚቻለው ከእንቅልፋችን የምንነቃው ነገሮች ካለፉና ተበልተን ተበልተን ካለቅን በኋላ መሆኑ ችግራችንን ውስብስብ ያደርገዋል:: ብልህ የሆኑ ሰዎች የወደፊቱንም መመልከት ይችላሉ:: እኛም ያለፈውንና የወደፊቱን ረጋ ብለን ማሰብ ይጠበቅብናል:: ለመሆኑ ወደ ኤች.አይ.ቪ. እየመራ ያመጣን ምንድ ነው? ራሳችንን ቆም ብለን መጠየቅ ያለብን ይመስለኛል::እንደገናም ኤች.አይ. ቪ. /ኤድስን ለማቆም ብቻ ሳይሆን «ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምን ሊያስተምረን ነው የመጣው?» ብለን ራሳችንን መመርመር አለብን:: እነዚያ እንደ ቀላል ነገር የምናያቸውንና ዋጋ የሳጣናቸውን ኅብረተሰቡ ግን ለዘመናት የዳበራቸውን ልምዶች ፣ አመለካከቶች ፣ ሃይማኖታዊ ሕግጋት... በሙሉ ተራ ነገሮች እንዳልሆኑ መለስ ብለን በማስተዋል ራሳችንን ካላስተካከልን ምንአልባትም ከኤች. አይ.ቪ. /ኤድስ የባሰም ነገር ሊመጣ ይችላል::

*ሐመር፦ አንድ ሰው በኤች.አይ.ቪ /ኤድስ መያዙን እንዳወቀ ምን ማድረግ አለበት?*

*አቶ ኅበና፦* መሠረታዊው ነገር እያንዳንዱ ሰው ሲወለድም ይሁን ከተወለደ በኋላ የራሱ የሆነ ችሎታ እንዳለው ሁሉ አንድ ዓይነት ጉድለት ሊኖረው እንደሚችል ማመን ነው:: የተማረ ያልተማረ፣ የሚሰማ ወይም የማይሰማ... ሊሆን ይችላል:: ኤች.አይ.ቪ./ኤድስም ከዚህ የተለየ አይደለም:: ሞትን ካሰብንም በዚህ ቀን ብሎ በቀጠሮ ሲመጣ አጋጥሞኝ አያውቅም:: ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ ግን ከአሥራ ዓመት በላይ ዕድሜ ሊሰጥ ይችላል:: በመሆኑም ኤች. አይ .ቪ./ ኤድስን ስንረዳው አመለካከታችን ይቀየራል:: የዚያኑ ያህል አንድ ሰው ኤች.አይ .ቪ. በሚያዝበት ጊዜ የሚኖረው ስሜትም ሆነ ሌሎች ስለ እርሱ ያላቸው አመለካከት የተስተካከለ ይሆናል:: እንዲህ ስል በኤች አይ.ቪ./ኤድስ ብንያዝ ምንም አይደለም ብሎ መቀበል፣ አለመደናገጥ፣ አለመበሳጨት ብቻ በራሱ በቂ አይደለም::

ዋናው ነገር የኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ ያለበት ሰው ምን ማድረግ አለበት? የሚለውን ነገር ማወቅና ማድረግ ላይ ነው:: ለሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ መጠንቀቅ፣ለራስ ማድረግ የሚገባንን እንክብካቤና ጥንቃቄ ማድረግ፣ ከኅብረተሰቡ በኩል ሊገጥም የሚችለውን መገለል ልቋቋመው እችላለሁ ወይ ብሎ ራስን ማዘጋጀት... የመሳሰሉት ዋናና መሠረታዊ ናቸው::

*ሐመር፦ በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡት ሕፃናትስ?*

*አቶ ኅበና፦* የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስን የጥፋት ውጤት መመልከት የሚቻለው በዚህን ጊዜ ነው:: እኔንም ከሁሉም በላይ የሚያሳስበኝ ምንአልባትም ከ15 ዓመታት በኋላ ወደ 3,000,000 የሚጠጉ ልጆች እናትና አባታቸውን ያጡ ይሆናሉ የሚለው ግምት ነው:: እነዚህን ሦስት ሚሊዮን ልጆች እንዴት አድርገን ነው የምናሳድገው፣ የምንንከባከበው፣ የምናስተምረው? ... ጨለማ ነው:: በእኛ አገር የኢኮኖሚ አቅም ቀርቶ በጣም አደጉ በሚባሉት አገሮች እንኳን ሦስት ሚሊዮን እናትና አባት የሌላቸውን ልጆች ሰብስቦ ለማሳደግ ይከብዳቸዋል:: እንግዲህ የሞተው ወገን ከወለዳቸው ልጆች ውጪ ምን ያህል ሰዎችን በሥሩ ያስተዳድር እንደነበር ስናስብ ደግሞ ምን ያህል ሰው እንደ ሚጎዳ መረዳት እንችላለን:: የኑሮ አቅምን ልቅነት ስንመለከተው ደግሞ የምንከፍለው ብዙዕዳ ምንአልባትምሊሚቀ ጥሉት ሦስትና አራት አሥርት ዓመታትም በቀላሉ የምንወጣው ላይ ሆን ይችላል::

የሆነው ሆኖ በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ሳጡት ሕፃናት ልናደርገው ይገባል ብዬ የማስበው ራሱ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በሄደበት አቅጣጫ መሄድን ነው:: ለምሳሌ ኤች. አይ.ቪ./ኤድስ እያደረገ ያለው ምንድነው? የእኛን የማኅበራዊ ሕይወት ትስስር እየተጠቀመበት ነው:: ባልን ከሚስት ሚስትን ከባል ይነጣጥላል:: ጎረቤትን ከጎረቤት ያራርቃል:: አባትና ልጅን ይለያያል:: እንደዚህ በሕይወታችን ውስጥ ገብቶ ግንኙነታችንን ሰባብሮ ነጣጥሎ ተጫወተብን:: አንድን ቤተሰብ ብቻውን አስቀረው:: ልጆችን ወደ ጎዳና እንዲበተኑ አደረገ::

እንግዲህ እኛ ቀድሞ የነበረንን ትስስር ከማጠንከር ባሻገር ተጨማሪ መዋቅር መንደፍ ይገባናል:: ለምሳሌ የባልና የሚስት ግንኙነት፣ ፍቅርና መተማመን እጅግ የጠበቀ መሆን አለበት:: ኤድስ መግቢያ ቀዳዳውና የመስፋፊያ መንገዱ ያደረገውም ይህንኑ ነውና:: በተጨማሪም የራስን ልጆች ብቻ ሳይሆን የእኅት ፣ የወንድም ፣ የአጎት ፣ የአክስት ፣ የጎረቤት... ልጆችን ማቅረብና መንከባከብ ያስፈልጋል:: ይህንንም የምናደርገው ልጆቹ ወላጅ አልባ ከመሆናቸው በፊት ነው:: እንደዚህ ዓይነቱ ባሕል ከዳበረ አስቀድሞ የተመሠረተው ፍቅር የእናትና የአባትነት ስሜትን በልጆች ላይ ስለሚፈጥር አሳዳጊ አልባ አይሆኑም:: የነገ የአገር ተተኪ ከመሆንም አይታገዱም:: የኤድስም መከፋፈያ መንገዱ ይቆረጥበታል::

ይህም አዲስ ነገርን መፍጠር ሳይሆን ከዚህ ቀደም የነበረንን መልካም ባሕል ማዳበር ብቻ ነው የሚያስፈልገው:: ከዚህ ቀደም ዘመድ የዘመድን ልጅ ወስዶ ያሳድጋል:: ያስተምራል:: እናት የጎረቤት ልጆችን ሳይቀር እስከ ማጥባት ትደርስ ነበር:: ማብላት፣ ማጠጣቱ፣ ሲያጠፉም እንደ ራስ ልጅ መቅጣቱ የነበረ ነው:: ትውልድ እንዲቀጥል፣ ልጆች በየጎዳናው እንዳይበተኑ የግድ ወደ ቀድሞው ባሕላችን ተመልሰን ይህ ንን ተግባራዊ ማድረግ አለብን:: በረሃብና በእርዛት ሲሰቃዩ፣ እያዩ ከንፈርን መምጠጡ ብቻ ዋጋ የለውም::

*ሐመር፦ እግዚአብሔር ይስጥልን*



www.eotcmk.org

# ብጸልይም ልረሳት አልቻልኩም

<u>ጥያቄ</u>:- አሁን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪ ነኝ:: የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ከአንዲት በሌላ ትምህርት ቤት ከምትማር ልጅ ጋር ፍቅር ይዞኝ ነበር:: ብዙ ጊዜም ደጋግሜ ጠየቅኋት:: ነገር ግን መልሷ አለኝ ከማለት የተለየ አልሆነም:: እኔ ግን ሌላ ጓደኛ እንዳላት ባረጋግጥም ምክንያቷን ልቀበል አልቻልኩም:: እርሷም ከኅሊናዬ ልትጠፋልኝ አልቻለችም:: እግዚአብሔር ለእኔ የሚላትን እስኪሰጠኝ መታገስና መርሳት እንዳለብኝ ባስብና ብጸልይም ልረሳት አልቻልኩም:: ዘወትር እየተጨነቅሁ በመሆኑም በትምህርቴ ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ምክራችሁን ለግሱኝ::

ወንድማችሁ
/ከናዝሬት/

<u>መልስ</u>:- ወጣቶች ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ሲደርሱ ሊዋደዱ ተዋደውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለትዳር ሊበቁ ይችላሉ:: ነገር ግን አልፎ አልፎ እንደሚታየው ስሜቱ ከአንደኛው ይልቅ በሌላው ላይ ሊያይልና አፍቃሪውም ወገን የግድ ካልተወደድኩ በማለት በሌላው ላይ ችግር የሚፈጥርበት አጋጣሚም ይኖራል:: ይህ የእውነተኛን ፍቅር ምንነት አለመረዳት ፣በመንፈሳዊ ሕይወት አለመብሰልና የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማወቅ ነው:: የሆነው ሆኖ ዘላቂውን ትዳር ለሚያስብ ሰው ትዳሩ መሠረት የሚኖረው በእግዚአብሔር ፈቃድ መመራት ሲቻልና ፍቅሩም ከሁለቱም ወገን ሲሆን ብቻ ነው:: በስሜት ተመርቶ በአንደኛው ወገን ፍላጎት ብቻ የሚመሠረት ትዳር ትዳር ሊባል አይችልም::

አንተንም የገጠመህ ምንአልባትም ከዚህ የተለየ ላይሆን ይችላል:: ልጅቷን ወደድካት፣ አነጋገርካትም:: እርሷ ግን ፈቃደኛ አልሆነችም ወይም ሌላ ጓደኛ እንዳላት ገለጸችልህ:: ያለችው ትክክል እንደሆነም አረጋገጥክ:: በዚህን ጊዜ ፍቅርህ እውነተኛ ፍቅር ቢሆን ኖሮ ሊቆርጥልህ በተገባ ነበር:: ምክንያቱም እውነተኛ ፍቅር ያመዛዝናል፡ ለራሴ ብቻ ይሁን የሚል የራስ ወዳድነትና የስግብግብነት መንፈስ የለበትም:: በዚያ ላይ አንተ መውደድ፣የራስህን ሰው መምረጥ እንደ ምትችለው ሁሉ እርሷም የመውደድ የመምረጥ መብት እንዳላት ማገናዘብ ትችል ነበር:: እንዲሁም የወደዱትን ሁሉ ማግኘት ሊከብድ እንደሚችልና ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚሆን ነገር እንደሌለ አምነህ መቀበልም ትችል ነበር::

በመሆኑም ይህንን ሁሉ ከግንዛቤ ወስደህ ለጥያቄ ከመሄድህ በፊት ራስህን ማዘጋጀትና ፈቃደ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ነበረብህ:: አስቀድመህ የማግኘትም ሆነ የማጣት፣እሺ ወይም እንቢ የመባል እድል ሊገጥምህ እንደሚችል ማሰብ ነበረብህ:: እንደዚያ ቢሆን ኖሮ «አለኝ» ወይም «አይሆንም» የሚለውን ቃል በሰማህ ጊዜ ልቡናህ መቀበል በቻለና እስከዛሬም ድረስ የግድ የእኔ ብቻ መሆን አለባት በሚል አሳብ ባልተጨነቅህ ነበር::

ወንድማችን የችግርህ ዋነኛው ምክንያት እውነታውን ለመቀበል ራስህን አለማዘጋጀትህና የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበል አለመፈለግህ ነው:: አስቀድሞም ማግኘት እንዳለ ሁሉ ማጣትም ሊኖር እንደሚችል ለሚያስብና በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚመራ ሰው የሚገጥመውን ሁሉ እንደአመጣጡ ለመቀበል ብዙም አስቸጋሪ አይሆንበትም::

በተጨማሪም በእውነተኛ ፍቅር ውስጥ ስግብግብነት፣እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን የሚል የራስ ወዳድነት አሳብ ሊኖር አይገባም:: ብዙ ወጣቶች በአጉል የወጣትነት ስሜት ተመርተው ማፍቀርን እንደ ጀብድ በመቁጠር በሌላ ወገን ምንም ዓይነት አሳብ ሳይኖር በግድ የራሳቸው ለማድረግ ይጥራሉ:: ይህ ግን ፈጽሞ ትክክል አይደለም:: አንተም «አለኝ» እያለችህ የእርሷ ምክንያት እውነትም ይሁን ሐሰት ተቃውሞዋ የእግዚአብሔር መግለጫ ሊሆን ይችላልና መቀበል ነበረብህ:: እንደመንፈሳዊነትህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ብቻ ሳይሆን መቀበልም ይገባልና! የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ የአንተ ልትሆን አልቻለችም:: እግዚአብሔር ለአንተ የምትሆንህን እውነተኛ የትዳር ጓደኛ ጊዜው ሲደርስ ሊሰጥህ ይችላልና ያንን አስበህ ራስህን ለዚያ ልታዘጋጅ ይገባል:: «ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና» በእግዚአብሔር ላይ ከታመንክ አሁን «መርሳት» አልቻልኩም ያልከውን ስሜት ማሸነፍ ትችላለህ::

ስለሆነም ያጣኸውን ነገር እያሰብክ የዛሬውንና የነገውን ሕይወትህን ባታበላሽ መልካም ነው:: ዛሬ እርሷን እያሰላሰልክ የትምህርት ውጤትህ ቢበላሽብ የሚደርስብህን ነገርና የሚገጥምህን ችግር አስብ:: ማሰብ የሚገባህን ነገር በጊዜው ባለማሰብ የትምህርትህ ብቻ ሳይሆን በቀቢጸ ተስፋ በነፍስም እስከመጎዳት ልትደርስ ትችላለህ:: የማይገባህንና የሌላ የሆነን ሰው መፈለግህም መልካም አይደለም:: ሶምሶን ኃይሉን /ጸጋውን/ ያጣው ለእርሱ ያልተሰጠውን በመፈለጉና ከማይገባ ቦታ በመዋሉ ነው::

በዚህ ላይ ክርስቲያን መሆንህንም አስብ:: አጉል ራስህን ደካማና ልፍስፍስ አድርገህ በመቁጠር የገጠመኝን ፈተና መወጣት አልቻልኩም አትበል:: ዓላማህን፣ያለህበትን ቦታና ጊዜ፣የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምንነትና የተሰጠህን ጸጋ ማሰብ ከቻልክ የማታሸንፈው ነገር አይኖርም:: «በእርሱ በወደደን ከአሸናፊዎች እን በልጣለንና::» ሮሜ.8÷38:: ዩኒቨርሲቲ የገባኸው ለትዳር ሳይሆን ተምረህ ራስህን ችለህ ወገንህን፣አገርህንና ቤተ ክርስቲያንህን ለማገልገል እስከሆነ ድረስ የመጀመሪያውና ዋነኛው ዓላማህ ይኸው መሆን አለበት:: በዚህ መሐል የገለጽከውን ዓይነት ፍቅር ቢገጥምህም መልሱ የሚያስደስትህ /እሺ/ ቢሆን እንኳን እንደመጣ መቀበል የለብህም:: ያለጊዜው መጥቶ ከዓላማህ ሊያሰናክልህ መሆን አለመሆኑን በርጋታ ማረጋገጥ ይኖርብሃል:: ከዓላማህ ተሰነካክለህ÷ እርሷንም ሳታገኝ ራስህንም ከማጣት መድረስ የለብህምና በቅድሚያ ራስህን አድን::



www.eotcmk.org

ትኩረትህ በትምህርትህ ላይ ብቻ ይሁን። ተማሪ መሆንህን አስበህ ሌሎች ተጨማሪ ሸክሞችን በላይህ ባትጨምር መልካም ነው። አብሬችሁ ሆናችሁ /ዘወትር እየተመለከትካት/ መርሳት አቅቶህም ከሆነ ከርሷ ለመራቅ ሞክር። እርሷን ሊያስታውስህ የሚችሉትን ነገሮች /ፎቶግራፎች፣ጓደኛ፣ቦታዎች/ ከአጠገብህ አርቅ። የበለጠም ጸልይ። በእግዚአብሔር ታመን። እርሱ ኃይልና ብርታቱን እንዲሁም የልብ ህንም መሻት ይሰጥሃል።

ስለዚህ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመርተህ፣ዓላማህን በማስቀደም ከገጠመህ ፈተና ልትወጣ ይገባል። ያን ጊዜ ከአሰብከበት ትደርሳለህ። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔር ለአንተ የሚላትንም ታገኛለህ።

## ኃጢአቴን መናዘዝ እፈራለሁ

*__ጥያቄ__ ስለ ንስሐ ሲነገር እሰማለሁ። እኔም ንስሐ መግባት እንዳለብኝ አስባለሁ። ኃጢአትን በካህን ፊት መናዘዝ እንደሚገባም ተምሬአለሁ። ይሁን እንጂ ኃጢአቴን በካህን ፊት ቀርቤ መናገር እንዳለብኝ ሳስብ እጨነቃለሁ። ለመሆኑ በኃጢአቴ ከተጸጸትኩ ብቻ አይበቃም? በካህን ፊት ቀርቤ ኃጢአቴን ለመናገር በጣም እፈራለሁና ምን ይሻለኛል?*

*ወ/ት ምሕረት /ቃሊቲ/*

__መልስ__ የእርስዎ ችግር የንስሐን ምንነት በሚገባ ያለማወቅ ችግር ነው። ንስሐ ማዘን፣መጸጸት፣በሠሩት በደል ማፈር ነው። 2ቆሮ.7÷10-11። አንድ ሰው ስለሠራው ኃጢአት አዝኖና ከተጸጸተ ወደ መምህረ ንስሐው ሄዶ ኃጢአቱን ይናዘዛል። ማቴ. 18÷18። ኑዛዜም እግዚአብሔር ሳይ ፈርድ በራስ ላይ ፈርዶ ራስን በሰውና በእግዚአብሔር ፊት መክሰስ ወይም መውቀስ በመሆኑ የግድ አስፈላጊ ነው።

አንድ ክርስቲያን ክርስቶስ በደሙ ከዋጀው በኋላ የእርሱን ውለታ ዘንግቶ ንጹሑንና ቅዱሱን ሰውነት በኃጢአት ማቆሸሽ ስለማይገባ ባው ንስሐ ይገባል። በኑዛዜ ጊዜም ራሱንም÷ክርስቶስንም መበደሉን በማወቅ ራሱን ተከሳሽ÷ካህኑን አስታራቂና ዳኛ አድርጎ ከእግዚአብሔር ፊት እንደቆመ ያስባል። ካህኑም «በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ነው፤ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ነው» በማለት ከእግዚአብሔር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከኃጢአት እሥራት ይፈታዋል፣ ይመክረዋል÷ያስተምረዋል፤ በጸሎቱም ያስበዋል። ይህ ሁሉ የሚ ሆነው በግልጽ ተነጋግሺውና ካህኑ እየተያዩና እየተነጋገሩ ሲሆን ነው። ምንአልባትም እንደዚህ ማድረጉ በእርስዎ እንደጠደረሰው ሊያስፈራ ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ይህ በራሱ በስውር ያለ ፍርሃት /ያለ ሃፍረት/ የተሠራ ኃጢአት ክፍያ /ቅጣት/ ዋጋ ነው። ይህም «ኃጢአቴን ሌላ ሰው አውቆታል የሚል ኀፍረት እንዲሰማን ያደርጋል። በስውር የሠራነው ኃጢአት መገለጡን ዐው ቀን እናዝናለን።

ምንአልባትም እንደዚህ ዓይነት ነገር ሊፈጠር የሚችለው /በካህን ፊት ራስን መግለጥ የሚያስፈራው/ ለራስ ክብር በመጨነቅ /በማሰብ/ በሰው ፊት ንፁህ መስሎ ለመታየት በመፈለግ ወቀሳን በመፍራት÷ የእግዚአብሔርን ፍቅር ካለ መረዳት በመናፍቃን የጥርጥር እንክርዳድ ተጽእኖ የተነሣ÷ ከሰይጣን ጾር፣ ወዘተ ሊሆን ይችላልና የችግርዎን መነሻም ይመርምሩት። ለምሳሌ በመናፍቃን ተጽእኖ የተነሣ በኃጢአት መጸጸት ብቻ አይበቃም ወይ? እስከማለት ደርሰው ከሆነ ቃለ እግዚአብሔር ብቻ ቢሰሙ÷ለጥያቄም መልስ ቢያገኙ ወይም በማይመች አካሄድ ባይጠመዱ እንደዚህ ከጥርጥር የተነሣ አስጨናቂ መስሎ የሚታየው ነገር ይበሩልዎታል። ከሰይጣንም ጾር እንደሆነ ዘወትር ችግሩን በግልጽ ከንስሐ አባትዎ ጋር እየተነጋገሩበት በጾምና በጸሎት ይትጉ።

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተገለጠው በድብቅ የተሠራ ኃጢአት በእግዚአብሔር ከመገለጡ በፊት በበደል ተጸጽቶ ራስን በሰውና በእግዚአብሔር ፊት መውቀስና መክሰስ አስፈላጊ ነው።ኢያሱ.7÷1-14። የሐዋ. 5÷1-11። ይህም የኃጢአትን አስከፊነት በሚገባ እንድንረዳ ያደርገናል። እንደዚህ ማድረግ የቻለ ሰው ዳግመኛ ወደ ኃጢአቱ አይመለስም። ኃጢአት ምን ያህል አስከፊ /መራራ/ መሆኑን ይረዳልና!

እንደዚህ ማድረግ የሚቻለውም ከላይ እንደገለጽነው የንስሐን ምንነት በሚገባ ሲረዱ÷ የእግዚአብሔር ፍቅር ሲታሰብና ፍጹም እምነትና ትኅትና ሲያዝ ነው። በኃጢአት ከልብ መጸጸትና ትኅትና ካለ ራስን በካህን ፊት ዝቅ ማድረግ ይቻላል። በዚህም ከእግዚ አብሔር ዘንድ በረከት ይገኛል።

ቤተክርስቲያን እንደምታዘው አንድ ሰው ንስሐ ገባ የሚባለው በኃጢአቱ ተጸጽቶ መናዘዝ ሲችል ነው። ይህም ሥርዓት በሐዋርያት ዘመን የነበረ ነው። «...የጌታም የኢየሱስ ስም ተከበረ÷ አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር።» የሐዋ.19÷18

ስለዚህ ኃጢአትዎን መጥላትዎንና ከልብ መጸጸትዎን የሚያረጋግጡትና ዳግመኛም ወደ ፈጸሙት ኃጢአት የማይመለሱት ፊት ለፊት ለካህን ተናግረው «እግዚአብሔር ይፍታህ» ሲባሉ ነውና ጊዜ ሳይሰጡ ይፈጽሙት። መጸጸት ማለትም ትርጉም የሚኖረው በተግባር መገለጽ ሲችል በኑዛዜና በሕይወት መታደስ ሲታጀብ እንጂ ባዶ መጸጸት ብቻ ዋጋ የለውም። እንደዚህ ከተጸጸትንበት ብቻ አይበቃም? የሚሉ ሰዎች በክርስቲያናዊ ኑሮአቸው ሰውን ማሳየት የማይችሉ÷ ከሕግ እግዚአብሔር ወጥተው የራሳቸውን መንገድ የሚፈልጉ ናቸውና በእግዚአብሔር ቤት መጽናት አይችሉም። የጀመሩትን ለፍጻሜ አያደርሱም። የንስሐ ፍሬ ማፍራት አይችሉም። ለዚህ ይሁዳን ማን ማት ብቻ ይበቃል። ይሁዳ አምላኩን ለገንዘብ ሲል አሳልፎ በመስጠቱ ተጸጽቶ ነበር። ነገር ግን በተግባር አንዳች የፈጸመው ነገር አልነበረም። ሁልጊዜም ከሃዲነቱ እንደ ተነሣ ይኖራል። ስለዚህ ንስሐ ሲገቡ በኃጢአት ከተጸጸቱ በኋላ መናዘዝ የእግዚአብሔር ሕግ በመሆኑ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሊፈጽመው ይገባል። የሐዋ.5÷1-11፤ማቴ.8÷1-4፤ኢያሱ 7÷14።

እንግዲህ እነዚህን ዓይነት ነገር ሊፈጠር የሚችለው /በካ ህን ፊት ለመናዘዝ ሳይፈሩ ምን ያህል አስደሳች እንደሆነ አስበው ሊፈጽሙት ይገባል። ስለዚህ በሰው ፊት የሚሆነውን ብቻ ሳይሆን ማሰብ ያለብዎት ከእግዚአብሔር የሚያገኙትን ዋጋም [illegible] ብቻ ሊሆን ይገባል።



www.eotcmk.org

# የቤተክርስቲያናችን ትምህርት በዚህ መልኩም ቢቀርብ

❖ ዐውደ ትዕይንት ❖ ዐውደ ጥናት

/ሰቡጊዳ/

«በቃ አሁን ታረቅን። እኔ ከጥግ ቆማችሁ እጃችሁን በማንሣት ሰማይ ሰማይ እያያችሁ ብቻ የቆማችሁ ይመስለኝ ነበር። እንዲህ በሥራ ከሆነማ በቃ ታርቀናል፤ አብረን እንሠራለን» ያለኝ ዩኒቨርስቲ ያስተማረኝ አንድ ዶክተር ነበር። ማኅበራችን ከመጋቢት 20–23 ባዘጋጀው ዐውደ ጥናት በአንዱ ተሳትፎ ሲወጣ ልሸኘው ስከተለው ተማሪዎቹ ሁሉ ሲፈታ አይተን የማናውቀውን ፊቱን ፈገግ አድርጐ ይህንን አለኝ።

ዶክተር «ሰማይ ሰማይ እያያችሁ » ያለውን ባልቀበለውም የሥራ ነው ሊያስታርቀን መቻሉን፤ አልፎም ከእሱ ጋር ለሥራ በአንድ ላይ እንደሚያስልፈን ከአንደበቱ ስረዳ እጅግ የመደሰቴን ያህል፤ ከኢትዮጵያዊነቱ አልፎ እንደብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን በቤተክርስቲያን አፀድ ውስጥ ሲመላለስ ባደገው ምናልባትም በ «ዲያቆን» ዶክተር ቤተክርስቲያናችን ለጥናት ወደኋላ ቀረሽ ተብላ ትዝብት ላይ መውደቋ አሳዝኖኛል። ይህ ነገር አንድ በአብነት ት/ቤት በተለይ በቅኔው የዘለቁ ሊቅን አባባል አስታውሶኛል። «ይቺን ቤተክርስቲያን ለመተቸት እንኳን ተወልዶ አድጐ ፊደል የቆጠረው ገና በማኅፀን ያለው ይደርስላታል።»

በእርግጥ ሁላችንም የምናምነው አንድ እውነት አለ። ፍልስፍና የማያስፈልገው የነገረ ሃይማኖት ዕውቀቷ ይጠና ሳይሆን ቤተክርስቲያናችንን የዕውቀት ምንጭ የሚያስብሏት የሥነ ዜማ፣የሥነ ጽሑፍ፣የሥነ ሕንፃ ወዘተ… ዕውቀቶቿ እንደ ዕንቁ የዕውቀት ሀብትነታቸው ከአብራኳ በተከፈሉ ልጆቿ አንድ በአንድ እየተመዘኑ ተጠንተው ለትውልዱ በሚገባ መልኩ አልቀረቡም። የዚህን እውነታ ደግሞ በከፍተኛ ትምህርት ያለፉም ሆነ ያላለፉ ነገር ግን በተጠቀሱትም ሆነ በሌሎች የቤተክርስቲያን የዕውቀት ክፍሎች ዙሪያ ሳንብብ ብለው አብያተ መጻሕፍትን ያሰሱ ሁሉ ያረጋግጡታል። ይህንን እውነታ ለማፍረስ ጥረት ያደረጉ ከሚመስሉ ጥቂት የኢትዮጵያ ልጆች በስተቀር ኢትዮጵያዊው ዕውቀት በኢትዮጵያውያን ተጠንቶ አይገኝም። የሚገኙት የቤተክርስቲያናችንን ታሪክ፣ቋንቋና ይትበሀል ሁሉ በሚያውቁ ፈረንጆች «የተሠሩት» ናቸው። ብዙዎች እንደሚስማሙበት፣ በዐውደ ጥናቱ ሳምንትም በአንጽንኦት እንደተነገረው ይህ ጉዳይ ትክክለኛው የቤተክርስቲያናችን ትምህርት እንዲበረዝና የሌለ ነገር እንዲጨመርበት ከማድረጉ በላይ ቤተክርስቲያናችን ተንከባክባ ይዛ ያቆየችንን ዕውቀቷንና፣ትጋትን ከዓላማ ጽናት ጋር እያስተማረች፣ ጡቷን እያጠባች ያሳደገቻቸውን ልጆቿን ማንነትና የትነት እንዲነጠቁ አድርጓል። ምሳሌ እንጥቀስ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን አሳምረን እንደምናውቀው ቤተክርስቲያናችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱሳንን፣ሰማዕታትና መላእክትን እያነሣች እያንዳንዱን የሰውነት አካላቸውን በመጥቀስ የምታመሰግንበት መልክእ የተባለ የጸሎት ስልት /style/ አላት። ይሁንና ይህን የጸሎት ስልታችንን ያለምንም መረጃ ማን ያስጥለኛል በሚል የትእቢት መንፈስ ዶ/ር ክርስቲን ቴደርስን የተባለች ስዊድናዊት ሴት በአንድ ስርቆታዊ መጣጥፏ እሷ ማስረጃ ያለቻቸውን ሀሳቦች ጠቃቅሳ ስልቱን ኢትዮጵያውያን ከእሷ አገር እንዳመጡት እንጂ የእኛ ነው ልንለው እንደማንችል ልትሞግተን ሞክራለች።

ሌሎች ደግሞ ቤተክርስቲያናችን ቅዱሳንን በምትመዘግብበት ዓምዷ ያስፈረችውና በርካታ የነገረ ሃይማኖት የጸሎት መጻሕፍትን ጽፎልን ያለፈውን በዚያም «ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ» እያልን ሁሌ የምናስታውሰውን ታላቅ ኢትዮጵያዊ አባት አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫን አርጠመናዊ ነው በማለት ያልሆነውን ዜግነት እንስጥህ ሲሉት እናያለን።

ምንም እንኳን ወደፊት በዚህ ዙሪያ ሰፋ ያለ ጽሑፍ ለማቅረብ ሙከራ የማደርግ ቢሆንም ከምሳሌው አንድ ልጨምርና ልለፍ። በፍልስፍናው የዓለምን ቀልብ የሳበውንና «ኢትዮጵያዊው አርስጣጣሊስ» የሚባለውን ፈላስፋው ዘርዐያዕቆብን የእናንተ አይደለም ፈረንሳዊ እንጂ፣የፍልስፍና ጽሑፉም የፈረንሣይ ነው ይሉናል።

ይህንን ስል ለምን ነክጠተውብን ከሚል ስሜት እንዳልሆነ ልብ ይሏል። አባቶቻችን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው በርካታ የነገረ ሃይማኖት መጻሕፍት የጻፉት ለኢትዮጵያውያን ድኅነት ብቻ አይደለም። ነገር ግን ጠባችን ለምን የሆነውን ወዳልሆነ ወሰዱት? ነው።

ብዙ ሊያነጋግረን ይችል ይሆናል እንጂ. «ሰዎቹ» እንዲህ እንዲህ እንዲሉ ያስቻላቸው የበር ጠባቂና አንሥተን እንኑጥ ሲሉም ከእጃቸው የሚያስጥል መጥፋቱ ነው። እንደእውነቱ ያወቁትን ለማሳወቅና ካለማወቅ ትክክለኛው የቤተክርስቲያን ነገር ሲጣመም ዐይተውም በቶሎ ለማስተካከል ዕለት ዕለት የሚተጉ አባቶች እንዳሉ ሁሉ እኛ ያወቅነውን ማን አባቱ ሊያውቅ ይፈልጋል? ብለው የዕውቀት በራቸውን የከረቸሙ የጋን መብራቶችም አሉ። ይህንን ያዩ ሰዎችም ጥቂቱን አግዝፈው «ቄስ ካወቀው ጥሩ ሰይጣን ያወቀው ጥፋ» እያሉ ሲዘብቱብን ይስተዋላሉ። ይህ መክሊት ቀብሮ ደግሞ እንኳንስ ለትችት በቀደመው ሰው በይቅርባዩ አምላክም የተወደደና ይቅርታን የሚያገኝ ድርጊት አይደለም። /ማቴ.25÷26/ የአንዱ አዘጋጅ ጥናታቸውን ካቀረቡ በኋላ ለተሳታፊዎች ያሉት የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ የከነከነ፣ በወቅቱ የነበሩትን የቤተክርስቲያን ሊቃውንትም ድንገት ከች ብሎ ያነጋገረ ምናልባት ያስደነገጠ አባባል ነበር። «በእግዚአብሔር የማይከለከለውን ጥበብና ማስተዋል አበው ሊቃውንት እንዴት ትከለክሉናላችሁ?»

ነገርን ነገር አንሥቶት





www.eotcmk.org

ይኸን ያህል ካልን ለዚህ ጽሑፍ መቅረብ ምክንያት ወደሆነው ኤግዚቢሽን በሱም በኩል ወደ አራቱ ቀን ዐውደ ጥናት እንሂድ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በቤተክርስቲያን ታሪክ በዚህ መልኩ /በስፋት/ ሲቀርብ የመጀመሪያ የሆነ ዐውደ ትዕይት ከመጋቢት 17–24 በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል አዘጋጅቶ ነበር። «የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንት፣ዛሬና ነገ» በሚል ርዕስ የቤተክርስቲያኗን ታሪክ፣ዕውቀት ንዋያተ ቅድሳት፣ዜማ፣ ቅዱሳት መካናትና ሥዕላት መሠረት አድርጐ በተቀናበረ ዐውደ ትዕይት ለዕይታ የሚቀርብ ምን ሊሆን እንደሚችል ከተማማተ ግምት ላይ የሚጥል ባይሆንም ወደ ዐውደ ጥናቱ ከመሄዳችን በፊት የዐውደ ትዕይንቱን አጭር ገጽታ በመጠኑም ቢሆን ላቅርብ።

ዐውደ ትዕይንቱ ዘጠኝ ክፍሎች ነበሩት። የመጀመሪያው ክፍል የታሪክ ክፍል ነበር። በዚህ ክፍል ኢትዮጵያ ከሕገ ልቡና ጀምራ እስከ ሕገ ወንጌል ያለፈችበት የታሪክ ሂደት በፎቶ ግራፍ፣ በሥዕልና በቻርት ተደግፎ ቀርቦ ነበር። ኢትዮጵያ ከሕገ ልቡና ጀምሮ ሕገ ወንጌልን እስከተቀበለችበትና ከዚያም በኋላ ያለው የቤተክርስቲያን የታሪክ ሂደት ቀርቧል። የዚህ ክፍል ዕይታ ከተጠናቀቀ በኋላ የቅዱሳት መካናት ዐውደ ትዕይንት ንዑስ ክፍል ይገኛል።

ይህ ክፍል የአብያተ ክርስቲያናት፣ገዳማት፣አብነት ት/ቤቶች፣ጥንታውያን አድባራትና የጠበል ቦታዎች በሚል እንደ ታሪኩ ሁሉ በፎቶ ግራፍ፣ በቻርትና በሥዕል የተደገፉ መረጃዎች ቀርበውበታል። ከዚያም ቤተክርስቲያናችን ልዩ ልዩ የቤተመቅደስ ሥርዓቶች የምትፈጽምባቸው ንዋያተ ቅድሳት ሥልጣነ ክህነት ባላቸው የማኅበሩ አባላት ገለጻ ጋር የሚቀርቡበት የንዋያተ ቅድሳት ንዑስ ክፍል ይገኛል።

ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍት ንዑስ ክፍል ይገኛል። በዚህ ንዑስ ክፍል የቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ በኢትዮጵያ /ቅድመ ክርስትና ፣ጥንተ ክርስትና፣ መካከለኛው ዘመንና የቅርብ ዘመን/ በሚል በአራት ተከፍሎ ቀርቧል። ከዚያም ጠበብ ባለ መንገድ የቤተክርስቲያናችን መጻሕፍት ከይዘታቸው አንጻር በ10 ተከፋፍለው በዓይነት በዓይነታቸው ከአብነት ጋር ቀርበዋል።

ከዚህ ንዑስ ክፍል በኋላ የቅዱሳት ሥዕላት ንዑስ ክፍል ይገኛል። በዚህ ንዑስ ክፍል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት መለያ ባሕርያት ፣የአሣሣል ቴክኒክ፣ ሊሰጣቸው ስለሚገባው ክብርና የሐረጋት አሣሣል በምሳሌ ተደግፈው የቀረቡ ሲሆን ከዚህ ጋር በአሣሣል ቴክኒካቸውም ሆነ በይዘታቸው ከቤ ተክርስቲያን ቀኖና ውጭ የሆኑ ሥዕላት በምሳሌነት ቀርበዋል

ቀጣዩ ደግሞ ዜማ ንዑስ ክፍል ነው። በክፍሉ ስለ ኢትዮጵያዊው የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ የዜማ ታሪክና ዓይነት እንዲሁም የዜማ መሣሪያዎች ቀርበዋል።

የተዘረፉና የተጐዱ ቅርሶች በሚለው ቀጣዩ ክፍልም ቅርሶቻችን በተለይም ንዋያተ ቅድሳት የደረሰባቸውንና እየደረሰባቸው ያለውን ሰው ሠራሽ /ቃጠሎ፣ ስርቆት ...ወዘተ/ እና ተፈጥሮአዊ /ማርጀት፣ብል ... ወዘተ/ ጉዳቶች ከአብነት ጋር ቀርቧል።

ቤተክርስቲያን ነገ ምን ዓይነት መልክ ይኖራታል? የሚል ጥያቄ አንሥቶ መልስ ለመስጠት የሚሞክረው ትንቢታዊ ክፍል ደግሞ ቀጣዩ የዐውደ ትዕይንቱ ንዑስ ክፍል ነበር። ንዑስ ክፍሉ ከሌሎች በተለየ ቤተክርስቲያናችን በልማቱ ፣ዘመናዊ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂን /ዌብ ሳይት፣ኢ–ሜይል፣ኢንተርኔት...ወዘተ/ በመጠቀሙ ወጥ የሆነ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ዲዛይን በመያዙ ምን ዓይነት ገጽታ ሊኖራት እንደሚችል በአዘጋጆቹ ትንቢታዊ እይታና ምሳሌ ቀርቦበታል።

የዐውደ ትዕይንቱ አዘጋጅ የሆነውን ማኅበር የሚያስተዋውቀውና የዐውደ ትዕይንቱ የመጨረሻ ንዑስ ክፍል ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማ/ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ንዑስ ክፍል የተባለው ነው። ማኅበሩ ከጅምሩ አሁን እስካለበት ደረጃ ያለው ታሪክ ከማኅበሩ አጠቃላይ መዋቅር ጋር ቀርቧል። በተጨማሪም የጀመረውን የገዳማትና አድባራት ዕርዳታ እንዴት አድርጐ ለመቀጠል እንዳቀደ የሚያሳይ ፕላን በቻርት ቀርቧል።

ዐውደ ትዕይንቱ በመጠኑ ከላይ በተገለጠው ሁኔታ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ለሕዝብ ክፍት ሆኖ በዐውደ ትዕይንት አካልነቱ የተዘጋጀውና ከመጋ ቢት 20–23 ቀን የተካሄደው ዐውደ ጥናት ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባሕል ማዕከል አዳራሽ እየተካሄደ ነበር።

ደግሞ የቤተክርስቲያን ነገር ጥናት የሚሠራበት ነው እንዴ? ከሚለው ጀምሮ የሌለ ታሪክ ሊታመጡብን ነው! የሚሉት አባባሎች የዐውደ ጥናቱ አዘጋጆች የቅርብ ጊዜ ትዝታዎች ናቸው። ለማንኛውም ነገረ ቤተክርስቲያንን መሠረት ያደረገ ዐውደ ጥናት ሲዘጋጅ ይህ የመጀመሪያው እንደመሆኑ የእግዚአብሔር ዕርዳታ ታክሎበት ከብዙ ድካምና ጥረት በኋላ ዐውደ ጥናቱ እንደ እግዚቢሽኑ አካልነቱ «የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና፣ዛሬና ነገ» በሚል ዐቢይ ርዕስ በብፁዕ በአቡነ ቄርሎስ የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የሰሜን ወሎና የዋግኅ ምራ አህጉረ ስብከት ሊቀጳጳስ ረቡዕ መጋቢት 20 ቀን 1992 ዓ.ም ተከፈተ።

### ረቡዕ መጋቢት 20 ቀን 1992 ዓ.ም.

በአምስት ክፍላት ተከፋፍሎ የቀረበው ይህ ዐውደ ጥናት የተጀመረው አቶ ላቀው ይርጋ ከባሕልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር «የያሬዳዊ ዜማ ታሪኩ፣ዕድገቱና ባሕርያቱ» በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ነበር። «የቅዱስ ያሬድ ቀን» በሚል በተሰየመው በዚህ ቀን በቀረበው ጥናት ስለኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ታሪክና በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ስለደረሳቸው አምስቱ ጸዋትዎ ዜማዎች /ድጓ፣ጾመ ድጓ፣መዋሥዕት፣ ዝማሬና ምዕራፍ/፣ የዓመቱን ጊዜያት በአራት ከፋፍሎ /ክረምት፣ መፀው፣ሐጋይና ፀደይ/ መዝሙር ስለ ማዘጋጀቱ ስለ ስምንቱ የዜማ ምልክቶች /ይዘት፣ ድፋት፣ ሂደት፣ ቁር



www.eotcmk.org

ጥ ፣ቅናት፣ጭረት፣ ርክርክና ደረ
ት/ ቀርቧል፡፡ ይህን የያሬዳዊ ዜማ
ትምህርት ጠብቆ ለትውልድ ለማው
ረስ ወደፊት ምን መደረግ እንዳለ
በትም አቶ ላቀው ከመፍትሔ ሀሳብ
ጋር አቅርበዋል፡፡ ከጠቆሚቸው የመ
ፍትሔ ሀሳቦች ውስጥ የዜማ ማስ
ልጠኛ ተቋም በአዲስ መልክ ማዕከላ
ዊነት ባለው ቦታ በማቋቋም ሥር
ዓተ ትምህርት ቀርፆ ማስተማር፣
በየገዳማቱ ያሉትን የዜማ መጻሕ
ፍት ወደ አማርኛ በመተርጐም
ትውልዱ እንዲያነባቸው ማድረ
ግ፣የዜማ ሊቃውንት ዕውቀታቸውን
ወደ ጽሑፍ የሚለውጡበትን
መንገድ ማመቻቸት የሚሉት ይገኙ
በታል፡፡ በተነሡት ነጥቦች ላይ ተሳ
ታፊዎች ጠቃሚ ውይይቶችን አካሂ
ደዋል፡፡

**ሐሙስ መጋቢት 11 ቀን 1992 ዓ.ም**

የዕለቱ ስያሜ «የቅዱስ ላሊ
በላ ቀን» የሚል ነበር፡፡ በዚህ ዕለት
ሁለት የጥናት ወረቀቶች ቀርበዋል፡፡
የመጀመሪያው ጥናት «የሕንፃ
ቤተክርስቲያን አሠራር በኢትዮ
ጵያ» የሚል ሲሆን የጥናቱ አቅራ
ቢም አቶ ዓባይነህ ካሤ /ከማኅ በረ
ቅዱሳን/ ናቸው፡፡ የጥናቱ አቅራቢ
በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውስጥ
ያሉትን የሕንፃ አብያተ ክርስቲያ
ናት አሠራር ዓይነት ለማው
ጣት በቂ ጥናት አድርጌያለሁ ባይ
ሉም እስከዛሬ ካዩአቸው በመነሣት
የኢትዮጵያ የሕንፃ ቤተክርስቲያን
የአሠራር ዓይነቶችን በአምስት
ከፍለው አቅርበዋል፡፡ እነሱም ክብ፣
መስቀል ግር፣ ዋሻ፣ፍልፍል፣ ሰቀ
ልማ ናቸው፡፡ ከሥርዓት፣ ከትው
ፊት፣ከምጣኔ ሀብት እና ከጊዜ አን
ፃር የእያንዳንዱን የሕንፃ ዓይነቶች
ጥቅም አስቀምጠዋል፡፡ አቶ ዓባይነህ
ከዚህም በተጨማሪ በቀድሞ ጊዜ
ያት ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት
በተራራ ላይ እንደሚ ታነፁ ጠቅሰው
ያ የሆነበትን ምሥ ጢራዊ ትርጉም
ከጥቅሙ ጋር በተብራራ መልኩ
አስቀምጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም
በቅጽረ ቤተክርስቲያን ስለሚታነፁ
ሌሎች ሕንፃዎችም ያትታሉ፡፡ እነ
ሱም ቤተልሔም፣የማጥመቂያ /የክር
ስትና/ቤት፣የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ፣
የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተጠቅሰ
ዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በጥናቱ አቅራቢ
ሊጨመሩ የሚገባቸው ሕንፃዎች
ያሏቸውን እንደ ቤተመጻሕፍት፣
ቤተመዘክር ያሉትን ጠቅሰዋል፡፡
በመጨረሻም የጥናቱ አቅራቢ ሕንፃ
አብያተ ክርስቲያናት እንዴት ይታ
ደሱ በሚል ርዕስ ለሕንፃ አብያተ
ክርስቲያናትና ታሪካዊ ሥፍራዎች
የሚደረገው ጥገና ሕንፃዎቹ የቀድ
ሞ መልካቸውን እንዳጠፉ ለትው
ልድ በሚሸጋገሩበት መልኩ መ
ሆን እንደሚገባው ምሳሌዎችን በመ
ጥቀስ አስገንዝበዋል፡፡

ጠቃሚ ጥያቄዎች፣ አስተ
ያየቶችና ውይይቶች የተደረጉበት
ይህ የጥናት ወረቀት ሲጠቃለል
ለዕለቱ ሁለተኛ የሆነው ወረቀት
ቀርቧል፡፡ «The Ethiopian Orthodox
Tewahido Church in Natural Resor-
ces Conservation--- የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ» በሚ
ል ርዕስ በአቶ አሰግድ በዛብህና በአቶ
ታዬ በቀለ የተዘጋጀው ይህ ጥናት
ቤተክርስቲያናችን እንደታላላቅና
ጥንታውያን አፀድ መገኛነቷ ዛሬ
እየተመናመነ ለመጣው የአገሪቱ
የደን ሀብት መጠበቅ እያደረገችው
ያለውን አስተዋጽኦ አሳይቷል፡፡
ከዚህም ጋር ቤተክርስቲያን ለዱር
አራዊት የምትሰጠውን ክብር ልዩ
ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስና አዋልድ
መጻሕፍት ማስረጃዎችን በማቅረብ
በስፋት አሳይቷል፡፡ በመጨረሻም
የጥናቱ አቅራቢዎች መንግሥት
ቤተክርስቲያን እያደረገችው ያለው
ን ይህን አስተ ዋጽኦ ተረድቶ አስፈ
ላጊውን ትብ ብር እንዲያደርግላት
የሚልና ሌሎች የመፍትሔ ሀሳቦችን
አስቀምጠዋል፡፡

**ዓርብ መጋቢት 22 1992 ዓ.ም**

«ኩርዓተ ርዕሱ» በሚል
በተሰየመው በዚህ ቀን «የኢት
ዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥነ ሥዕል
ታሪክና መለያ ባሕርያቱ» የሚል ጥ
ናት በሰዓሊ እሸቱ ጥሩነህ /ካባሕ
ልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር/ ቀር
ቧል፡፡ የዚህ ጥናት ጭብጥ ሥዕልና
የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ፣ ሥዕ
ልና ምእመናን፣የሥዕል ጥበባቱ ዓላ
ማና ተግባራት በሚሉት ነጥቦች
ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

በዘመን ሂደት ውስጥ የኢ
ትዮጵያ የሥዕል ጥበብ የራሱን ዓይ
ነተኛና ልዩ ያሰኘውን የሥዕል ጥበ
ባት አቅጣጫ መፍጠሩን ምን ጭ
ጠቅሶ ያብራራው ይህ ጥናት በአጠ
ቃላይ የኢትዮጵያ ትውፊዊ ክርስቲ
ያናዊ የሥዕል ጥበ ባቱን አገል
ግሎት በሦስት ከፍሎ አይቶታ
ል፡፡ እነሱም የልዩ ልዩ ታሪኮች
መግለጫ ሥዕላትን መሣል ፣የቤ
ተመቅደስ ግድግዳዎችን፣ በሮችን
መስቀላትን፣ልብሰ ተክህኖ የመሣ
ሠሉትን ንዋያተ ቅድሳት ማስጌ
ጥና ንዋየ ምእመናንን መሸለም
የሚሉት ናቸው፡፡ በቤተክር ስቲ
ያናችን ሥርዓት በአራቱም የመቅ
ደስ ግድግዳ አቅጣጫዎች በአራት
የተከፈሉ የተለያዩ ሥዕላት እንደ
ሚሣሉ የጠቀሰው ይህ ጥናት በአ
ሁኑ ወቅት እየታየ ያለውን የባዕ
ዳን ሥዕላት ወረራ አስመልክቶ
የችግሩን መንስኤና ይሆናሉ ያላቸ
ውን የመፍትሔ ሐሳቦች አቅር
ቧል፡፡ የመፍትሔ ሐሳቦችን በሚ
መለከት ቤተክርስቲያን ትውፊታ
ዊ የሥዕል ጥበባቷን አስመልክታ
ልዩ ጉባኤ ማዘጋጀት እንዳለባት፣
በ«ምሥጢራት» ስም የተያዙ የሊ
ቃውንቷና የሰዓልያን ዕውቀቶ
ችና ክሂሎቶች ሳይበታተኑ ወይም
በሥጋ ሞት ምድራዊ ዓለምን
ሳይለቁ የምታስቀርበትን መንገድ
ማፈላለግ እንዳለባትና በልዩ ልዩ
ቦታዎች የሚገኙ ሥዕላቷን በኤሌ
ክትሮኒክስ መሣሪያዎች አስነ
ስታና አሰባስባ የራሷን ሥዕላት
ለምእመናን አገልግሎት ለማዋል
ማሳተም /ማባዛት እንደሚገባት
ተጠቁሟል፡፡

**ቅዳሜ መጋቢት 23/1992 ዓ.ም**

ዕለቱ በሁለት ክፍላተ
ጊዜያት ተከፍሎ አምስት የጥናት
ወረቀቶች የቀረቡበት ነበር፡፡ ይኸ
ውም ጠዋትና ከሰዓት በሚል
ሲሆን በጠዋቱ ሁለት ጥናቶች
ቀርበው ነበር፡፡

የመጀመሪያ «በቅርሶች
በተለይም በንዋያተ ቅድሳት ላይ
እየደረሱ ያሉ ጥፋቶች» በሚል
ርዕስ የቀረበው ነው፡፡ በአቶ
ጥላሁን ገ/ ሥላሴ ከቅርስ ጥናትና
ጥበቃ የቀረበው ይህ ጥናት ከሙዝ
የሞቹ አለመስፋፋት ጋር ተዳምሮ
በንዋያተ ቅድሳት ላይ ስለደረሰው
ና በመድረስ ላይ ስላለው ሰው ሠ
ራሽ /ጦርነት፣ ዘረፋ፣ የእሳት
ቃጠሎ ወዘተ / እና የተፈጥሮ
/ማርጀት፣በብል መበላት... ወዘ
ተ.../ ጥፋት ከምሳሌ ጋር ታትቷ
ል፡፡ ወደፊትም ምን መደረግ እንደ
ሚገባው ተጠቁሟል፡፡ ከዚህም





'

www.eotcmk.org

ውስጥ ከሁሉ በፊት ሳይንሳዊ የሆነ አገር አቀፍ የቅርስ ምዝገባ መካሄድ አለበት፤ ምን እንደጠፋን? ማን እንደወሰደብን? መቼ እንደጠፋብን? አሁንም አናውቅ ም፡፡ ምክንያቱም ምን እንዳለን ስለማናውቅ ምን እንደጠፋን ልናውቅ አንችልም የሚል ይገኝበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኅብረተሰቡን ስለ ቅርስ ማስተማር፣ የአብያተ ክርስቲያናትን የቅርስ አያያዝ ሁኔታ ማሻሻል፣ቁጥጥርን በቅንጅት መሥራትና ሙዚየሞችን ማቋቋም በመፍትሔ ሀሳብነት ቀርበዋል፡፡ ሰሚከተገኘ በሚያሳዝን ሁኔታ እየተጐዱ ሳሉት ንዋያተ ቅድሳት በርካታ የመፍትሔ ሀሳቦች የተጠቆሙበት ይህ ጥናት ሕጉ ለንዋያተ ቅድሳቱ የሚሰጣቸውንጥበቃ በገመገመውና በአቶ ደረጀ ታፈሰወርቅ በቀረበው አጭር ጥናት ተደግፎ ጠቃሚ ውይይቶች ተደርገውበታል፡፡

«የመገናኛ ብዙኃን አስተዋጽኦ ቅርሶችን በመጠበቅ» የሚለው ሁለተኛው የዕለቱ ጥናታዊ ጽሑፍ ነበር፡፡ በዲ.ዳንኤል ክብረት /ከማኅበረ ቅዱሳን/ የቀረበው ይህ ጥናት በአገሪቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉት የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ የመገናኛ ብዙኃን ቅርሶችን በመጠበቅ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ገምግሞ ወደፊት ማድረግ ያለባቸውን ጠቁሟል፡፡ ጋዜጠኞች የባለቤትነት ስሜት ቢሰማቸው፣ የመገናኛ ብዙኃን ሕዝቡ ሀብቱን ዐውቆ ለቅርሶች ዘብ እንዲቆም አስፈላጊውን ትምህርት ቢሰጡ፣ ቅርስን በተመለከተ የተደራጁ ማኅበራትን ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እየሠሩ ቢያበረታቱ፣በቅርሶች ላይ የሚያተኩሩ ዐምዶችንና የአየር ሰዓቶችን መክፈትና ሌሎች ነጥቦች በመፍትሔ ሀሳብነት ተጠቁመዋል፡፡

የጠዋቱ የዐውደ ጥናቱ ክፍለ ጊዜ ተጠናቆ ወደ ከሰዓቱ ስንሄድ «የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ቀን»በሚል ስያሜ ሦስት የጥናት ወረቀቶች የቀረቡበትን ክፍለ ጊዜ እናገኛለን፡፡

በዚህ ክፍለ ጊዜ በቅድሚያ የቀረበው «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በተክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ አጭር ታሪክና ቅኝት» በሚል ርዕስ በአቶ ገዛኸኝ ጌታቸው የተጠናው ነበር፡፡ ጥናቱ ለኢትዮጵያ አጠቃላይ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ መሠረት የጣለችውን ቤተክርስቲያን ያሏትን መጻሕፍት በዘመን ከፋፍለው የየዘመኑንም ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያት አሳይቷል፡፡ እንዲሁም የቤተክርስቲያናችንን የሥነ ጽሑፍ ታሪክ በአስራ ሦስት በመክፈል ለየክፍሉ ናሙና መጻሕፍትን በመዘርዘር ቀርቦበታል፡፡ በመጨረሻም የጥናቱ አቅራቢ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ያሉዋትን መጻሕፍት ስምና አድራሻ እንዲሁም ስለ መጽሐፍቱ ይዘት በጥቂቱ የያዘ መዝገብ ቢዘጋጅ፣ የቤተክርስቲያን ልጆችም አባቶቻቸው ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት ይጠቀሙበት የነበረውን የግዕዝ ቋንቋ በማጥናት እነዚህን ታሪካዊ መጻሕፍት ቢመረምሩ የሚሉ ምክሮችን አስተላልፈዋል፡፡

«የገድላት አዝማናዊ አከፋፈልና ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ» የሚለው ደግሞ ሁለተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ ነበር፡፡ የጥናቱ አቅራቢ ዲያቆን ኤፍሬም እሸቴ /ከማኅበረ ቅዱሳን/ ናቸው፡፡ የጥናቱ አቅራቢ «የኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የመረጃ ምንጮች» ያሏቸውን ገድላት የተጻፉላቸውን አዝማናት፣ የገድላቱ ጸሐፊዎች የሰጧቸውን ምስክርነቶች መሠረት በማድረግ በሦስት አዝማናት ከፋፍለው አቅርበዋል፡፡ እነሱም የዘመነ አክሱም ገድላት፣ የዘመነ ዛጉዌ ገድላት፣የዘመነ ሰሎሞናውያን ገድላት ሲሆኑ ለየዘመናቱ ዋቢ የሚሆኑ ገድላትን አቅርበዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ተዘጋጅቶ የቀረበው ጥናት ከሁለቱም ወገን /ከቤተክርስቲያንና ከዩኒቨርሲቲው / በመጡ ሊቃውንት ውይይት ተደርጎበታል፡፡

የመጨረሻውና የዐውደ ጥናቱ መዝጊያ የሆነው ጥናት ደግሞ «የግእዝ ቅኔና ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታው» የሚል ነበር፡፡ እንደሌሎች ሁሉ በዚህኛው ጥናት ላይም ጠቃሚ ውይይቶች ተደርገው ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ አስተያየታቸውን ሰጥተው ዐውደ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

እንግዲህ ለሳምንት በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከልና ለአራት ቀናት በአ.አ.ዩ. የባሕል ማዕከል የተካሄደው ዐውደ ትዕይንትና ዐውደ ጥናት ይህን ይመስል ነበር፡፡ ዐውደ ጥናቱ በእግዚአብሔር ዕርዳታ እንዳሰቡት እንደተከናወነ አዘጋጆቹ ያምናሉ፡፡ ከጉባኤውማሳ ሰቢያ የተሳከላቸው ክፍሎች ሁሉ /በ፣ተክህነት፣ሊቃውንት፣ምእመናን፣የከፍተኛ ት/ት ተቋማት/ ቢያስቡበት ለቤተክርስቲያናችን የነገ ጉዞ ጠቃሚ የሚሆኑ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡ ከዚህና ከሌሎች ቁም ነገሮች አንፃር እንደዚህ ዓይነቱ ዐውደ ጥናት መዘጋጀቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ዓይነቱ ልምድ በሰንበት ት/ ቤቶችም ሊለመድ ይገባል፡፡ ታዲያ በዝግጅቶች ሁሉ የአባቶች ተሳትፎ በእጅጉ ሊታከልበት ይገባል፡፡

በመጨረሻም በዐውደ ጥናቱ ላይ የቀረቡትን የጥናት ወረቀቶች እንደ አስፈላጊነታቸው ለመጽሔት በሚሆን መልኩ በተከታታይ እንደምናወጣቸው እየገለጽን ዐውደ ጥናቱ ምንም ዓይነት የገንዘብ ችግር ሳይገጥመው እንዲካሄድ ያስቻለውን የኢትዮጵያ ፊረን ሳይ የባሕል ጥናት ተቋምን፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዐውደ ጥናቱ ዓላማ መሳካት ምቹ የሆነውን አዳ ራሽ በመፍቀድ /የባሕል ማዕከል/ ፣ በዩኒቨርስቲው የመረዳጃ ማኅበ ር ከነሠራተኞቹ በሻይ ቡና አቅር ቦት ፕራትና ፍጥነት ላደረገልን ትብብር እናመሰግናለን፡፡


ረድኤተ እግዚአብሔር
አይለየን


**የሐመረ መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደምበኛ ይሁኑ**

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| ለአዲስ አበበ | 10.00 | 20.00 | 18.70 | 37.40 |
| ለክፍለ ሀገር | 10.50 | 21.00 | 19.00 | 38.40 |
| ከኢትዮጵያ ውጭ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |




www.eotcmk.org




ቅዱስነታቸው ኤግዚቢሽኑን አስመልክተው አስተያየታቸውን ሲያሰፍሩ።



የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በባህል ማዕከል አዳራሽ



ክቡር አቶ ወልደሚካኤል ጫሞ የባህልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ ክቡር አቶ ስምዖን መቻል የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር እንዲሁም ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች በኤግዚቢሽኑ መክፈቻ ወቅት

« **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ** » የሚል መጽሐፍ በቅርብ ቀን በገበያ ላይ ይውላል::

*በአቶ ዓባይነህ ካሤ ተዘጋጅቶ*

*በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል የታተመው*

*ይህ መጽሐፍ* :-

- *የመጻሐፍ ቅዱስ ታሪክ*
- *የመጻሐፍ ቅዱስ ባህል*
- *መጻሐፍ ቅዱስና ትርጉም*

*በሚሉና በሌሎች ርዕሶች ዙሪያ ቤተክርስቲያናችን የምታስተምረው ትምህርት በስፋት ቀርቦበታል:: መጽሐፉን በመግዛት እርስዎንና ቤተሰቦችዎን ያስተምሩ!*

*ማኅበረ ቅዱሳን*

# በማኅበረ ቅዱሳን የንዋያተ ቅድሳት ማከፋፈያ

- የካህናት አልባሳትና ንዋያተ ቅድሳት እናከፋፍላለን
- በተክሊል ለሚጋቡ የሙሽራ ካባዎችን እናከራያለን
- የመዘምራን ልብስ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ እናዘጋጃለን
- ማናቸውንም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ አልባሳት በትእዛዝ እናዘጋጃለን::
- የቤተክርስቲያንን ሥርዓት ጠብቀን፣ቀጠሮዎን አክብረን በተመጣጣኝ ዋጋ እንድንሠራልዎ ይጎብኙን::

**አድራሻችን** አዲስ አበባ...ከምኒሊክ አደባባይ ወደ ስድስት ኪሎ በሚወስደው መንገድ ከመቅደላ ሆቴል አጠገብ :

**ስልክ** 128460

ዋጋው 3 ብር



www.eotcmk.org

©

!" #$ %
& ' ( ) * $++